በቅድሚያ ቢነገር ሌላ ነገር የሚያስብ ሰው የለም። ለልጃችንም፣ ትንሽ ትንሽ ወጣ ማለት ይጠቅማታል። በዚያውም አካላዊ እንቅስቃሴ ታደርጋለች»

«ይህ እርከሱ፣ እንዲያውስ በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ሊያስተውላት ቻለ?» አለ ድንገት ከተኛበት ደንብሮ በመቀመጥ። «በዚህ ቤት ውስጥ ምስጢራዊ ግንኙነት ፈፅመው ሊሆን ይችላል?»

«እንግዲህ ይህን ስታመነኝርክ አትዋል። ምን ጣጣ ነው? ልጃችን ጠንካራ ተፈጥሮአዊ ትህትና እንዳላት እኔ እናቷ እመሰክርላታለሁ። ሰወዬው ያነጋገራት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ለዚያውም እኔ በቦታው ነበርኩ።»

በትንሿ የአትክልት ሥፍራ የነበረውን ሁኔታ በአጭሩ አስታወሰችው።

«እናም» ስትል ማዳም ዱ ማይሌ ቀጠለች። «ስለዕፅዋት አበቀቃቀል ያላትን ዝንባሌ ያወቀው ያን ጊዜ ነው። ሰውዬው ትክክል መሆኑን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። በአትክልት ማብቀያ ውስጥ ከማበቅላቸው ትንንሽ ዕፅዋት መካከል በሙቀት ወይም በድርቁ ምክንያት ሽምድምድ የሚልካለ ሁሌም ለአሊስ እሰጣታለሁ። ወደ ክፍሏ ትወስደውና ከጥቂት ቀናት በኋላ አረንጓዴና ጤነኛ ሆኖ መልሳ ትሰጠኛለች።»

ማዳም ዱ ማይሌ፣ በጥሩ ሁኔታ ተከራክራ ባሏን አሳመነችው። ፖንሴ፣ ከንቱው የመመለስ እድል አይኖረውም ሲል ለራሱ አሰበ። የሰውዬው ሃሣብ ክብር የጐደለውና ሕገወጥ ዕቅድ ቢሆንም፣ ይህን ለማስፈፀም ግን ለምንጊዜውም ዕድሉ አይኖረውም። ይህን የመጨረሻ እንቅፋት በድል በመወጣቱ ሰላምና እርካታ አገኘ። ምንም እንኳ ለዚህ ሁሉ የርሱ ድርሻ ቢኖርበትም፣ ቆንሲሉ፣ ነቢያዊ አሽከሩን በጣም ተራ ማስታወሻ አስይዞ ላከው። «ልጆ፣ ከአባ ጋቦሬ ጋር ሆና ሁልጊዜ ማለዳ በቤትህ ተገኝታ እፅዋትህን ታጠናለች። አሁን ሂድ»



# 2

# ጉዞ ወደ አበሻ ሃገር

# 1

ወደ አበሻ አገር የሚጓዘው የሀሐዩ ንጉሥ የመልዕክተኞች ቡድን፣ ልኮ ከንጋቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ ተንቀሳቀሰ። ሃጂ አሊ፣ በመሪው ግመል ላይ ተቀምጧል። ጭንቅላቱን በአዲስ ሻሽ ጠምጥሟል። እርሱን የተከተለው ጆን ባፕቲስት ነው። ጆን ባፕቲስት፣ በአንድ ቁንጥንጥ ፈረስ ላይ ጉብ ብሏል። ነጭ ላባ ያለበት ሰፊ ነጭ ባርኔጣ አድርጓል። በመጨረሻ ያሉት የውሸቱ አሽከር፣ ነገር ግን እውነተኛው ጀስዊት ዮሴፍ፣ ናቸው። ዮሴፍ ከገለባ በተሠራ ባርኔጣ ፊታቸውን ደብቀው፣ በከተማው መግቢያ በር አጠገብ በቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው ሲጠብቋቸው አገኟቸው። ከኋላ አምስት የጭነት አጋሰሶች ተከትለዋል። ግመሎችና በቅሎዎች ተደባልቀው ጓዝ ተጭነው፣ በጥቂት ነቢያውያን ባሮች ይነዳሉ።

ለጥንቃቄ ሲባል ባለፈው ምሽት በቆንስላው ቤት ከተደረገው ሥነስርዓት በስተቀር የመሰነባበቻ ነገር አልተከናወነም። ከሌሎች ጋር ለመገናኘት ሲመጣ ከለሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ ጆን ባፕቲስት፣ በሰጋሲዮኑ አጥር ሥር አልፏል። ሙሴ ዱ ማይሌና ባለቤቱ ሰገነቱ ላይ ሆነው ምልክት ሰጥተውታል። ይህን ምስኪን ልጅ ሲያዩት እጅግ አዘኑ። ዕጣ ፈንታው ሆኖ፣ በሁሉም መልክ ሲታሰብ ዳግመኛ የማይመለሰው ልጅ፣ በታላቅ ትህትና እንደሚጨነቅላቸውና እንደሚያስባቸው በሚያመላክት መልክ፣ ዓይኖቹ በምሥጋና እምባዎች ተሞልተው ሰላምታ አቀረበላቸው። እውነቱ ግን፣ ጆን ባፕቲስት ለሁለቱ አዛውንት ሽርጣኖች ተጨንቆላቸው ሣይሆን፣ ተስፋ ለሚያደርጋትና ከበስተኋላቸው በሁለተኛው ፎቅ ባለው በአንደኛው በረንዳ ላይ ሆና ለምትመለከተው ለአሊስ ነበረ።

ቀጥሎ የተከናወነው፣ ለቱርኮች የሚያቀርቡት ረዥምና ሞቅ ያለ የደህና ሁኑ ሰላምታ ነው። ቅፍለቱ አስፈላጊውን የጥበቃ ሁኔታ እንዲያገኝ ያደረገው ፓሻ፣ የግል ሐኪሙ ለትቶ ሲሄድ አለቀሰ። ፓሻው፣ ሁልጊዜም የሐኪሙን ትዕዛዝ እንዳከበረ ነው። በዚህም ይደሰታል። ምንም እንኳን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ መከታተል የሚገባው ሕክምና መረር የሚል ቢሆንም የአሜሬች ሥራውን ለማከናወን ድጋሚ ስምምነት አድርጎ ነበር። ሁሴይን የሚባለው ፓሻ ዕድሜው ሃምሣ ዓመት ይሆናል። በነዚህ ዘመናት፣ በእኩል ከባድ መከራና መጠን ያለፈ የአስረሽ ምችው ሕይወት ውስጥ ዕድሜውን ያገባደደ ሰው ነው። ለርሱ ግብዕ ማለት ደስ

የማትልና ለአገዛዝ የማትመች አገር ነች። በወታደራዊ አንጃዎችና በአገረ ገዥዎች መካከል መቋጫ የሌለው ውስብስብ ችግር እንዳደከመው ነው። ግጼለሽ ሆኖ ሲሰነብት የአመፅ መጠን ያድጋል። ባላንጣዎቹ በብልጣብልጥነት ተግባር ሲያታክቱት ጥቂት ደርዘን የሚሆኑት አንገታቸው እንዲቀላ ይወስናል። ለፖንሴ መልካም መሥሪያ ቤት ምስጋና ይግባውና በነዚህ ሁለት ተቃራኒ ሃይሎች መካከል የሚወዛወዘው ችግር ተቀብሯል። በቅርቡ የነበሩት መንግሥታቶችና የሞት ቅጣቶችም ጥቂቶች ነበሩ። እንግዲህ ፖንሴ ለቅቆ ሲሄድ በድጋሜ ይከሰቱ ይሆናል። ይህን ሁሉ ዕድል ፈንታው የወሰነው ስለሆነ ፓሻው ለማስቆም ሃሣብ የለውም።

የጆን ባፕቲስት ደንበኞች የሆኑ ሃብታም ቱርኮችና አረቦች ገንዘብ አዋጥተው እየሰጡት በቶሎ እንዲመለስላቸው ይፀልያሉ። ድሆችን ለመርዳት አንድም ጊዜ አሻፈረኝ ብሎ አያውቅምና፤ የካይሮ ተራ ነዋሪዎችም በሐኪሙ መሄድ ተጨንቀዋል። አካለ ስንኩላን ለማኞችና ትሁት ቤተሰቦች፤ የሃኪሙን መልቀቅ ዜና በመስማታቸው ተሰብስበው፤ በጠባቦቹ መንገዶች ላይ በሚገኙ የዛፍ ጥላዎች ሥር የተኙትን እከካም ውሾች በመቀስቀስ በፍርሃቷ እየጮሁ ከፊት ለፊታቸው እንዲሮጡ በማድረግ አጀበውት ይጓዛሉ። ፊቶቻቸውን በዓይነርግብ የሸፈኑ ሴቶች፤ እንደነገሩ ገለጥ አድርገው ያያሉ። ጆን ባፕቲስት እንደሚመለስ ቃል ይገባላቸዋል። በመጨረሻ ላይ ግን፤ እግሮቹን አንቀው የያዙት ሰዎች እንዲለቅቁትና ፈጠን ብሎ መጓዝ እንዲችል ይገስፃቸዋል።

በዚህ ስሜታዊ ሁኔታ ብዙ ጠመዝማዛ ጐዳናዎችን በማለፍ መንገደኞቹ ከተማዋን አቋርጠው ወጡ። እስከምሽት ግዳግዳ ድረስ በፈረስ ላይ ተቀምጦ የነበረው ሜትር ዠረሚ ለቅፍለቱ በሙሉ ረጋ ያለ የደህና ሁኑ ሰላምታ ሰጠ። ዝግጅት ይደረግ በነበረበት በእያንዳንዱ ቀን ጆን ባፕቲስት፤ ጓደኛው ሃሣቡን ቀይሮ አብሮት ለመጓዝ ወስኖ እንደሆን ሲጠይቀው፤ ባዚያው በእያንዳንዱ ቀን ዠረሚ በበኩሉ ስለርሱ ከቶውንም እንዳያስብ ይነግረው ነበር። ሆነም ቀረም፤ ሁለቱም ሕይወትን ለተወሰነ ጊዜ እያታለሉ በጋራ እንዲሰሩ ያገናኛቸው ሲሆኑ፤ አሁን ደግሞ የየግላቸውን መንገድ ይጓዛሉ። ለዚህም ዕጣ ፈንታ ሲሉ፤ ሌላውን ይለቅቃሉ። ሜትር ዠረሚ የአሣማ ወርቾ በሚያከለው እጁ፤ የጆን ባፕቲስትን እጅ ለመጨረሻ ጊዜ ሲጨብጠው ያሣየው ስሜት አነስተኛ ነበር። ምናልባት ተጨባብጠው እያሉ፤



እጆቹን የወዘወዘበት ጊዜ ከተለመደው ይልቅ ረዘም ያለ ሲሆን ቢችልም፤ ሲለቅቀው ግን ቃል አልተነፈሰም።

አነስተኛው ጓድ ከተማዋን ለቅቆ የወጣው በሥጋጃ ሠሪዎች በር ነው። የሴፍን በፈርኦኖች የውሃ መውረጃ ቦይ ግንብ ሥር አድፍጦ አገኙት። ይህ ሲሆን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ይሆናል። ፀሐይዋ ቢጫ ቀለማኗ በድንጋዮች ላይ እያበራች ነው። ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ በተጓዙ ቁጥር የሰውነታቸው ጥላ ከበስተኋላቸው ባለው መሬት ላይ እየረዘመ፤ እየረዘመ ይሄዳል። የአባይን ወንዝ ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን በሆኑ ሰዎች ቀዛፊነት፤ በሁለት ትላልቅ ጀልባዎች ላይ ተሣፍረው ተሻገሩ። ግመሎቹ ፈርተው ከቃጫ የተሠራውን ለኮአቸውን ይጐትቱታል። ብርሃን እየሸሸ ሲሄድና የውሃው መልክም ቀለም መምሰል ሲጀምር፤ መንገደኞቹ ገና ወንዙ መሃል ናቸው። በዚያ ቦታ ሆነው፤ የካይሮን ግራጫ ግዝፈትና የኦቶማኖችን የፀሎት መጥሪያ ግንብ፤ በርቀት በወንዙ አንድ ጐን ሲመለከቱት፤ ከበስተኋላቸው ደግሞ በጥቁር አረንጓዴዎቹ የዘንባባ ዛፎች መጋረጃ ውስጥ፤ አስፈሪውን የፒራሚድ ቁልል ይመለከታሉ። በምሽት ጊዜ መንደር ደረሱ። በጠባቦቹና መግቢያ መውጫቸው በማይታወቁ የሸክላ ቤቶች ውስጥ የዘይት መብራቶች ቢጫ ብርሃናቸው ይፍማል።

የሃጂ አሊ የአጐት ልጅ፤ በግራር ዛፍ ጥላ ወደ ተዋበውና ወደ ተነጠፈው ግቢው እንዲገቡ ፈቀደላቸው። መኝታቸውንም በቤቱ ጣሪያ ላይ ባለው እርከን እንዲያደርጉም ጋበዛቸው። ካይሮ ከዚህ ቦታ በጣም ሩቅ ነው። ምሽቱም ድብልጥ ጨለማ፤ ቀዝቃዛና ጠፍ ጨረቃ ነበር። በርግጥ ጥሩ እንቅልፍ ወሰዳቸው።

በማግስቱ ከማለዳው ቀደም ብለው ለቀቁ። በወንዙ ዳርቻ እጅግ ሰፊ፤ እንደሃር ለስላሣና የሚያብረቀርቅ ሜዳ፤ እዚህም እዚያም ጥቁር አራት ማዕዘን እራፊ ጨርቅ የተለጠፈበት አረንጓዴ ልብስ መስሎ ተዘርግቷል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ለብቻ፤ ወይም ጥቂት ደስ የተሰኙ ቡድኖች በነዚህ አዲስ በታረሱ ማሣዎች ላይ በትጋት ይሰራሉ። ሌሎቹ መንገዱን ተከትለው በሬዎቻቸውን ከፊት ለፊት እየነዱ የእርሻ መሣሪያዎቻቸውን በትከሻዎቻቸው ላይ አድርገው ይጓዛሉ። አነስተኛው ቅፍለት፤ ይህን ረኻርም ለም መሬት አቋርጦ በፒራሚዶቹ ጥግ ወዳለው በረሃ ዘለቀ። የማለዳውን ሙቀትና ፀጥታ እየተዝናኑበት፤ የፒራሚዱን ግርጌ በዝግታ አለፉት። ጆን ባፕቲስት፤ ካይሮ ውስጥ በኖረባቸው ዓመታት እዚህ ቦታ አዘውትሮ የመጣው በሃሣብ ለመናወዝ ሲል ነው። የቺዮፕስን ፒራሚድ፤ ከንጋት በፊት ፀሐይ

ከተራሮች ጫፍ ላይ ስትላቀቅ ለማየት ሁለት ጊዜ ወጥቶታል። ስፊኒክስ /አካሉ የአንበሳ፣ ጭንቅላቱ የሰው/ የተባለውን ሲቃረቡ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ከቅፍለቱ ሹልክ ብሎ ተለይቶ በመሄድ፣ ይህን ታላቅና ማራኪ የአሸዋ ድንጋይ ሃውልት ዞረው። ከሐውልቱ አናት ላይ ሲደርስ ፊት ለፊቱ ቆሞ፣ አረቦች አቡ አል ሁልል፣ ወይም የሽብር አባት በማለት የሞት ያህል የሚፈሩት መሆናቸውን አስታወሰ። ጥላ ያጠላባቸውን የሃውልቱን ዓይኖች ተመልክቶ፦

«ዳግም እንደምንገናኝ ምዬ አረጋግጣለሁ»

ከዚህ በኋላ ቅፍለቱን ለመቀላቀል ጋለበ።

በሚቀጥለው ዕለት ከዋክብትን ጣሪያቸው አድርገው፣ በረሃው፣ ከታረሰው ለም መሬት ጋር በሚዋሰንበት ቦታ ላይ ስልምቻቸውን ሰብስበው እውላላ ሜዳ ላይ ሲንከባለሉ አደሩ። በሚቀጥሉት ሁለት ሣምንታት የአባይን ሸለቆ ይዘው ወደ ማንፋሉት መንደር ቀስ እያሉ ሲወጡ፣ የተለመደውን የቅፍለት የጉዞ እንቅስቃሴ ሥርዓት ተከተሉ። ማለዳ፣ ፀሐይ ስትወጣ ይነሣሉ። እሣት ላይ የፈላ በጣም ጣፋጭ ሻይ ይጠጣሉ። ጓዛቸውን በእንስሳቱ ላይ ይጭናሉ። ሠመመን ውስጥ ያሉ በሚመስል ሁኔታ ፀጥ ብለው ይጓዛሉ። የሚሠፍሩበትን ቦታ ይመርጣሉ። ጭነት ያራግፋሉ። እራት ይበላሉ፤ ይተኛሉ።

ከአሥራ አራት ቀናት የእግር ጉዞ በኋላ፣ ማንፋሉት ከተማ ደረሱ። ከተማዋ ትልቅ ብትሆንም ከጥርብ ድንጋይ የተሠሩት ቤቶችዋ በጣም አጫጭሮች ስለሆኑና ከመሬት በላይ ከፍ ስለማይሉ፣ የበረሃው ምድር አካል ይመስላሉ። ማንፋሉት ከተማ ከገቡ በኋላ ግን፣ ተስፋ አድርገው የሚፈልጉትን ምቾች ያገኛሉ። የቤቱን የላይኛውን አካል ለተጓዦች ከሚያከራይ አንድ አይሁዳዊ ነጋዴ ላይ ማረፊያ የሚሆናቸውን ቤት ተከራዩ።

አብረውት በመቀላቀል እስከ ኑቢያ ድረስ ሊጓዙ የሚችሉትን ትልቅ ቅፍለት ማግኘት የሚችሉት እዚህ ነው። ትልቁ ቅፍለት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚንቀሣቀስ ሃጂ አሊ ያውቃል። ነገር ግን በበረሃ ውስጥ «በቅርብ» የሚለው ቃል ከብዙ ጊዜ ከሚለው አገላለፅ የሚያንሰው በትንሹ ነው። ቀናት አለፉ። ከዛሬ ነገ የሚለው ጥበቃቸውም በዚህ ሙቀቱ በሚያቃጥል ሐሩር መንደር በዝግታ ቀጠለ።



ከፊት ለፊቱ ሊገጥመው ከሚችለው አደጋ ይልቅ፣ በዚህ ረዥሙ ጉዞ ላይ የሚያገኛቸው ተንዳኖቹ ጉዳይ፣ ጆን ባፕቲስትን ይበልጥ አሣሰበው። ሃጂ አሊ፣ እንደግመሉቹ ሁሉ ጭውውት ያበዛል። በአንዲት ትንሽ ሹል ስንጥር እንጨት ጥቁሩን ጥርሱን ሲጐረጉር ሰዓታት ይፈጃል። አንዲት ትንሽ የእህል ትራፊ ጐርጉሮ ማውጣት ከቻለ አስደንጋጭ የመምጠጥ ድምፅ ያሰማል። ፖንሴ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ሁሉ፣ ይህ የቅፍለት መሪ፣ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ይገለፃል፣ እያለ ይመልሣል። ስለጉዞው፣ ስለአበሻ አገር ወይም ስለንጉሡ ነገስቱ አንዳችም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልሆን አለ። የነጋዴው ሁኔታ፣ ጆን ባፕቲስትን ሐኪም ነው ብሎ ባለማመኑ እንደሆነ አረጋገጠ። ፖንሴን ለመውሰድ የተስማማው ቆንስሉ አጥብቆ ግፊት ስላደረገበትና መስማማቱም ጥሩ ምክንያት ስላለው ነው። ይህም ሆኖ ነጋዴው ፖንሴን የሚፈትንበትን አጋጣሚ እየጠበቀ ይመስላል።

ጆን ባፕቲስት፣ ከአባ ብሬቬደንት ጋር ያላቸው ግቡቡነት በመጠኑም ቢሆን አስደሣች እንደሆን አወቀ። በሃጂ አሊ ፊት የሚሰጣቸው ትዕዛዞች አጫጭሮች ናቸው። ይህንንም ቢሆን ዐይኖቹን ሣይሰብራቸው ፊዕሞ አያደርገውም። ማንፋሉት ከተማ ውስጥ በስነቡቱባቸውና ብቻቸውን መሆን ሲገደዱ፣ቄሱ ዕፅዋትን እንዲያዩ በማለት ወደ ባላገር ይዟቸው ይወጣል። አንዳንድ ጊዜ በድፍረት ወደ አባይና ወደ ቆላው የደለል ምድር በመሄድ አዳዲስ የሰንበሌጥ ዝርያዎች፣ በየቦዩ ውስጥ ንፁህ የውሃ አረንጓዴዎችን ያገኛሉ። አንዳንድ ጊዜም ወደ በረሃው በመዝለቅ ውሃ የሞላቸው ጣፋጭ ተክሎችን ይሰበስባሉ። እንዲሁም ጊንጦች ርስ በርሳቸው ሲፋለሙ ይመከለታሉ። አባ ዴ ብሬቬደንት፣ በሣይንስ መስክ ጠንካራ መሠረት እንዳላቸው ወዲያውኑ መገለፅ ጀመረ። ጆን ባፕቲስት፣ ከአንድ ቱርካዊ ታካሚ የተሰጠውን ከነሃስ የተሠራ ትንሽ የእቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ በጭነቱ ውስጥ ሸጉጦ አስቀምጧል። እንዴት መጠቀም እንደሚችል ጄስዊቱ አስተምረውታል። ወዲያውኑ፣ በይቅርታ አጠያየቅ ዓይነት ተግባራዊውን ሠርቶ ማሣየት የሥነ ከዋክብት ጭውውታቸውን በምሁራዊ አገላለፅ ጨረሱት። ርስ በርሣቸው የተዋወቁ ሲመስላቸው፣ ሁልጊዜም እንደሚጠቀሙበት፣ እጅግ በጣም ትህትና በዞዘበት ሁኔታቸው፦

«ገና ወጣት ሆኜ፣ ከረዥሙ ዓመታት በፊት፣ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ የሚያደርግ አንድ መሣሪያ ፈልስፌ ነበር። አትሣቅ! ነገሩ ትልቅ አልነበረም። ነገር ግን የተፈጥሮ ሣይንስ

ፈላስፎችን ሲበዛ አስደንቋቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ የዚህን የመማሪያ ዓይነት ከእንጨትና ከብረታብረት ሠርቼ ነበር»

ጆን ባፕቲስት የመንጓት ድምፅ አሰማና ዝርዝሩን እንዲያወጉት ገፋፋቸው።

«ከረዥም ጊዜ በፊት ይመስለኛል። ደህና አድርጌ እንኳ አላስታውሰውም» ሲሉ ቄሱ መለሱ። በመቀጠልም እንደማፈር እሉና።«የማይንስ አካዳሚ ጋዜጣ ዕቅዶቹን በማተም ክብር እንዳገኝ አድርጉኛል»

እኒህ ሃዘንና ትካዜ አድቅቋቸው፣ የሥነ-ፈለክ ጥናት ከንቱ ሥራ ነው ብለው ከሚያስቡ የጀስዊት ቄስ ይልቅ፣ ሌላ የተሻለ የጉዞ ጓደኛ ሊታሰብ ይችል ነበር። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ላይ፣ ያለውን መጠቀም ይመረጣል። ያስወዳጅ መኖር የማይችለው ጆን ባፕቲስት፣ ለአባ ብሬቬደንት የራሱን ታሪክ ዘረገፈላቸው። ደንገዝገዝ ሲል የልብ ጓደኞሞች ሆነው፣ ሽሚዞቻቸው በላብ ረጥበው፣ ያገኙትን ዕፀዋትና ነፍሳት በቅርጫት ሞልተው ጉን ለጉን ሆነው ሲመለሱ ይታያሉ። በአንደኛው ትከሻቸው ላይ ባዶ የፍየል ቆዳ ስልቻ አንጠልጥለዋል። ይህ፣ ቀትር ላይ ሁለቱም የሚጠጡትን ውሃ የሚይዙበት ነው። ተመልሰው ሲመጡና ኰማዋ በዓይን ርቀት ላይ ስትሆን የጌታና የሎሌ ሚናቸውን ይጀምራሉ።

ጆን ባፕቲስት፣ የአባ ብሬቬደንትን የአዕምሮ ብስለትና ችሎታ አወቀ። እኒህ አደጋ የማይችሉ፣ ጨዋ፣ የጤናቸው ሁኔታም ደካማ የሆኑ ሰው፣ ወደ ጉድጓድ ውሃው እየተቻኮሉ የሚሄዱና የሚመለሱ፣ በባልዲው ውሃ ክብደት የተነሣ ቁና ቁና የሚተነፍሱ፣ እንደትል ለሚመለከታቸው ለሃጂ አሊ፣ ወገባቸው እስኪንቋቋ የሚያጕነብሱትን ሲመለከት ይበልጥ ማፈር ጀመረ። ይህን ዓይነት ውርደት እንዴት እንደሚቀበሉም ይገርመዋል። አዕምሮውን ለዘመናት በነፃነት ሲጠቀምበት ለኖረው ሰው ይህ ድርጊታቸው ይበልጥ ያሣፍራል።

ይደርሣል የተባለው ትልቁ ቅፍለት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። የጕዞውን ምክንያት ጨርሶ ሊዘነጋው ስለማይችል፣ ፖንሴ ይበልጥ መስጋት ጀመረ። ይህ ደግሞ እጅግ መጥፎ ውጤት ይኖረዋል።



በጭራሽ ሳይታሰብ በድንገት የተጣለባት እምነት፣ ተግባርና ሃላፊነት፣ አሊስ ዱ ማይሌን እጅግ በጣም አስደነቃት። አባቷ ሁሉንም ነገር በዝርዝር ነገራት። እንዴት ሊሆን ይችላል በሚል ለረዥም ጊዜ ልትረዳው ሳትችል ብትቆይም፣ የኋላ ኋላ በደስታ ተሞላች። በማግስቱ፣ የማለዳውን ጊዜ በሙሉ፣ የእጅ መሣሪያዎችዋ የሆኑትን ማንኪላዎችን በማፀዳዳት በየመልካቸው ስትደረድራቸው ቆየች። አንድ ተልዕኮ ይጠብቃታል። ራሷን ችላ አንዳች ነገር እንድታከናውን፣ አንድ ሰው ሃላፊነት ሲሰጣት በምድር ላይ ይህ የመጀመሪያዋ ነው። ፀሎትዋ ሁሉ ተሰምቶላታል። በጠባቡ ክፍሉ ውስጥ እያንዳንዷን እርምጃ ደጋግሞ እንደተመላለሰባት እስረኛ ከምታውቀው ከዚህ የጠላቻችዋ ቤት፣ በመጨረሻው ላይ ልትወጣ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቦታው በማንም ያልተያዘ ስለሆነ የመምራት ዕድልም ይኖራታል። ቦታው እንደ ደን፣ ሥርዓት ባጣ ሁኔታ ውስብስብ ያለ መሆኑን አባቷ ገልፆላታል። ይህ ገለፃ የማወቅ ፍላጎትዋን ይበልጥ ነፍስ ዘራበት። ከዚህ ደስታዋ ጋር በርግጥ ፍርሃትም ተሰምቷታል። ተልዕኮዋን በአሸናፊነት ትወጣዋለች? ጠላትነት ካላቸው፣ አጠቃላይ ካልሆኑና ራሳቸውን ለመግደል ዝግጁ ከሚሆኑት ዕፀዋት በስተቀር ከሌሎች ዕቃዎችና ሕይወት ያላቸው ነገሮች ጋር አትፋጠጥም ይሆን? ሊያጋጥማት የሚችለው አደጋ ብዙ እንደሚሆን ስጋታ ብትሸበርም፣ በመጨረሻ ግን ልበሙሉነት ተሰማት። ከዚህም ባሻገር ቦታው ሙሉ በሙሉ እንግዳና ባዕድ አይሆንባትም። ቤቱ የጆን ባፕቲስት ፖንሴ ነው። እርሱ በኖረበት ግቢ ውስጥ ልትገባ ነው። በዝምታውና በመሄዱ ቅር ብትሰኝም፣ ትውስታዋ እውነት ሆኖ ከቤቱ ባለቤት ጋር በነበረችበት ጊዜ ይሰማት እንደነበረው፣ አሁንም በተመሣሣይ ስሜት ውስጥ እንደምትሆን ገመተች።

አባ ጋቦሬ፣ በዚህ ሥራ ውስጥ ሣይደሰቱ ገቡበት። ቅፍለቱ ካይሮን በለቀቀ ማግስት፣ አሊስን ሄደው አመጧት። ዕፀዋቱ ከዚህ በላይ ጥንቃቄ ሣይደረግላቸው ሊተው አይቻልም። ኮፈኗ ወደ ኋላ የምትተጣጠፈዋን መኪናውን፣ ቆንሲሉ ፈቀደላቸው። ሁለቱም፣ ለጥቂት ደቂቃዎች ጉዞ ወጡ። በዚያኑ ማለዳ ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ሴት ልጁ ከዚህ በኋላ ከአባ ጋቦሬ ጋር በመሆን በመድሃኒት ቀማሚው ሰው አሮጌ ቤት ውስጥ ዕፀዋትና ተክሎችን እንደምትንከባከብ፣ እንግዶቹና ጉብኚዎቻቸው ሁሉ እንዲያውቁለት አደረገ። ጉዳዩ ይፋ እንዲሆንና እንከን የሌለው አሠራር ሆኖ እንዲታይ ፈለገ። ፖንሴ ቤት መግቢያ በር ላይ ሲደርሱ ጀስዊቱ፣

መኪናው እንዲቆም አደረጉ። ቁልፍ በእጃቸው ስላለ እውነታውን፣ ምስጢር ማድረግ አልፈለጉም። ወደ መጀመሪያው ክፍል የሚያመራውን በር ሲከፍቱ፣ ሜትር ዝርሚ፣ ደህንነቱ የሚጠበቅበት የነበረውን የብቸኝነት ክፍሉን አገኙ። ፕሮቴስታንቱ፣ ክፍሉን ለቅቀ ከመሄዱ በፊት የእልጋ ልብሶቹን አንስቷቸዋል። በየቦታው የተዝረከረኩትን ማህኖችም ወደ አንድ ጐን ሰብስቧቸዋል። በተቻለው መጠን ክፍሉን አፅድቶታል። በክፍሉ መሃል በሚገኝ ጠረጴዛ ላይ፣ አድራሻው ለአባ ጋቦሪ የሆነ ደብዳቤ አገኙ። በክፍሉ ውስጥ ያለው ብርሃን፣ ለደካማው አይናቸው በጣም ደብዛዛ ስለሆነባቸው፣ ደብዳቤውን ልጅቱ እንድታነብብላቸው ጠየቋት። ጀስዊቱ፣ በሕይወት ዘመናቸው አንድ ጊዜ ወጣት እንደነበሩ፣ ዛሬ ግን አይደሉምና ወደ ሁለተኛው ፎቅ ለመሄድ ደረጃውን በመውጣት ራሣቸውን እንዳያደክሙ ሃሣብ የሚሰጣቸው ደብዳቤ ነው። ለርሣቸው የሚሆንና ሲፈልጉ ጋደም ሊሉበት የሚችሉበት ረዥም ሶፋ፣ እዚሁ ክፍል ውስጥ የተዘጋጀላቸው መሆኑን ሁለቱም በአንድ ጥግ በኩል ተመለከቱ። ጥንቃቄና ብልህነት በሚታይበት መልክ፣ ህመምተኛው ቄስ የሚፈወሱበትን፣ በተለይ ያዘጋጁትና መድሃኒት የተሞላበት፣ ከሥሩ የቧንቧ መክፈቻና መዝጊያ የተገጠመለት ትልቅ ደምበጃን አሉ። በላይኛው ፎቅ ላይ ለዕፅዋቱ የሚያስፈልጓቸው ጥንቃቄዎችን በተመለከቱ መመሪያዎች የተመዘገቡባቸው ሁለት ትላልቅ መዝገቦችን ማዳሞዜል ታገኛቸዋለች።

ቄሱ፣ መድሃኒቱን ቀመስ አድርገው ፊታቸውን ከፊገግታ ጋር አኮሣተሩ።

«ክምጣጣ ነው እንዴ?» ስትል አሊስ ጠየቀች

«ልጄ ሆይ፣ መድሃኒት ስለሆነ መቀበል ያለብንም እንደመድሃኒትነቱ ነው»

መድሃኒቱ በሐኪም የታዘዘ ባይሆን ኖሮ፣ አባ ጋቦሪ፣ መጠጡ፣ አልኮሆል ነው ብለው ይምሉ ነበር። አንድ ሙሉ ብርጭቋቸውን ከጨለጡ በኋላ በረዥሙ ሶፋ ላይ ጋደም አሉና ተማሪያቸው፣ በላይኛው ፎቅ ላይ ሥራዋን በትጋት እንድትቀጥል መመሪያ ሰጧት።

ከጥቂት ቀናት በፊት፣ አባቷ እንዳደረገው፣ ደረጃዎቹን ወጥታ ስትጨርስ፣ ጥቅጥቅ ያለ የተክሎች ክምችት ያለበትንና የማይታሰበውን የዕፅዋት ማሣደጊያ ቤት አገኘች። ተክሎቹ፣ እርጥበት አዘሉን ትንፋሻቸውን በለሲት ተንፍሰዋል። በክፍሉ ውስጥ ያለው አየር፣ ሞቃት



ሆኖ ርጥበት ያለው ሲሆን፣ የእንጨት ብስባሽና የደን አበባዎች ሽታ አለው። በጣሪያው ላይ በበቀሉት ዛፎች ውስጥ ያረፉት ወፎች፣ ፂው ፂው የሚለውን ድምፃቸውን ያሰማሉ።

ወጣቷ ልጃገረድ፣ በየእንጨቱ ቅርንጫፍ ላይ ጣቶችዋን በዝግታ እያሣረፈች፣ በማሀሮች ውስጥ በበቀሉት ዕፅዋት መካከል ባሉት ጠባብ መተላለፊያዎች በዝግታ ተራመደች። በአንድ ጠረጴዛ አጠገብ ያርሣ ከበርፖማዎቹ በአንዱ ላይ ተቀመጠች። ቦታው በርግጥም የተለየ፣ በዙሪያዋ ያለ መስሏት ከሚታሰባትና ከፈጠረው ወጣት ሰው ባህርይና ሁኔታ ጋር የማይመሣሰል ነው። ጣፋጭ በሆነ የቀን ህልም ውስጥ በሰመመን ስትንዝ፣ ጠረጴዛው ላይ ሁለት ወፍራም መዝገቦችን ተመልክታ ነቃች። መዝገቦቹ ተግባሯን አስታወሷት። የመጀመያውን ቅፅ ገለፀችው። ከሃያ ዓመታት በፊት ሆላንድ ውስጥ የታተመና በዕፅዋት አበቃቀል ጥናት ላይ የተደረገ ጥብቅ ስምምነት ያለበት መፅሃፍ ነው። የመፅሃፉ ውፍረት ሃሞቷን አፈሰሰው። ሙሉ በሙሉ አንብባ እስክትተረጉመው ድረስ ዕፅዋቱ ሞተው ይረግፋሉ። ይሁን እንጂ የመጀመሪያዎቹን ገፆች ገለጥ፣ ገለጥ ስታደርጋቸው፣ የገፅ ማስታወሻ ምልክት የመሰለች ቀራጭ ወረቀት በጠርዝ በኩል ታየቻት። በዚያች ወረቀት ላይ የተፃፈው እንዲህ ይላል። «ለትልልቆቹ ተክሎች፣ በየቀኑ አንዳንድ ባልዲ ውሃ ስጫቸው። ለትንንሾቹ አንዳንድ ብርጭቆና ግንዶቻቸው ወይም ቅጠሎቻቸው ብዙ ውሃ ለሚያከማቹት ሁሉ በሣምንት ግማሽ ብርጭቆ አጠጫቸው። ቀን ቀን መስኮቶቹን ሁሉ ክፈቻቸው። ወደ ቤት ስትመለሺ ግን ዝጊያቸው። ለቀሪዎቹ ዕፅዋት፣ አንቺ ጥሩ ነው የምትይውን ፈፅሚላቸው። ከሁሉም በላይ ግን ልክ ለኔ እንደምታወሪኝ ሁሉ እፅዋቱን አነጋግሪያቸው . . . ጆን ባፕቲስት»

አንብባ ስትጨርስ፣ አሊስ ሣቋን ለቀቀችው። ይሁን እንጂ፣ የቄሱን ስሜት እንዳትሰብ ለግታ አፏን በእጇቿ ዘጋችው። ከታችኛው ፎቅ የሚሰማው አንድ አይነት አተነፋፈስ ብቻ ነው። ይህ ማለት፣ አባ ጋቦሪ ተኝተዋል ማለት ነው። ትንሿን ወረቀት አጣጥፋ መደርደሪያው ላይ በሚገኙ ሁለት መፅሀፍት መካከል ደበቀቻቸውና ከፊትዋ የተደቀነውን፣ ቀላሉንና የሚስማማትን ሥራ ከግቡ ለማድረስ በደስታ ጀመረች።

# 2

የመልዕክተኛው ቡድን ከሄደ ከሁለት ቀን በኋላ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እስከ ቆንሲላው ጽህፈት ቤት ድረስ የመጣ እንግዳ ተቀበለ። ሰውዬው የተለመደ ዓይነት መልክ የሌለው ሲሆን፣ ወንድም ፖስኳል እባላለሁ ብሎ ራሱን አስተዋወቀ።

ወደ ቢሮው ሲገባና ሰውዬውን ሲመለከተው፣ ቆንሲሉ ተንቀጠቀጠ። ሰውዬው፣ ያለጥርጥር የካፑቺን መነኩሴ ነው። በወገቡ ላይ የታጠቀው ገመድና ጀርባው ላይ የተንጠለጠለው ቆብ፣ የካፑቺን መነኩሴነቱን ማያሳስቱ ይናገሩቢታል። በሰፊው ካባው ውስጥ በመሆኑ፣ ቅርፁን መናገር ቢያቅትም፣ በተከሻው ስፋት፣ በቁመቱ ርዝመትና እጁ ላይ የሚታየው ቅርፊት የመሰለ ቆዳው፣ ሰውዬው ለሥራ እንዲንቀሣቀስ የታዘዘ ዛፍ ቆራጭ ያስመስሉታል። በአስፈሪው ቁመናው፣ አራት ማዕዘን በሆነው የራስ ቅሉ ቅርፅ ፣ በሚጠቀለለው ጥቁር ጺሙና የሚያንፀባርቁ ትናንሽ አይኖቹ የተሟላ ሰው ነው። የንግግር ቅላፄው ጫን ያለ የኢጣሊያንኛ ዘዬ ነው። የ«ረ» ን ፊደል ድምፅ ሲያወጣት፣ በአፉ ውስጥ እያንከባለላት ነው። የሱካንዳ ነጋዴ፣ ጮማና ቀይ ሥጋን ለመለየት ሲል በቢላዋው እንደሚቆራርጥና እንደሚሰነጣጥቅ ቃላቱንም በጭካኔ ያወጣቸዋል።

«የማህበረሰባችን መሪ ነኝ» ሲል ለቆንሲሉ ዝቅ ብሎ እጅ እየነሣ ተናገረ።

እንግዳው መነኩሴ፣ ወደ ኢትዮጵያ ንጉስ የተላከውን ኤምባሲ መርቶ እንዲሄድ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ የሾመውን ሰው ለማግኘት እንደሚፈልግ ገለፀ።

ቆንሲሉ፣ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው አንዳችም ነገር እንደሌለ ለመካድ ሞከረ። መነኩሴው ግን፣ ካባው ውስጥ እጁን ሰድዶ አንድ ወረቀት አወጣና ቆንሲሉ ለፖንሴ የሰጠውን፣ የፈረንሣይ ግዛት ዘውድ ማህተም ያረፈበትን የምስጢር ደብዳቤ አንድ አንቀፅ አነበበ። ይህ ውይይት በሚካሄድበት ጊዜ በቦታው የነበረው ሙሴ ማቼ፣ የአለቃው ፊት እንደሞት ሲጠቁር ተመልክቶ፣ ቆንሲሉ ሀሊናውን ሊስት ነው ብሎ አሰበ። ይሁን እንጂ፣ ቆንሲሉ ራሱን ተቆጣጥሮ መነኩሴው ይህን መረጃ ከየት እንዳገኘው ለመጠየቅ ብርታት አገኘ።



«እርስዎ ነዎት ቆንሲል፣ እርስዎ ነዎት የላኩልን» አለ ካፑቺኑ ያለቁ ጥርሶቹን በፈገግታ እያሣየ

«እንዲህ ያለ ነገር ጨርሶ ልከላችሁ አላውቅም»

«ፀሐፊዎ ይመስለኛል። ትርጉሙ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ለአንድ ወንድማችን አመጣው። የሰም? ለወንድም ፍራንሲስ ነው። ያውቁት ይሆናል?»

ቆንሲሉ፣ ወደ ማቼ ዞር አለና በእይታው ገላመጠው። ሊመታው ቢችል ኖሮ፣ ያለማመንታት ያደርገው ነበር። ያጠፋው ጥፋት ይቅርታም የማያሰጥ ነው። ይህን ጥፋተኛ ነፍን ሙሉ በሙሉ ሊደመስስለት የሚችል ቅጣት ስለመኖሩም ተጠራጠረ። ቆንሲሉ የደብዳቤው ትርጉም እንዲረጋገጥለት የፈለገው በቋንቋ ችሎታቸው ዕውቅ ናቸው በሚባሉትና ከከተማው በስተኋላ ባለው ቄራ አጠገብ በሚኖሩት የሜሮናይት እምነት ተከታይ መነኩሴ፣ በወንድም ፍራንሲስ ነበር፣ ነገር ግን ይህ ብቃት የሌለው፣ ይህ ጅል ፀሐፊ፣ ጉዳት ለማያስከትለው ሶሪያዊ መነኩሴ ሣይሆን ሳልተባለው፣ ያውም ለካፑቺን መነኩሴ ነው ደብዳቤውን ያሣየው።

ደስ ባይለውም፣ በመጨረሻው ላይ ሙሴ ማቼ በበኩሉ አመነ። በዲፕሎማሲያዊ ምስጢር አጠባበቁ ረገድም፣ በመሠረታዊነት ያሰበውን ጉዳይ ገለፀ። ቆንሲሉ፣ ለንጉሡ የሚፈውን አፊሴል ደብዳቤ፣ ማይወድ በግድ ከንዞው እንዲቀሩ ሳያረጋቸው ለነዚሁ ካፑቺኖች መግለጽ ይገባዋል። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተከናወነውን አሣፋሪ እውነታ ተረዳ።

በዚህ መካከል ሙሴ ማይሌ፣ አዕምሮው ተረጋጋ። እስመግባቱን ለማስወገድም ቢሆን ወደፊት ጊዜ ይኖራል። አሁን ግን፣ ይህ ባለጌ መነኩሴ የያዘውን ወረቀት እንዲህ አጠንክሮ ወጥሮ የሚከራከር ምን ቢፈልግ ይሆን? አውጥቶና አውርዶ ሲያበቃ፣ የፈረንሣይ ንጉሥ ነጋሥት፣ ለአበሻው ንጉሥ በፃፉት ደብዳቤ ላይ ጀስዊቶችን አለመጥቀሣቸውን አስታወሰ ገለፀ።

«ይህ ኤምባሲ የተባለው ጉዳይ በጣም ግሩም ሃሣብ ነው» ሲሉ ወንድም ፖስኳል ቀጠሉ። «የመጣሁት ሊረዳችሁ የሚችል ሃሣብ ይዤ ነው። የእምነታችን ተከታዮች የሆኑት ወንድሞች፣ በላይኛው ግብፅና ኑቢያም ውስጥ አሉን። ከዚህ በኋላ፣ መነኩሴው፣ ኢትዮጵያን በሚመለከት የርሣቸው የሃይማኖት ማህበር በቀጥታ ምን እንደሚመለከተው ወደ ማስረዳቱ

ገቡ:: ጳጳሱ ራሣቸው፣ ካፑቺኖዎች፣ ኢትዮጵያን እንዲለውጡና እንዲያሣምኑ፣ ቅዱስ የሣላፊነት ተልዕኮ ሰጥተዋቸዋል:: በርግጥ ከሁለት ሣምንት ከማይበልጥ ጊዜ አካባቢ፣ ቅዱስ አባታችን፣ የፍራንሲስካን ሃይማኖት ማህበር የርሣቸው መልዕክተኛ በመሆን ወደ አቢሲኒያ ደብዳቤ ይዘው እንዲሄዱ በይፋ ሰይመዋቸዋል:: በዚህም፣ የጳጳሱን የኢኖሴንት 12ኛን፣ ለአብነት የሚያበቃ አስመሣይነት፣ ቆንሲሉ ተገነዘቡ:: በፈረንሣይ ንጉስ ነገስት ለሚደረገው የጀስዊት ሚሲዮናዊ ጓድ ቡራኬያቸውን ከሰጡ በኋላ፣ በዚያኑ ጊዜ በሎሌያዊ ማጭበርበር ከጀስዊቶች ጋር በቀጥታ ፉክክር ውስጥ ያሉትን የሃይማኖት ማህበር መሪ፣ የራሣቸውን የጳጳስ መልዕክተኛ በማለት ሰይመዋቸዋል:: በሌላ አነጋገር፣ ጳጳሱ፣ በመካከላቸው ፍቅር የሌላቸውን ሁለት የሰባኪያን ጓዶች በአንድ አቅጣጫ ልከዋል ማለት ነው::

ይሁን እንጂ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ጊዜ የለም:: ቆንሲሉ፣ ከዚህ በኋላ ሊከተል የሚችለው አደጋ ስለተሰማው ወዲያውኑ ልዩ አፀፋዊ ምላሽ ሰጠ::

«በሰማይ ያለኸው ሃያሉ አምላኬ! ወንድም ፓስኳል፣ ምን ዓይነት አለመታደል ነው! በእርግጥ እቅዳችንን በፀሃፊዬ በኩል አስታውቄዎት ነበር:: ነገር ግን ወንድም ፍራንሲስ ምንም ዓይነት መልስ ሣይሰጡን ሲቀሩ፣ በበኩላችንም ስለኤምባሲያችን እውቀና እንጂ ሌላ ምንም ነገር የለም በሚል እንደቀላል ነገር ወሰድነው:: በዚህ ኤምባሲ ውስጥ መሣተፍ የምትፈልጉ መሆናችሁን የሚያመላክት አንዳችም ነገር አልነበረም:: ሰዎቹ ከሄዱ ሦስት ቀን አለፋቸው:: ከዚህ በኋላ እነርሱ ላይ ልንደርስ የምንችልበት አንዳችም ዘዴ የለንም::»

«አዎን፣ አለመታደል ነው» አሉ ወንድም ፓስኳል፣ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ:: «በጥቂት ቀናት ውስጥ ሁለት ዕድሎች አመለጡን:: ከአንድ አረባዊ ነጋዴ ጋር አብረው ሊጓዙ ዝግጁ የነበሩ ሁለት ወንድሞች ነበሩን:: ነጋዴው ወደዚህ የመጣው፣ ለአበሻው ንጉሥ ሐኪሞችን ሊወስድለት በማለት ነበር:: አሁን ግን ደብዛው ጠፍቷል::»

«እንዴት ሊሆን ይችላል?» ሙሴ ዱ ማይሌ፣ በሰውነቱ ቀዳዳዎች ሁሉ ላብ እያመነጨ በመደነቅ ጠየቃቸው:: «በእርግጥ ቅሬታዎ ይገባኛል» ቆንሲሉ የማፅናናት ቃላቱን ቀጠለ:: የካፑቺኑ መነኩሴ፣የሚናገሩት ጠፍቷቸው፣ እንደነገሩ ጉንበስ በማለት ሠላምታ ሰጥተው፣ ወጥተው ሄዱ::



ሕይወት እንደሆነች በአጋጣሚዎች የተሞላች መሆንዋን ለመቀበል፣ ወንድም ፓስኳል ዝግጁ ነበሩ:: ከዚህም ባሻገር፣ በያንዳንዱ የመጨረሻ ሁኔታ በሌሎች ሰዎች የግል ህይወት ጣልቃ በመግባት ማግዘን ተገቢ አለመሆኑን የምሥራቅውያንን ባህል ስለሚገነዘቡ ያውቁታል:: ይሁንና የመልዕክተኞች ቡድን፣ እጅግ በጥድፊያ ከከተማው የለቀቀ ይመስላል:: ቆንሲሉም፣ በመልክም ታማኝነት ተግባሩን በሚወጣው ሰው ሳቢያ በጣም የታወከና የተረበሸ ይመስላል:: የካፑቺኑ መነኩሴ ምርመራቸውን ለመቀጠል ወደ አረቦች መኖሪያ አቀኑ::

መነኩሴው እንደወጡ፣ ሙሴ ማያሌ ወረቀቱን በጫጭቆ ጣለው:: ፊቱ በላብ ተበምቆ፣ ሙሴ ማጅ ላይ ዞረበት:: ነገር ግን በቁሱ ላይ ሊፈፅመው የማይችለውን እልሁን ሊወጣበት ከመነሳቱ በፊት፣ ፀሐፊው፣ ተሰብሮ እንደሚወድቅ የሰውዝ ሽፋን ዓይነት፣ በግንቃው ወለል ላይ በጉልበቱ ወድቆ ተነበረ:: ቆንሲሉን፣ በሕይወት ዘመኑ እንዲህ ወድቆ ይቅርታውን የለመነው ሰው የለም:: ሙሴ ዱ ማይሌ፣ የፀሐፊውን የሁለት ወር ደመወዙን ለመያዝ ወሰነ::

***

በመጨረሻ፣ ትልቁ ቅፍለት ማንፋሉት ደረሰ:: ገና ሰማይና መሬት ሣይለቀቅ፣ ከተማዋ በእንቅልፍ ላይ እያለች ከትት አለ:: ባለፈው ምሽት፣ ትልቁ የገበያ ቦታ፣ ግራጫ አሸዋ የተዘራበትና ጥቂት አጥንታቸው ያገጠጠ ውሾች የሚልከሰከሱበት አና መሬት ነበር:: ዛሬ ማለዳ ደግሞ፣ ከዳር እስከዳር በጠባቂዎቻቸው ሥር ባሉ ግመሎች፣ በገመድ ተቀርቅበው በተሰሩ ጭነቶችና በመጠለያነት እንዲያገለግሉ ሲባል በእንጨት አጠናዎች ላይ በተወጠሩ የሐር ጣቃዎች ምድሩ ተሸፍኗል:: ሰማያዊ የወታደር ሸኬት የለበሱ፣ በጭንቅላታቸው ላይ ጥምጣም ያሰሩና የጥምጣሙም ጫፍ እንደ አንገት ልብስ በትከሻቸው ላይ የተለቀቀ ሰዎች፣ እጅግ ብለው እየተንጫጉ ከቦታ ቦታ ይንቀሣቀሣሉ:: የሻይ ማንቆርቆሪያዎች በእሣቱ ላይ ተጥደዋል:: የበግ ጠቦቶች ሥጋ ከሚጠበስበት ምድጃ፣ በቅባቱ ሳቢያ ሰማያዊ የሚመስል ወፍራም ጭስ፣ በሰው ጭንቅላት ልክ ቡልል ይላል::

ሃሰን አል ቢልቤሲ የሚባለውን የዚህን ትልቅ ቅፍለት መሪ፣ ሃጂ አሊ በሚገባ ያውቀዋል:: በዚህ ጠንካራ ግንኙነታቸው ሳቢያም አንዳንድ ጉዳዮችን በዩሉ ለመፈፀም

ይችላል። ስለሆነም አምስቱን በቅሎዎቹን በሁለት ግመሎች ለወጠ። የዚህ ምክንያቱ አንደኛ የግመሎቹ ዋጋ ከካይሮ ይልቅ እዚህ በመጠኑ ስለሚቀንስ፣ ሁለተኛም በቅርቡ ለሚያቋርጧቸው በረሃዎችም ግመሎቹ የተሻሉ ምርጫዎች ስለሆኑ ነው። ይሁን እንጂ፣ እንዳለመታደል ሆኖ ሁለቱ ግመሎች በአምስቱ በቅሎዎች ላይ ያለውን ጭነት ለመሸከም የሚችሉ አይደሉም። ይህን ችግር ለመቋጨት የሚያስችለውን አማራጭ ሃጂ አሊ በአስቀያሚው ፊንግታው አስረዳቸው። ዮሴፍ፣ የሚጓዝበት የጋማ ከብት ከእንግዲህ አይኖረውም። በበረሃው አሸዋ ላይ የመጓዝ ልምድ እንዳላቸው እንደነቢያውያኑ፣ እርሱም ከጭነት ከብቶቹ ጋር በእግሩ መራመድ ይኖርበታል።

አባ ብሬቬደንት፣ ይህን እጅግ የከፋ ውርደት በትህትና ተቀበሉት። እንዲያውም፣ የጉዞ ጓደኞቻው አንድም ዓይነት ተቃውሞ እንዳያነሣና ጥርጣሬ እንዳይፈጠር፣ ጥንቃቄ ማስፈለጉን በማስገንዘብ እሺ እንዲል አደረጉት። የጂስዊቱ ቄስ፣ ገደብ የለሽ ሽንፈትን ለመቀበል ፈቃደኛና ደስተኛ መሆናቸውን አስተዋለ። በዚህም የተነሣ፣ ሰውዬው ቀም ነገረኛ ናቸው በሚል ለርሣቸው በመጀመሪያ የነበረው የርህራሄ ስሜቱ ተነነበት። ካህኑ ትጋታቸውን በማስመሰልና በትህትና ደባልቀው የያዙ ናቸው። ብሬቬደንት፣ ሁልጊዜም ጥንቃቄ የተሞላበት አቋም ይይዛሉ። ከጆን ባፕቲስት ጋር በሚያደርጉት ጉዞ የሚያገኙት ደስታ ከፍተኛ መሆኑን ቢገልፁም፣ ብዙም ሣይቆይ ገሸሽ እያደረጉት መሆናቸው መታወቅ ጀመረ። ሰውዬው፣ በርግጥ ሊሠሩት የፈለጉት ከእሾሃማ ፍሬነታቸው በስተጀርባ ሆነው እምነታቸውን የሚያጠነክርላቸውን መንፈሣዊ እንቅስቃሴ ማከናወን ነው።

የሁለቱ ሰዎች ፊፅሞ አለመመሣሰል ከዕለታት አንድ ቀን በቤት ውስጥ ቡተነሣ ጭውውት ላይ ተገለፀ። ጆን ባፕቲስት፣ አሁን ዮሴፍ የተባለትን ሰው፣ ወደ ክህነት ተግባር እንዴት እንደገቡ ጠየቃቸው። ካህኑም፣ በገራገር የራስ መተማመን ስሜት መልስ ሰጡ።

«በጣም ቀላል ነው። የተወለድኩት ከሃብታምና ሁሉም በእጁ፣ ሁሉም በደጁ ከሆነ ቤተሰብ ነው። ለኔ፣ ሁሉም ነገር በጣም ቀላል ነበር። ማወቅ የቻልኩት ያስተማሩኝን ብቻ ነበር። ሳይንስ በሚባለው ቋንቋ፣ የአፈጣጠር ፍቃድ ያለችግር ተዘጋጅቶ ቀርቦልኝ፣ እግዚአብሔርም፣ ቅዱስ ፈቃዱን በኔ ላይ አዘነበ። ሁሉንም ነገር እርሱ ሰጠኝ። እኔም፣ ሁሉንም ነገር መልሼ ልሰጠው ፈለግሁ»



«እኔ ደግሞ» አለ ጆን ባፕቲስት «በተቃራኒው አቅጣጫ ነኝ። የተወለድኩበት፣ ቤተሰብ አልባ ከሆነና ከድሃ ነው። በስድስት ዓመቴ፣ ለአንድ መድሃኒት ቀማሚ እንዳገለግል ተላክሁ። አንድ ውሻ መንከባለልን እንዲማር እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ የዚህ የመድሃኒት ቀማሚ ሴት ልጅም ፊደል አስተማረችኝ። ያገኘሁት ዕውቀት ይኸው ብቻ ነበር። የቀረውን ሁሉ በራሴ ጥረት ተማርኩ። በምችለው ዘዴ ሁሉ መማር ቻልኩ። የርስዎን አባባል ብከተል፣ እግዚአብሔር ምንም አልሰጠኝምና ዕዳ የለብኝም»

ሕግ የጣሰን ተማሪ የሚመለከት ሌላ ተማሪ፣ ቅጣቱን ትጋራለህ ቢባል የሚሰማውን ዓይነት ፍርሃት፣ ጂስዊቱ በመሸበር ስሜት ተመለከቱት። ምንም እንኳ ፖንሴ እውነተኛው ሊያብሎስ ባይሆንም፣ ከመልዕክተኞቹ አንዱ እንደሆነ ገመቱት። ከመጀመሪያ ጀምሮ፣ አባ ዜርማውና ቆንሲሉ፣ ማለቂያ የሌለው ሃይማኖታዊ ማስጠንቂያ በጆሮአቸው ውስጥ ሲያንቆቁሩላቸው ስለነበረ፣ መሠረት የሌለው ጥላቻ ተክለውባቸዋል። በዚያኑ ዕለት፣ ጆን ባፕ ቲስት ብቻውን መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ተገነዘበ። ሜትር ዠረሚን እጅግ በጣም ነው ያጣው። ጓደኝነቱን፣ ግብዞችን ሁሉ ከአገር እንዲጠፉ የሚያደርገውን ለእውነት ሟችነቱን፣ ቸርነቱንና እንደልብ የማይገኘውን የጨዋታ ለዛውን በርግጥ አጥቷቸዋል።

ከሁለት ቀናት በኋላ፣ ቅፍለቱ ማንፋሉትን ለቀቀ። የጋማ ከብቶቹ ወደ አንድ መቶ ሃምሣ ይደርሣሉ። ጉዞው ቀጥ ያለና ረዥም ሠልፍ ሲሆን ሃጂ አሊ፣ ፖንሴና ዮሴፍ በጉዞው መሃል ላይ ናቸው። ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አንድ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ከተጓዙ በኋላ፣ አልካንታራ በተባለ መንደር ሲደርሱ ሠፈሩ። ከዚህ በኋላ የአባይ ቅርንጫፍ ነው የሚባል አንድ ጠባብ የድንጋይ ድልድይ ያለበት የወንዝ ቦይ አቋረጡና፣ በበረሃው ውስጥ ጭንቅላቱና ሆዱ አካባቢ በመሸርሸር የተጉዳ፣ የተቀመጠ ፊርአንን ይወክላል የተባለ ትልቅ የእግርና የመጫሚያው ፍራሽ ያለበት ሃውልት አጠገብ ሠፈሩ። ሰቅፈለቱ መሪ ውስታ ምስጋና ይግባውና፣ ሃጂ አሊና ፖንሴ በሃውልቱ የአውራ ጣቶች መካከል ሁለት ውብ ቦታዎችን የኔነው የኔ ነው፣ ለማለት ችለው ነበር። በዚህ እጅግ ታላቅ በሆነው የድንጋይ ክምር መካከል ያለው ገባ ያለ ቦታ ዋሻ መሰል ስለሆነ ከሌሊቱ ቅዝቃዜ ይከላከላቸዋል።

ዮሴፍ፣ ለጌቶቻቸው ራታቸውን አዘጋጁላቸው። ሾርባውን እያማሰሉ ባሉበት ጊዜ፣ ፖንሴ ከምድጃው አጠገብ ሆኖ አገዛቸው። የጀስዊቱ ካህን ከመቼውም ይልቅ የተጨነቁ ሆነው አገኟቸው።

«ግመል ነጂዎቹን ቀደም ብዬ ነበር የተቀላቀልኳቸው፣ እናም ጥቂቱ ውይይታቸው ጆሮዬ ጥልቅ አለ» አሉ ቄሱ።

«እሺ፣ ምን ነበር የሚሉት?»

«በቅፍለቱ ውስጥ ሌላ ፈረንሣዊ አለ ይላሉ»

«ይህ ታዲያ መልካም ነው» አለ ፖንሴ ሳይቆጣና ሳይረበሽ። «አውሮፖውያን ነጋዴዎች ወደላይኛው ግብፅ ብዙ ጊዜና እንዲያውም ኑቢያ ድረስ ይጓዛሉ»

የጀስዊቱ ቄስ የባህርይ ሁኔታ ይረብሸው ጀምር። የሚታይባቸው የጥፋተኛነት ስሜት ሁኔታ፣ ባልተቋረጠ መልክ የመጨነቃቸውና ለዛ ማጣታቸው ሁሉ ያበሣጆት ጀመር። ጆን ባፕቲስት በበኩሉም፣ ሰውዬውን በአሽሙር መጎሻሸምና ግልፅ ማድረግ ጀመረ።

«እንዲህ ባለ ትልቅ ቅፍለት ውስጥ ብቻህን እንደሆንክ አስብ፣ እናም በተጓዦች መካከል ሁለት ሌሎች ክርስቲያኖች እንዳሉ አወቅህ እንበል። ይህ መቼም ተራ ግንዛቤ ነው። ታዲያ ፈጥነህ ልታገኛቸው አትሻም?» ሲሉ አባ ብሬቬደንት እያጉረመረሙ ጠየቁት።

«ወደ ምስራቁ ዓለም፣ ማንነታቸው በራሣቸው አገር ሰው እንኳ ሳይታወቅ የሚጓዙ ዘዋሪዎች ብዙ ናቸው» አለ ጆን ባፕቲስት ትዕግስቱ እያለቀበት

«እንግዲያውስ ይህን የሚባለውን ሰው ሄደን እንፈልገው፣ በዚህም ከኛ ይሸሽ እንደሆነ ወይም የሚደብቀው ነገር እንዳለ እናውቃለን»

በመጨረሻ ላይ ጆን ባፕቲስት ተሸነፈ። መከራከሩ ሰልችቶታል። የእኒህ እርጉም ቄስ ጉጉትም፣ እያሸነፈው መጣ። በሠፈሩ ዙሪያ ዞሮ ለማየት ተስማማ። ዮሴፍ፣ ማማሰያ ማንኪያውን ለኑቢያው ሰጡትና እንዳያቃጥለው አስጠነቀቁት። ምሽቱ ከመጋመሱ በፊት



የቀራቸው ጊዜ አጭር በመሆኑ፣ ቅፍለቱም ትልቅ ስለሆነ የሥራ ክፍፍል አደረጉ። ካህኑ፣ በትልቁ የድንጋይ ሃውልት በአንድ ጐን ሲሄዱ፣ ፖንሴ በሌላው ጐን ሄደ። ጨለማው ፈጠነ። ከአድማስ ላይ የተንጠለጠለችው ፀሐይ፣ ቀይ ኳስ መምሰልና በጥቁሩ የበረሃው ክብ የመሬት ቅርፅ ላይ መዘርጋት ጀምራለች። እየሸሸ የሚሄደው ብርሃን፣ ከሰፈሩ በተነሣው አቧራ ሳቢያ፣ የተለያዩ የቀስተ ደመና ቀለሞች ስለተፈጠሩ፣ ወዲያና ወዲህ የሚንቀሣቀሱትን ሰዎች፣ ጭጋጋማ ብርሃን ዙሪያቸውን ከብቧቸዋል። ሁለቱ ሰዎች፣ ጨለማው ለዓይን እስኪከለክል ድረስ ብዙ ቡድኖችን ለመመርመር ቢሞክሩም፣ ፈረንሣዊ የሚመስል ሰው ማግኘት ግን አልቻሉም። አባ ቬርሣው፣ በክፍቱኖች ላይ የሚቃጣ ሴራ እንደሚኖር ስላስጠነቀቋቸውና የነዚህም ሴረኞች ጠረን በዚህም ምስጢራዊ ጉዞ ውስጥ ስለሚሸትት ፈልገው በማጣታቸው ውጤት ላይ እርግጠኛ አልሆኑም።

የሚቀጥሉት ቀናት በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። አንድም የውሃ ጉድጓድ ሳያገኙ ድንጋያማ በረሃ ማቋረጥ ነበረባቸው። የዮሴፍን ሁኔታ ለተመለከተው የሚሰቀጥጥ ነበር። በከባዱ ሙቀት ሳቢያ እየተንጠራወዙ በያንዳንዱ ዕረፍት በሚደረግበት ቦታ ላይ የተሰነጣጠቁትን ከንፈሮቻቸውን ለማርጠብ በፖንሴ ክርቻ ሥር ወደተንጠለጠለው የፍየል ቆዳ ስልቻ ያመራሉ። በሁለተኛው ቀን፣ ባለዘለበቱ ጫማቸው ተገንጥሎ በመውደቁ፣ በሚያቃጥለው መንገድ ላይ በባዶ እግራቸው መንገዝ ተገደዱ። በዚህም የተነሣ በአንድ ቀን የውስጥ እግራቸው ከባድ ውሃ ቋጠረ። ፖንሴ ፣ መድሃኒቶቹን የቀረቀረበትን የቆዳ ሻንጣ ከፍቶ፣ የምስኪኑን ሰው እግሮች በመቀባት እብጠቱ እንዲቀንስላቸው፣ ቁስለቱ እንዲደርቅላቸውና ከሕመማቸውም እፎይታን እንዲያገኙ አደረጋቸው። በማግስቱ፣ ከመኝታቸው ነቅተው መራመድ ሲሞክሩ፣ ገርጥተውና ነፍሣቸውን ስተው ነበር። ይህን የተመለከተው ጆን ባፕቲስት፣ የራሱን ግመል እንዲቀመጡበት ቢጠይቃቸውም፣ ዮሴፍ እንዳችም ነገር ሳይሰማቸው አፋቸውን ዘግተው መንገዱን ሁሉ ተጓዙ።

እኒህ ሰው ለታዛዥነት እውነተኛ ፍቅር አላቸው። ሆኖም ግን፣ የነፃነትን ያህል የሚፈሩት ሌላ ምንም ነገር የለም ሲል ጆን ባፕቲስት አሰበ።

እንደ ዕድል ሆኖ በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሰማዩ ደመነ። ሙቀቱም መለስ አለ። በዚያ አካባቢ ያለው የምድረበዳው ቦታ በደቃቅ አቧራ የተሸፈነ ነው። ይህ ደግሞ ለባዶ እግር ቀለል ይላል። በዚያን ዕለት ምሽት፣ ሃጂ አሊ፣ እሰፈሩበት ቦታ ድረስ መጥቶ፣ ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ አንድ ትልቅ የበረሃ ገነት የሆነ መንደር እንደሚደርሱ፣ በዚያም ብዙ ቀናትን እንደሚስነብቱ ነገራቸው። ከዚህ በኋላ፣ ወደ ቅፍለቱ መሪ ወደ ሃሰን አል ቢልቤሲ ሄደ። ሃሰን አል ቢልቤሲ፣ አንድ የተጐዳ ግመል አርዶ፣ ሥጋው በትልቅ እሣት ላይ እየተቀቀለ ነው።

የሚቀጥለውም ቀን እንዲሁ እጅግ ሞቃት ነበር። ዮሴፍም፣ በድጋሚ እጅግ በጣም ተሰቃዩ። በዚህ ዕለት ምሽት ላይ ጥንታውያኑ፣ ፖርባ የበረሃ ገነት የሚሉት፣ አረቦች ደግሞ

አልዋህ ብለው ከሚጠሩት በታላላቅ የቴምር ዛፎች ተሞልቶ ደን ከሚመስለው መንደር ደረሱ። ይህ ቦታ፣ ግብፅ ግዛት ውስጥ የሚገኝ የመጨረሻው ሩቅ ቦታ ነው። ትንንሽ የቴምር ዛፍ ደኖች እርስ በርሳቸው በቀጫጭን የተክሎች ገመድ እንደ ደሴት ተያይዘውና ተበታትነው፣ በዚህ ደረቅ የአሸዋ ባህር ላይ ይታያሉ። ቦታው በሙሉ አንድ ትልቅ ከተማን ያክላል። ከጥቁሩ አፈር ውስጥ፣ ብዙ ምንጮች ኩልል ብለው በመፍለቅ ረዣዥም የሰብል ተክሎችንና ጥቅጥቅ ያሉ ሣሮችን ያጠጣሉ። በአጫጭር የድንጋይ አጥሮች የተከበቡና አይነ ምድር እንዲደርቅ ማድረግ የሚችሉ ሰብሎች፣ የተዘሩባቸው እርሻዎች አሉ። ሃጂ አሊ፣ በባህሉ መሠረት ቋሚ ደንበኛው ወደሆነች አንዲት የአካባቢው ሴት ዘንድ ሄዶ ሰነበተ። ፖንሴ በበኩሉ የሰሌን ክዳንና አልጋ ሳይቀር ያለው ጐጆ አገኘ። ግመሎቻቸውን ከአንዲት አነስተኛ ኩሬ አጠጥተው እንዲግጡ ለቀቋቸው። ጆን ባፕቲስት፣ አልጋውን ለዮሴፍ ለቅቆላቸው እርሱ ተንጠልጣዩን አልጋውን በሁለት የተምር ዛፎች ላይ አሠረ።



# 3

በበረሃው ጉዞ ውስጥ በነበሩባቸው ሁለት ቀናት መሃል፣ ሃጂ አሊ፣ ከጆን ባፕቲስት ጐን ተቀምጦ ሻይ ሲያፈላለት መፈለጉን ገለፀለት። ረዘም ላለ ጊዜ ሲሳሳቁ ከቆዩ በኋላ፣ ኪጋዩው፣ ለአፍታ ያህል ወደ ገለባው ጐጆ እንዲመጣ ፈረንሳዊውን ጠየቀው።

ጐጆው ውስጥ ከገቡ በኋላ «እስቲ ተመልከተው» አለ አጂ አሊ።

ከሰፊው ጃኬቱ እጅጌ ውስጥ አንድ ክንዱን አወጣና ክንዱን፣ ትከሻውንና የጀርባውን የላይኛውን ክፍል የበላውን የቆዳውን ቁስል ሊያሣየው ልብሱን ወደ ኋላው አወለቀው።

«ይህን አይነት ህመም ከያዘህ ምን ያህል ጊዜ ይሆንሃል?» ሲል ፖንሴ ጠየቀው።

«ሦስት ዓመት ያህል ይሆነኛል። ህመሙ አንዴ ይጠፋል፣ ደግሞ ይመለሣል»

«ለመሆኑ ታክከዋለህ?»

«ቀንና ማታ፣ ሳላቋርጥ ነዋ። ከዚህ ሊያድኑኝ የሚችሉት ነብዩ ብቻ ናቸው። ነገር ግን የርግቾቹም ዐይኖች ወደ ሌላ መመልከት ሲጀምሩ እኔም እስኪደማ ድረስ እጐደፍረዋለሁ።»

ልብሱን እንዲለብስ ፖንሴ ነገረው። ከጐጆው እንደወጡ፣ ሃጂ አሊ፣ በሻዩ ማንቆርቆሪያ አጠገብ ባለው መቀመጫ ላይ ቦታውን ያዘ። ሃኪሙ፣ በጐጆው በር አጠገብ ወደተከመረው ሻንጣው ሄደና በቡሽ የተከደነ ብልቃጥ አመጣ።

«ሁልጊዜም ጠዋትና ማታ በቁስልህ ላይ ይህን ቀባው። ከሦስት ቀን በኋላ እንደገና እንነጋገርበታለን»

ሃጂ አሊ፣ የሐኪሙን እጆች ሣማቸውና ብልቃጡን በጥንቃቄ ተቀብሎ ደስታና ሥራ ተደበላልቀውበት፣ አልባሹ፣ መድሃኒቱን እንዲቀባው ለማድረግ ሄደ።

ትዕይንቱን ክርቀት ሲመለከቱ የነበሩት አባ ብሬሼደንት፣ ጆን ባፕቲስት አጠገብ ለመቀመጥ መጡ። ካህኑ ከጥቂት ቀናት በፊት ካጋጠማቸው ሥቃይ ቢያገግሙም፣ ሁኔታቸው ግን አሁንም የሚያጠራጥርና አስፈሪ ነው።

«ይህን ያህል ጊዜ ለምን ቆየ? ከመነሣታችን በፊት ሁኔታውን ሊያሣየን ይችል ነበር» ሲሉ የግመሎችን ጌታ በመጠራጠር እየተመለከቱ አጉረመረሙ።

«መሆን አልነበረበትም። ካይሮን ከመልቀቃችን በፊት የኔ ህክምና ውጤት አልባ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቲ ያስቡ። ንጉሡንም ማዳን አይችልም፣ ተበዬ በድፍረት ተነግሮብኝ ጉዞውም ይሰረዝ ነበር። አሁን ባለንበት ደረጃ ላይ ግን ፣ ሃጂ አሊ፣ ከፍለነው ራሣችንንም በርሱ ሥር አድርገናል። እዚህ ቢተወን፣ ጥቅሙ በአመዛኙ የርሱ ነው?»

ሁለቱም ዝም አሉ። የካህኑ አዕምሮ ከመቼውም በበለጠ በጨለምተኛ አስተሣሰቦች እንደተወጠረ፣ ጆን ባፕቲስት ገመተ።

እንደ እውነቱ ከሆነ አባ ዶ ብሬቬደንትም ቢሆኑ፣ በጆን ባፕቲስት የሕክምና ችሎታ ላይ እምነት የላቸውም። ዕፀዋትን ለማየት በተጓዙባቸው ጊዜያት የመድሃኒት አዋቂው ችሎታ ምን ያህል ትንሽ እንደሆነ እንዲያዩ አስችሏቸዋል። ጆን ባፕቲስት ግን፣ በምንም ዓይነት የሚወናበድ ሰው አይደለም። «የሥነ-ዕፅዋት ዕውቀት ከመድሃኒት ጋር አንድ ዓይነት ነገር አይደለም። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው ትጋት፣ የተፈጥሮ አስተዋይነት፣ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል ያለውን የስሜት ቅርርብ መገንዘብ ነው። በሕክምና ጥናት የሚፈለገው፣ በሕመምተኛው ሰውና እርሱን ሊፈውስ በሚችለው ዕፅ መካከል ያለውን አስፈላጊ ስምምነት ማግኘት የመቻል ጉዳይ ነው»

እኒህን ጅላጅል ብሬቬደንትን በተመለከተ ከሆነ፣ እንደ አስማት አንድ ዘርፍ አድርገው ያስባሉ። እነዚህ በሃሣብ ያሉ ግን እውነት ያልሆኑ ጉዳዮች ዛሬ በሃጂ አሊ ላይ፣ እና ነገ ደግሞ በንጉሡ ላይ ምን ያህል ከባድ ጉዳት እንደሚኖራቸው አያውቁም። ይህን በተመለከተ ወደ ኋላ መመለስ በጣም የዘገየ ጉዳይ ነው። የጀስዊቱ ካህንም ዕጣ ፈንታቸው፣ ለልማት ወይም ለጥፋት ቢሆን ከዚህ እንግዳ ከሆነ የዕፅ ሃኪም ጋር አስተሳስረውታል።



የውይይቱን ርዕስ ለመለወጥና ድባቡም ቀለል እንዲል ለማድረግ በማሰብ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ጭውውቱን አል-ዋህ በተባለው በዚህ የበረሃ ገነት የሆነ መንደር ስም ላይ እንዲያተኩር አደረገ።

«ሥሙ የመጣው አል-ሃዊህ ማለት አየር ከሚለው ይመስለኛል። ስሙ በአካባቢው ካለው ቅዝቃዜና የተምር ቅጠሎች ያለዕረፍት እየተንሻሹ ከሚፈጥሩት ትንፋሽ ሊሆን ይችላል»

ብሬቬደንት፣ በሌላ በኩል፣ ሃላዋ ማለት ጣፋጭ ማለት ነው ወደሚለው ትርጓሜ ይበልጥ አደሉ። በቋንቋው ዕድገትና ታሪክ ላይ ያላቸውን ልዩነት አንድ ተወላጅ ሰው እንዲዳኛቸው ወሰኑ።በመጀመሪያ ያገኙዋቸው አንድ ሽማግሌ ሰው ሁለት አህዮችን ይነዱ ነበር። ቅርጫቶቻቸው በተምር የተሞሉ ሲሆን፣ ከከብቶቹ ጉን እየተራመዱ በትንሽ ዘንግ እንስሳቱን ወጋ ወጋ ያደርጓቸዋል።

አረቦች ቋንቋቸውን ይወድዳሉ። ቋንቋን በሚመለከት፣ በቃላት ላይ የሚነሱ አለመግባባቶችን ሁልጊዜም ያስተናግዳሉ። ሽማግሌው፣ ሁለቱን ተጓዦች እንዳገኟቸው ጭርምትምት ያለው ፊታቸው በታላቅ ፈገግታ ተዘረጋጋ። ሁለቱ ፈረንሣዊያን፣ የየራሣቸውን አስተያየት በአጭሩ ገለፁላቸው። ሽማግሌው፣ በያዙት ዘንግ የሽምላ ስንዘራን እንደማክሸፍ ዓይነት የብሬቬዳንትን ደረት ወጋ አደረጉና

«አይደለም!»

ቀጥሎም ወደ ፖንሴ ዞሩና እርሱም ላይ እንደዚያው ካደረጉ በኋላ «አል-ዋህ» አሉ። ቃሉን በተወላጆች ቅላፄ ተናገሩና እንዲከተሏቸው በዓይናቸው ጠቀሷቸው።

ሽማግሌው እየመሯቸው፣ ጆን ባፕቲስትና ብሬቬደንት እየተከተሏቸው፣ ሁለቱ አህዮች ከኋላ እየተጎተቱ መስኩ በተመነጠረበት ቦታ አቋረጠው አይነ ምድር እንዲደርቅ የሚያደርገው ሰብል ያለበትን ማሣ አልፈው በመታረስ ላይ ያለውን ቦታ አቋርጠው ጥቅጥቅ ያለ ጥቁር አረንጓዴ ቅጠል ያለባቸው የቁጥቋጦዎች ጥሻ ውስጥ ገቡ። ወደ ትንንሾቹ ዛፎች በበትራቸው እያመለከቱ ሦስት ጊዜ ተናገሩ።

«አል-ዋህ!»

ዕፁ፣ልስልስና አንፀባራቂ ጥቁር አረንጓዴ ቅጠሎች ከጥቂት እሾሆች ጋር ያለው ነው።

«የሙሴ በትር-አልዋህ» አሉ ሽማግሌው

ቀጥሎም ወደ ቁጥቋጦው አመለከቱ

«የካሊድ ኢብን አልዋሊድ በትር-አልዋህ!»

«ኢብን አልዋሊድ ማነው?» ሲሉ አባ ብሬቬደንት በትህትና ጠየቁ።

የቀረበው ጥያቄ፣ የማያረካና የማይምንት መገለጫ በመሆኑ ሽማግለው ግንባራቸውን ቋጠሩ።

«ታላቅ ጄነራል ነው። ክርስቲያኖችን ደምሳሽ የነበረ» አሉ።

«እውነት?» አሉ ቄሱ ቅር እያላቸው።

«ጥንት እዚህ ቦታ የነበረው ውሃ መራራ ነበር። ካሊድ ኢብን አልዋሊድ በበትሩ ምንጮቹን መታቸው። ከዚያም ውሃው የጠራና ንፁህ ሆነ። አልዋህ!»

ሽማግሌውን አመስግነው ወደ ጉጆው በዝምታ ተመለሱ።

«እና አሁንስ?» አሉ አባ ዴ ብሬቬደንት፣ እጃቢያቸው በሃሣብ ጭልጥ ብሎ መንዙን ሲመለከቱ። «ለመሆኑ ይህች ፕላኔት ምን መለኮታዊ መልዕክት ታመላክትሃለች?»

ጆን ባፕቲስት፣ ግልፅ ያልሆነ ምልክት አሣየ።

ቁጥቋጦው ብቻውን ጠፍቶ፣ ብቻውን አድጎ፣ በቆንሲሉ የአትክልት ቦታ ያለው ዓይነት መሆኑን እርግጠኛ ሆነ። ከዚያ ዛፍ ላይ ትንሽ ቅርንጫፍ ቆርጦ ሊወስድ ቀና በማለቱ አሊስን ያገኛት ትዝ ስላለው በሃሣብ ዋለለ።



ሰሁለት ሣምንት ያህል፣ አሊስ በየቀኑ በሃሣቡ ውስጥ ትመጣ ነበር። ሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ መልካም የየዕለት ልማዶች መሆን ጀምረዋል። አባ ጋቦሬ፣ ጣፋጩን መድሃኒታቸውን ከወሰዱ በኋላ በረኘሩሙ ሃሩ ላይ ተኝተዋል። አሊስ፣ ከወፎቹና ከዕፅዋቱ ጋር ለማውራት ወደ ፎቁ ወጥታለች። ጆን ባፕቲስት እንደተነበየው፣ እያንዳንዱ ተክል ምን እንደሚፈልግ፣ ትንንሾቹን አይሂችሁ ማለትና የአሽናፊነት ስሜት ያላቸውን የትልልቆቹን ቅርንጫፎች በደመነፍስ ስሜት እየገረዘች ወደኋላ መለስ ታደርጋቸዋለች። የመፃህፍቱን ገፆች ለመገላለጥና በቅርንጫፎቹ ላይ ተንጠልጥለው ያሉትን ሻምላዎች እያመነታችም ቢሆን ለመጨበጥ ጊዜው ነበራት። በተንጠልጣዩ አልጋ ላይ ወጥታ ዝርግትግት ለማለትም እስከመድፈር ደርሣ ነበር። ይሁንና፣ ሁሉም ነገር አለመኖርን የሚናገር ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ የጆን ባፕቲስት ዱካ ባለበት ሁሉ በስሜትዋ እርሱ ያለ ይመስላት ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጭንቅላቱ ተቆርጦበት እንደተወሰደበት በድን አካል ክፉኛ ታጣዋለች።

ከቡቱ ጋር ከተለማመደች ከሁለት ሣምንታት በኋላ፣ በውስጠኛው አደባባይ በሚገኘው እርከን ላይ ሙከራ ማድረግ ጀመረች። ምንም እንኳ መጋረጃዎቹ ሁሉ የተዘጉ ቢሆኑም፣ ምናልባት ከመስኮቶቹ በስተጀረባ ሆኖ የሚመለከት ሰው ቢኖርና የሆነ አሉባልታ ከአባቷ ጆሮ ቢደረስ በሚል ፈራች።

በመጀመሪያ ከእርከኑ ላይ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቆየች። ፊት ለፊት ባሉት መስኮቶች በስተጀርባ አንዳችም የሚንቀሣቀስ ነገር የሌለ መሰላት። ቀስ በቀስ ድፍረት እያገኘች ስትመጣ፣ በመጨረሻ ላይ ወንበር አውጥታ ግማሹን የማለዳ ሰዓት በደጅ ማሣለፍ ቻለች።

ቅፍለቱ ከሄደ ከአምስተኛው ቀን በኋላ፣ ከመጋረጃዎቹ በአንደኛው በስተጀርባ በኩል አንድ አነስተኛ ድምፅ ስትሰማ እዚያው ነበረች። በፍርሃት ራደች። በኋላም ደነዘዘች። መስኮቱን የሚቧጥጠው ድምፅ እንደገና ተመለሰ። ድምፁ የሚመጣው ከርስዋ ከሦስት ጫማ በላይ ከፍ ከሚለውና ለእርከኑ ቅርብ ከሆነው መስኮት ነው። በቅፅበት መጋረጃዎቹ ሁሉ ግልጥልጥ አሉና አንዲት ሴት ታየች። የደነገጠችው ወጣት፣ እርዳታ ለማግኘት፣ እሪታዋን ልታቀልጠው ስትል፣ ሴትዮዋ ጣቶችዋን ከንፈሮችዋ ላይ በማድረግ፣ አሊስ ምንም ዓይነት

ድምፅ እንዳታሰማ አስጠነቀቀቻት። አሊስ፣ ራሷን አረጋጋችና ሁለቱም ሴቶች በዝምታ ርስ በርሳቸው ተያዩ። በመስኮት የታየችው ሴት፣ በዕድሜ በሰል ያለች ነበረች። ሴትዮዋ፣ በርቀት ከሚገኝ የሕይወት ጫፍ የወረደችና በርስዋ ዕድሜ ማንም ሊደርስባት የማይችል መሰለቻት። ከአርባ ዓመት በላይ ይሆናታል። ጠንካራና ውብ የገበሬ ሴት ቁመና ያላትና ፊትዋ ሙልት ያለ ነች። ዐይኖችዋ፣ ፈገግታ የተሞሉና ጉላ ጉላ ያሉ ናቸው። ወዲያውኑ፣ በአንድነት መንፈስ ስሜት እንዳየቻት፣ በድሃ ኩራት የአይኖችዋን ብርሃን ለቀቀችባቸው። ተራ የሆነ ጥቁር ቡኒ የአገልጋይ ልብስ ለለበሰች፣ ድቡልቡሎቹ ክንዶችዋ፣ ጠንካራዎቹ ትከሻዎችዋና ፍርጥም ያሉት ጡቶችዋ ከቅርጫት ውስጥ ሞልቶ የሚፈስስ ፍሬ ይመስላሉ።

«አይዞሽ ጓደኛሽ ነኝ፣ ጓደኛሽ ነኝ» እያለች በአንድ እጅዋ ምልክት በመስጠት ስታንሾካሽክላት ሌላው እጅዋ ከንፈሮችዋ ላይ እንደተቀመጠ ነበር።

አሊስ፣ አቅሏ መመለሱን ስትመለከት፣ አሁንም ዝቅ ባለ ድምፅ «ሂጂና ቁሱ ተኝተው እንደሆነ ተመልከቺቸው» አለቻት።

ወጣቷ ልጃገረድም የተነገራትን ፈፀመች።

ወደ ታችኛው ፎቅ ስትወርድ ስለቁሱ እንዴት ማወቅ ቻለች? ስትል በመገረም ራሷን አወዛወዘች።

አባ ጋቦሬ በሰላም ያንኮራፋሉ።

«እነው ወደታች፣ እመጣለሁ» ስትል ሴትዮዋ ተናገረች።

በዚህ ላይ ወጣቷ ልጃገረድ ልትጨቃጨቅ አልፈለገችም። ይልቁንስ፣ ይህች ጠንካራ ሴት በመስኮቱ ላይ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ወጥታ፣ ዱካዋ እንደማይሰማ ድመት እርከኑ ላይ ስትዘልል ተመለከተቻት። ተከረዝ የለሽ ለንደል ጫማ ብታደርግም፣ አሊስ ትረዝማለች። የተጨማደደውን ቀሚስዋን በእጇ መዳፍ አንድ ሁለት ጊዜ ሳብ፣ ሳብ አድርጋ ካስተካከለች በኋላ፣ ወጣቷ ልጃገረድ አጠገብ ደረሰች። የአሊስን ሁለት እጆች በወዳጃዊ ስሜት በመያዝና ወደ ራስዋ ሳብ በማድረግ፣ በአድናቆት ከላይ እስከታች ቃኘቻት።

«እንደተባለውም በርግጥም ቆንጆ ነሽ» አለቻት



አሊስ በንግግሩ አፈረች። እንዲያውም ቀይ ወፍራም አበባ የሆነች መሰላት።

«እርሱ ከተናገረውም የበለጠ ቆንጆ ነሽ» ስትል አከለች።

በሴትዮዋ ፊት ላይ አንዳች የርህራሄና የማፅናናት ሁኔታ ይነበባል። ፈገግታዋ፣ በዓይኖችዋና በከንፈሮችዋ ዙሪያ የሚታዩት የፊት መሸብሸቦች፣ እንባና የመከራ ዘመናት አብረዋት እንደዘለቁ ያመለክታሉ። እንዲህ ንፁህ በሆነው ደስታዋ ላይ እነዚህ ነገሮች ጥልቅ የፍቅር ስቡት ኃይልን ይጨምራሉ።

«ማነው እሱ?» ስትል ጠየቀች

«ዠረሚ ነዋ! ሌላ ማን ይሆናል» አለች ሴትዮዋ እየሣቀች

ማዳሞዜል ዴ ማይሌ፣ በፊትዋ ላይ የሚነበበውን ቅሬታ መደበቅ አልቻለችም።

«ስለዚህ ጉዳይ የነገረኝም እርሱ ነው» ስትል ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ አክላ ተናገረች።

የአሊስን እጅ ይዛ ወደ አንድ ወንበር ወስዳት እንድትቀመጥ አደረገቻት። እርስዋ ግን ወደ ፎቅ መውጫው ላይ ባለው የደረጃ መደገፊያ ላይ ተደገፈች።

«ባለፉት ሁለት ሣምንታት ስከታተልሽ ነበር። ስለአንቺ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ። ስምሽን አውቃለሁ። ከማን ጋር ፍቅር እንደያዘሽም አውቃለሁ። በርግጥ ይህ ንግግሬ ተገቢ አይደለም። ስለራሴ ጥቂት ነገሮችን ልንገርሽ። ስሜ፣ ፍራንቾይዝ ይባላል። የምኖረው እዚህ ቤት ውስጥ ነው። ሁለቱ ጌቶች፣ እዚህ ቤት በነበሩ ጊዜ በየዕለቱ እየመጣሁ ምግባቸውን አዘጋጅላቸው ነበር። ይህ ማረጋገጫ ሊሆንሽ ይችላል?»

«አዎን . . . የለም . . . እኔ እንጃ አላውቅም» አለች አሊስ ግራ ገብቷት።

«በርግጥ ከቀናት በፊት ሳነጋግርሽ ይገባኝ ነበር። ታዲያ ፋይዳ ያለው ሥራ ሳላከናውን፣ እዚሁ ከአስር ጫማ በላይ በማይርቅ ቦታ ሆኜ፣ አንቺን ማየት የሚያስደስተኝ መሰለሽ?»

የፍራንቸይዝ ሃር የመሰለው ጥቁር የፀጉር ክምር በግራና ቀኝ ግንባርዋ ሲወድቅ፣ አንገትዋን መትታ ወደ ቦታው መለሰችው። እጆችዋ በከባድ ሥራ ምክንያት መቅላታቸውን፣ የጣት ጥፍሮችዋ በአጫጭሩ የተቆረጡና የተሰባበሩ መሆናቸውን፣ አሊስ ተመለከተች። ይሁን እንጂ እነዚህ እጆች የሴት እጆች ናቸው። የእጆችዋ ቆዳ፣ የደም ስር ጅማቶችዋን ሙሉ በሙሉ በውበት በመሸፈናቸው፣ ለስላሣና ደስ የሚያሰኙ ናቸው።

«አየሽ፣ ልትረጂኝ ይገባሻል። እኔ እንደሆንኩ የተቀበልኩት ትዕዛዝ አለ። መቼም . . . አንቺ ሁልጊዜም ትዕዛዝ ሳትቀበይ ትችያለሽ። እኔ ግን ቃል ገብቻለሁ።»

«ቃል ገብቻለሁ? ምን ብለሽ ነው ቃል የገባሽው? ደግሞስ ለማን ነው ቃል የገባሽው?» ስትል አሊስ ጠየቀች

«ለዠረሚ ነዋ። እዚህ አርፈሽ መቀመጥ እስክትችይ ድረስ ልጠብቅሽ፣ ቁስም ፈጥነው ማንቀሳቀሱታቸውን በየቀኑ ለማረጋገጥ፣ ምዬለታለሁ። በነገራችን ላይ ያዘጋጁላቸው መጠጥ አሁንም በበቂ መጠን አለ እንዴ?»

«ግማሽ ደምበጃን ይሆናል እላለሁ»

«ሲያልቅ ሲል መልሼ እንድሞላው አስታውሺኝ»

«በብዛት አለሽ እንዴ?» ስትል የመጠጡ የማለቅ ሁኔታ ለብዙ ቀናት ሲያስጨንቃት የነበረችው አሊስ ጠየቀቻት።

«እስከዘለዓለም ብትፈልጊውም ሞልቷል። ቆንሲሉ አባትሽ፣ በሃያ ፔያስትሬ የሚሸጡልን ዓይነት ተራና መናኛ መጠጥ ነው!»

ፍራንቸይዝ፣ ጭንቅላትዋን ወደ ኋላ ጣል አድርጋ በለሆሣስ ሣቀች። ጥርሶችዋ፣ ችምችም ያሉ፣ እንደሉል የነጡና ሙሉ ናቸው። ወዲያውኑ ኮስተር አለች።

«ይሆን ሁሉና እንዲያውም ደብዳቤውንም የምሰጥሽ ከዚህ በኋላ ነው ብዬ ለዠረሚ ቃል ገብቼለታለሁ።»



«ደብዳቤ!» አሊስ በሣቅ ፈነዳች

ምንንም ነገር ልትረዳ አልቻለችም። ዠረሚ? ደብዳቤ? እንዲያውም ፍርሃት፣ ፍርሃት ይላት ጀመር።

በታችኛው ፎቅ ውስጥ ከተኙት ሰው የሚመጣ ድምፅ እንዳለ ለማዳመጥ እንዲችሉ፣ ዝም እንድትል ፍራንቸይዝ አደረገቻት። የሚያዳምጡት ምንም ነገር ባለመኖሩ፣ ልጃገረዲቱም በመጓጓት የምትጠብቀው ነገር መኖሩን በመረዳት፣ ፍራንቸይዝ እጆችዋን ወደ ቀሚሷ ውስጥ ከትታ አንድ ፖስታ አወጣች።

«ምን ያህል ጓጉተሻል? አንቺው! እዚህ ቦታ ባለፉት ሁለት ሣምንቶች በትዕግስት ስትጠብቂ ሰንብተሻል። ከእንግዲህ በኋላ ጥቂት ተጨማሪ ጊዜያትን ማቆየት የሚበዛም ይመስለኛል! እንቺ ተቀበይኝ»

አሊስ፣ ደብዳቤውን እንደመንጠቅ ዓይነት አድርጋ ወደሰችውና አነበበችው። «ለማዳም ሞዜል ዴ ማይሌ፣» ከመጀመሪያው ዕለት አንስቶ ደጋግማ፣ ደጋግማ ስታነብበው የነበረውን የጆን ባፕቲስትን ማስታወሻ ዓይነት የብዕር አጣጣል ነው።

# 4

ከሦስት ቀን በኋላ ረኸሙ የቅፍለት ሰልፍ እንደገና በዝግታ ጀመረ። ራቅ እያለ ወደ ደቡብ በተዘረጉት ምድሮች ባሉት አገሮች የቀኑ ሐሩር ከባድ ነው። በዚህ ወቀት፣ ጨረቃ በምድረበዳው ላይ የለሊት ተረኛ መሆን ስለጀመረች በለሊት ለመጓዝ ውሣኔ ተደረገ። ቅፍለቱ ጉዞውን የሚጀምረው ከሰዓት በኋላ ፀሐይ መጥለቅ ስትጀምር ይሆናል። የውሃ ጉድጓዶች መጠንም እጅግ ስለሚቀንስ የውሃ ዕደላውም ሊያንስ ይችላል። ለስምንት ቀናት የሚበቃቸውን ምግብ ይይዛሉ። ግመሎቹ የመጨረሻውን የጭነት ክብደት ስለተሸከሙ፣ በመጨረሻ ላይ ዮሴፍ አንድ ጆንያ እንዲሸከሙ ተሰጣቸው።

ሃጂ አሊ፣ በግልፅ የማያስታውቅ አስተያየት ጀመረ። ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተመላለሰ የቅፍለቱን ጭነቶች ይመለከታል። ትዕዛዞችን እየጮኸ ያስተላልፋል፣ በአለንጋው ሸጥ ያደርጋል። በቀጥታ በፖንሴ ፊት ብዙ ጊዜ ቢመላለስም ለቁስሉ የተሰጠው ህክምና መሥራት አለመሥራቱን ግን የመግለፅ አዝማሚያ አላሣየም። ፈረንሣዊው ሰው ግን፣ የተባለው ሦስት ቀን ሣያልፍ በፊት አንዳችም ጥያቄ ላለማቅረብ ታቀበ።

ቅፍለቱ እንቅስቃሴውን ጀመረ። ለስለስ ባለው የምሽት አየር በዝግታ መጓዝ ቀጠለ። ጨረቃ የብርሃን ብናኟን በነገሮች ሁሉ ላይ እያሣረፈች ጨለማውን ስለምትገፍፍ፣ እፎይታን ትሰጣለች። የሚወዛወዙት ግመሎች፣ በዝምታ ተመቻችተው የሚራመዱት ሰዎች፣ በአሸዋው ላይ የሚሰሙት በመቶዎች የሚቆጠሩ የታፈኑ የእግር ዱካ ድምፆች ስሜትን በሚያጓጉ መልክ ያባብላሉ። በአጠቃላይ በእንቅልፍ ላለመውደቅ ከባድ ጥረትን ይጠይቃሉ።

ንጋት ላይ፣ በስተግራቸው ያለው ሰማይ በሃምራዊ ብርሃን መሞላት ሲጀምር፣ የመጀመሪያውን የውሀ ጉድጓድ ቦታ ደረሱና ጭነቶችን አራግፈው ሰፈሩ። ይህ ቦታ የበረሃ ገነት ሣይሆን፣ ጥቂት ዛፎች ያሉበት፣ በብርማ አብረቅራቂ ሰፈፍ ተሸፍኖ፣ ክፉኛ የሚሸት የጉድጓድ ውሃ ያለበት ነው። ሰፈፉ ተገፍፎ የሚነሣበት የተበከለ ነገር ያለበት ሲሆን ጣዕሙም የሚቀፍፍ ነው። ሰዎቹ፣ ጭንቅላቶቻቸውንና ፊቶቻቸውን በዚሁ ውሃ አቀዘቀዙ። በአዕምሮው ውስጥ ራሱን ለማጥፋት ለረዥም ጊዜ ሲያሰላስል የኖረ ሰው ካልሆነ በስተቀር፣ በውሃ ጥማት ምክንያት ይህንን ጠጥቶ ለመሞት የሚፈልግ ሰው አይኖርም።



ሃጂ አሊ፣ ሕክምና ካገኘ ሦስተኛውን ቀን እንዳይደርስ የለምና ደረሰ። ደርሶም አለፈ። ሠፈር ከተቀረቀረ በኋላ ሃጂ አሊ፣ በጥልቅ ስሜትና ክስተር ባለ ሁኔታ በፖንሴ ፊት አልፎ ከማለዳው ፀሎት በፊት ፊቶቻቸውንና እጆቻቸውን ለመታጠብ በጉድጓድ ውሃ አጠገብ ከተሰበሰቡት ሰዎች ጋር ተደባለቀ። ሰዎቹ፣ ደረቶቻቸውና ጭንቅላቶቻቸው እርቃናቸውን ናቸው። ሃጂ አሊ፣ በቀስታ እንደ ሰዎቹ አደረገ። ሰፊውን ሱሪውን እንደለበሰ ቢሆንም ጫማዎቹን ግን አወለቃቸው። ውሃ ቀድቶ በራሱ ላይ ከለበሰ። ሰውነቱን አሻሸና ምራቁን ተፋ። ጃኬቱንና ጥምጣሙን በአንድ እጁ፣ ጫማዎቹን በሌላው ይዞ ፖንሴ ፊት ቀረበ። ሕክምና የተደረገበት ቦታ በሙሉ መዳኑንና በጥቂት ቀናት ውስጥ ጨርሶ ሊጠፋ የሚችል ትንሽ ቅርፊት መሰል ነገር መኖሩን ዶክተሩ ተመለከተ። በሽታው ጠፍቷል። ሃጂ አሊ፣ በአክብሮት ለጆን ባፕቲስት ዝቅ ብሎ ሰላምታ አቀረበና ጃኬቱን አጥልቆ ፀጥ ያለ ቦታ በመምረጥ የመስገጃ ምንጣፉን ዘረጋ።

ሁሉንም ድርጊት ሲመለከቱ የነበሩት ዮሴፍ፣ በድብቅ በመስቀል ምልክት ሠርተው አማተቡ።

«ሃያሉ አምላክ! ይህ ተአምር ነው!»

የተሰጠው አስተያየት ችሎታውን ዝቅ ያደረገበት ስለመሰለው ጆን ባፕቲስት ቅር ተሰኘ።

«ሥልጣን ለመያዝ ሲሉ በምስጢር የሚደራጁ ጥቂት ቡድኖች ምን እንደሚሉ ያውቃሉ? በተአምራት የሚያምን ጅል ነው ይላሉ» ሲል ተናገረ።

አባ ብሬቪደንት፣ መሬት መሬት አዩ። «የማያምን ደግሞ ከሃዲ ነው። ዛሬ ማታ መንገዳችንን እንደገና ስንቀጥል በዚህ ጉዳይ ላይ በተመስጦ ሊያስቡበት ይችላሉ» አሉቸው

የሚቀጥሉት ቀኖችና ምሽቶችም በተመሣሣይ ሁኔታ አለፉ። የበረሃው መርከብ፣ ጭር ያለውን ምድረ በዳ ፈጥኖ ለማቋረጥ መገስገስ ጀመረ። በዚያ ቅልጥጥ ባለ የምድር ገፅ መሃል ከወበራቸው የቆዳ ድንኳኖች ሌላ አንዳችም መጠለያ ሣይኖራቸው ብዙ ጊዜ ተኝተው አሳልፈዋል። በጨርቅ ድንኳኖች ውስጥ ያለው ሙቀት የምድጃ ያህል ነው። በማነፃፀር ከታየ፣ ጉዞው ገና ሲጀምርና በእንቅስቃሴ ላይ ሲኮን ካለው ጊዜ ይልቅ፣ አሁን የዕረፍቱ ሰዓት ይበልጥ የሚሰቀጥጥ ነው። ምክንያቱም፣ ቢያንስ፣ ቢያንስ፣ በምሽቱ ጊዜ የምሽቱን ቅዝቃዜ

ይረከቡበታል። ንፁህና ጥሩ የሆነ ሌላ የውሃ ጉድጓድ ዘንድ ሲደርሱ የስልቻ ቀርበታቸውን ሞሉ።

የጆን ባፕቲስትን የሕክምና ችሎታ ከፈተነና ካረጋገጠ በኋላ፣ ሃጂ፣ ይበልጥ ያከብረው ጀመር። አሁንም ቢሆን ለፍላፊና ወሬኛ የጉዞ ጓደኛ ባይሆንም፣ ፈረንሣዊው ሰውዬ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ሁሉ በፈቃደኛነት መልስ መስጠትና እንዲያውም ይጠቅመው ይሆናል በሚልም የሚገምታቸውን መረጃዎች ይነግረው ጀመር። ከዕለታት አንድ ቀን፣ የዕለቱን ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ሃጂ አሊ ወደ ፖንሴ ዘንድ መጣ።

«እስከ አል-ዋሀ ድረስ ሌላ ፈረንሣዊ በቅፍለቱ ውስጥ ነበረ። ለመሆኑ ይህን ታውቅ ኖሯል?»

«ሲወራ ሰምተናል እንጂ አላየነውም፣ ለመሆኑ ማን ነበር?»

«አላወቅነውም። አሁንም ከኛ ሁለት ቀን ቀድሞን ሄዷል»

«ከማን ጋር ነው የሚጓዘው?»

«በግመል ላይ ተቀምጦ ነው የሚጓዘው። አንድ ሰው ተከትሎታል። ሰውዬው ብቻውን ነው»

ግመል ነጂው እንደሄደ፣ ዮሴፍ ስለዜናው ለመጠየቅ መጣ። በከፊል በአዘኔታ፣ በከፊል ደግሞ የጂስዊቱን ተስፋ መቁረጥ ለማስወገድ በማሰብ፣ ጆን ባፕቲስት፣ ሁሉም ነገር መልካም መሆኑን ነገራቸው።

አድካሚ የሆኑ ብዙ የዕረፍት ቀናት ቀጠሉ። ለአይን በምታጥበረብረው ሙሉ ደማቅ ጨረቃ ውስጥ፣ ዝምተኛና አሰልቺ የጉዞ ምሽቶችም ቀጠሉ። በመጨረሻም የምድረ በዳውን ደጋማና ሜዳማ ምድር ወጡ። ይህን ሰፊ ምድር ከወጡ በኋላ ከበስተግርጌአቸው በምሽት ከምድሩ ላይ በተነሣው የጭጋግ ሻሽ የተጀቦነውን የአባይን ሸለቆ ፀሐይ ስትወጣ አገኙት። ወንዙ በሚጠማዘዝበት ቦታ ላይ አንድ ትልቅ ከተማ አለ። አጫጭር ሆነው ትምችም ያሉት የሸክላ ቤቶች ፣ አረንጓዴ በለበሱ አደባባዮችና በታላላቅ የፀሎት መጥሪያ ግንቦቹ የተሞላ ነው። በታችኛው ግብፅ ከሚታየው ጦር መሰል ሾጣጣ የአቶማን ግንብ ይልቅ ይህ ፈፅሞ የተለየ



ነው። የደረሰበት ከተማ ዶንጎላ የሚባልና በሲናር ግዛት ዘውድ ውስጥ የሚገኝ የመጀመሪያው ከተማ ነው። ቅፍለቱ ከከተማው መግቢያ ውጭ ቆመ። ሃጂ አሊና ፖንሴ በቀትር ላይ ወደ ከተማው ዘለቁ። የዶክተሩ አሽከር በሶስት እርምጃ ወደ ኋላ ቀርቶ ይከተላቸዋል። በሲናር ንጉስ ስም፣ ከተማውን በመግዛት ላይ ለሚገኘው ሃላፊ ያመጡትን የድጋፍ ደብዳቤና ስጦታ አቀረቡ።

በብሩህ ጨርቅ በተሠራው ዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ለዕይታ የማይሞላ አጭርና ለንቋሣ ሰው ነው። እንግዶቹን በጋለ ስሜት ከተቀበላቸው በኋላ ፖንሴ መልካም ፈቃዱ ሆኖ ጎይነስውር በመሆን ላይ የምትገኘውን የአሥራ አንድ ዓመት ሴት ልጁን ያክምለት እንደሆነ ጠየቀው። ወጣቷ ልዕልት ተጠርታ ስትመጣ፣ የትም ቦታ ተከትላት የምትሄር የሴት አገልጋይዋን እጅ ይዛ ነበር። የህፃንዋ ዐይኖች ደስ በማይል በቢጫ ነገር ተጣብቆ የተሸፈነ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በተለይም ሌሊት የህፃንዋ እጆች ወደ ኋላ ታስረው ማደር ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም፣ የዓይኖችዋን ቅንድቦች ስትነካቸው ይህ የሚፈስሰው ቢጫ መግል ይፍስበታል፣ ሲል አገረ ገዥው አብራራ። ጆን ባፕቲስት፣ የመድሃኒት ሻንጣውን እንዲያመጡለት ዮሴፍን አዘዛቸው። ሻንጣው ሲመጣለት፣ ቀይ ዱቄት አወጣና ይህ በተወሰነ ንፁህ ውሃ ውስጥ ተበጥብጦ የልጅቱ ዓይኖች፣ በቀን ሦስት ጊዜ በዚሁ መድሃኒት እንዲታጠቡና ሌሊት ግን የጥጥ ባዘቶ እንዲመጠው እንዲያስሩላት አዘዘ።

በሚቀጥለው ማለዳ የልጅቱ ዓይኖች ደረቅ ሆኑ። ከሶስት ቀናት በኋላ ዓይኖችዋን ያለችግር ልትገልጣቸው ስለቻለች ብርሃኗ ተመለሰላት። አገረ-ገዥው በደስታ የሚያደርገው ጠፋው። ለፖንሴም፣ እርሱ ጠይቆት የማይፈቅድለት ምንም ነገር እንደሌለ ነገረው። ፖንሴ በበኩሉ የአገረ-ገዥውን ጥበቃ ብቻ እንደሚፈልግ መለሰ። ዶንጎላ በቆዩበት አንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ፣ በታላቅ ክብር፣ መስተንግዶና በቤተመንግሥቱ ውስጥ ማረፊያ ተሰጥቷቸው ነው። የድኩላ የኋላ እግርና የአልዋዲጌሣ ፍርምባ ተጋብዘዋል። ወቅቱ ባለመሆኑ ንጉሡ አየበነ፣ የጉማሬ ጉንጭም ተሰጥቷቸዋል።

ፖንሴ፣ ከታላላቆቹ መሣፍንትና ቤተሰቦቻቸው የመጡ ብዙ ህመምተኞችን እንዲያክም ተገድዶ ነበር። አገረ-ገዥው፣ ለርሱ ፈረስ፣ ለአሽከሩ ደግሞ አህያ እንዲንሸራሸሩባቸው አቅርቦላቸው በዚህ ሳቢያ ሁለቱ ፈረንሣውያን ይህን በተለየ ለም የሆነውን የሸለቆ ክፍል

ለማየትና ለማድነቅ ቻሉ። በዚህ አካባቢ የወንዙ ዳርቻ መሬት ከውሃው ወለል በላይ ከሁለትና ከሶስት ጫማ የበለጠ አይረዝምም። መሬቱም በግብፅ እንደሚሆነው በየዓመቱ በጐርፍ አይጥለቀለቅም። ሰዎች በሰሩት የማያቋርጥ መዘውር በግድቦቻቸውና በቦዮቻቸው ተጠቅመው ሰብሎቻቸው በመስኖ ይለማሉ። ወደ ቤተመንግስት እንደተመለሱ አገረ ገዥው በግብርና ላይ ስላሰው እቅድና አውራጃውን በትክክል በማስተዳደሩ መደነቁን በማከል ፖንሴ ገለፀ።

«ከተማዋን ልትንከባከባት ከፈለግህ ያንተው ናት። እዚህ ሃኪም ሆነህ መኖር ትችላለህ። ነገውኑ ሸለቆው ውስጥ ሃያ ኤከር መሬትና በዚያ ላይ የሚሠሩ ሰላሣ ቤተሰቦችን እሰጥሃለሁ። ከተማው ውስጥም ቤት፣ በግመሎችና በአረብ ፈረሶች የተሞላ ጋጣም ይኖርሃል። እመነኝ ደስተኛ ትሆናለህ።»

ሃጂ አሊ፣ ጠቃሚ ሰው መሆኑን በድጋሚ አስመሰከረ። በትህትና፣ ለአገረ ገዥው፣ ይህ ፈረንሣዊ የአበሻውን ንጉስ ሲጐበኝ እንደሚጓዝ ገልፆ ለተደረገላቸው ታላቅ መስተንግዶና ስጦታ ሲመለሱ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ገለፀ። የአባይ ሰዎች አበሻዎችን የውሃ ጌቶች አድርገው ያስቧቸዋል። የውሃውን መነሻ ስለሚቆጣጠሩት የፍሰት አቅጣጫውን ሊለውጡት ወይም እስከናካቴው ሊያደርቁት ይችላሉ ብለው ይገምታሉ። «የውሃዎችን አባት» ማስቆጣት የሚታሰብ ነገር አይደለም። ስለዚህም አገረ-ገዥው ዝቅ ብሎ እጅ ነሣ።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ፣ ከፖንሴ ታካሚዎች የሚሰማው ዜና እጅግ በጣም ጥሩ ነበር። በያንዳንዱ ቀን የማይታመን ማገገምና መዳን ይሰማል። አባ ብሬቬደንት እያጉረመረሙም ቢሆን፣ ምንገ ምንም ይሁን ምን፣ ይህ ውጣት የማዳን አቅም እንዳለው አምነው ተቀበሉ። የሌሎችን ሰዎች ስቃይ በጥንቃቄ ለመመርመርና ለመፈተሽ፣ ብሎም ለመፈወስ ችሎታው አለው። ከሰዎች ጋር ያለው መግባባትና መቀራረብም ፍፁም ንፁህ መልክ ያለው ነው። ህፃን ልጅን ሲመለከት፣ በልጁ ውስጥ ፈገግታ ይጫራል። እንስሳት ሳይቀሩ፣ የርሱ በዙሪያቸው መገኘት ርጋታን የሚሰጣቸው ይመስላል። በመንገድ ላይ የሚወጡና ሰዎችን በሩቅ የሚሸሹ አስቀያሚና አስፈሪ እከካም ውሾች፣ መግቢቸውም ባያውቅ በደመነፍስ ከተማው ውስጥ ይከተሉታል። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ሁሉ ጋር ያለው ግብነትና ስምምነት ከጥብቁና ከክብዱ ብሎ ካለው ቅዱስ አግናጢዮስ ይልቅ ከምኛምኞች የቅዱስ ፍራንሲስካ ተከታዮቹ አስተሳሰብ ጋር እጅግ ይመሣሰላል። ጀስዊቶች፣ እንዲህ ያለውን የልጅ ቂላቂልነት በርግጥ



አያደንቁም። በሌላ በኩል የፖንሴ ስጦታዎች እንደ አካባቢው ቋንቋዎችና እምነቶች አንዳችም ዓላማን እንደማያገለግል የእውነተኛውን እምነት ምክንያቶች ግን በምስጢር ለማሣካት የሚጠቅም ዓይነት ነው። ፖንሴ፣ ወደ አቢሲኒያ የሚያስገባውን እጅግ ድንቅ ፖስፖርት አስገኝቷል። ብሬቬደንት ደግሞ ከዚህ የሚገኘውን ጥቅም በሚገባ መጠቀም ይኖርባቸል።

በመጨረሻ የሚለቅቁበትና የሚሄዱበት ሁኔታ ተስተካክሎ ተዘጋጀ። ለመጨረሻው ስንብት በአንድ ቦታ ላይ ለምሽት ግብዣ ተጠሩ። ቅፍለቱ እስሚቀጥለው ማለዳ አይንቀሳቀስም። ምክንያቱም በአጐራባች አገሮች ሊገጥማቸው የሚችለውን አደጋ በመፍራት፣ ጉዟቸው በቀን እንዲሆን ወስነዋል።

በበሩ ላይ የመጧጠጥ አይነት ድምፅ በሚሰማበት ጊዜ ፖንሴ በክፍሉ ውስጥ ዕረፍት ላይ ነበር። ምናልባት ከተማ ውስጥ አንድ የታመመን ሰው እንዲመለከት ሊለምነው መልዕክተኛ መጥቶ ይሆናል። ማን እንደሆነ ለመለየት ብቅ ሲል ፀጉሩን የተላጨ በአፍንጫው ላይ ንፍጡ የሚወርድበት፣ ግማሽ ሰውነቱ እርቃኑን የሆነ አንድ ደካማ፣ ትንሽ ጥቁር ልጅ የማስታወሻ ወረቀት አውጥቶ ሰጠው። ደብዳቤውን ፖንሴ ከፈተው። የተፃፈው በፈረንሳይኛ ነበር።

«መጥተህ እንድንገናኝ። ይህ ህፃን ያሳይሃል»

የእጅ ፅሁፉ አጣጣል እንዳይለይ ቃላቱ የተፃፉት በትልልቅ ፊደላት ነው። በዚያም ላይ መልዕክቱ አልተፈረመበትም።

ፖንሴ በምድር ቤቱ ውስጥ የተኙትን አባ ብሬቬደንትን ቀስቅሶ፣ አብረውት እንዲሄዱ ሊጠይቃቸው ወሰነ። ቀጥሎም የተዘጋጀውና ይዞት የሚሄደውን ሻንጣውን ተመለከተ። ከዚያ ውስጥ አንድ ጉራዴ መዝዞ ታጠቀ። ሌላ አንድ ትልቅ ጋቤ አውጥቶ፣ በፍርሃት ለሚንቀጠቀጡት ጀስዊት ሰጣቸው። ጭለማው እየበረታ፣ ለአይን ያዝ ማድረግ በጀመረበት ሰዓት ትንሹ ልጅ እየመራቸው ወሰዳቸው። የከተማው መሃል በሰዎች የተሞላ ነው። ቀኑን ሙሉ ከቤታቸው ውስጥ የሚቆዩት የከተማው ነዋሪዎች፣ ከመስኮት የለሹ ቤታቸው ቀስ እያሉ በመውጣት ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው እያወሩ ይመላለሳሉ።

ጆን ባፕቲስት፣ የሚጓዙበትን አቅጣጫ ካርታ በአእምሮው ለመመዝገብ ሞከሮ ተወው። በመጨረሻም ሦስት ጠባብ መንገዶች የሚገናኙበት አንድ አነስተኛ አደባባይ ዘንድ ደረሱ። በአደባባዩ አንድ ወገን በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ እንደሚገኙት ሁሉ ሁለት ካሬ ሜትር የማይሆኑት መስኮቶች በብረት ግሪል እንደሚሸፈኑባቸው ያለ ሻይ ቤት አለ። ወደ ውስጥ ዘልቀው ሲገቡ ቤቱ ሰው የለበትም። ወለሉና ግድግዳው፣ ዙሪያን ከአፈር የተሰሩት የመደብ መቀመጫዎች ቡትት ያሉ ቀይና ሰማያዊ ስጋጃዎች ለብሰዋል። አንዲት ትንሽ የዘይት ፋኖስ፣ በአንደ የመዳብ ሣህን ላይ ተቀምጣ ሞቃት ግለቷን ታሠራጫለች። በክፍሉ ጀርባ፣ ጨለማ ውስጥ ተቀምጦ የነበረው ሰው እነርሱ ሲገቡ ብድግ አለ። ፖንሴም በቅልጥፍና እጁን ወገቡ ላይ በታጠቀው የጐራዴ እጀታ ላይ አሣረፈ።

«ወዳጄ» አለ ሰውዬው

ፖንሴ፣ በረዶ ሆነ። በጨለማው ውስጥ በአስፈሪ ሁኔታ የሚንቀሳቀሰውን ረዥም ሰው ተመለከተው።

«ይህን ድምፅ አውቀዋለሁ . . . »

እንግዳው ቀርቦ፣ በጭንቅላቱ ላይ የነበረውን ፈትቶ፣ በጠረጴዛው ላይ ባለው ብርሃን እንዲታይ ሲል ቆመ።

«ሜትር ዠረሚ!» አሉ ጀስዊቱ

የጓደኛውን ድምፅ ወዲያውኑ የለየው ጆን ባፕቲስት፣ ዘሎ ክንዶቹን እቅፍ አደረጋቸው። በደስታ ፖኸት አሰሙ።

ፖንሴ፣ ከጥንት ጓደኛው ጋር ዳግም በመገናኘቱ እጅግ ተደሰተ። የሴፍ፣ እምብዛም ጓደኛ ሊሆኑ ስለማይችሉ ከእንግዲህ በኋላ ብቸኛ አይሆንም። ሜትር ዠረሚ፣ ለሁሉም ቡና አዘዙና ሲጨርሱ፣ ከኪሱ ውስጥ የያዙትን አነስተኛ ጠርሙስ አውጥቶ ነጣ ያለ ፈሳሽ ቀዳላቸው። ዳግም በመገናኘታቸው ስለጤንነታቸው ጠጡ።

«ግመል ጋላቢው የተባልከው ፈረንሣዊ ለካ አንተ ነበርክ ስትከተለን የነበርከው?» አለ ጆን ባፕቲስት



«ግብፅ ውስጥ እስካለን ድረስ ራሴን ማሣወቅ አልችልም። ሣልፈልግ ቀርቼ እንዳልሆነ ግን እመነኝ»

ዐይኖቻቸው ደካማውን የፋኖስ መብራት ስለተለማመደ፣ ፖንሴ በጓደኛው ላይ የሚስተዋለውን የመልክ ለውጥ ተመለከተ። ፊቱ በጣም ከስቷል፣ አይኖቹም ጉድጓዳቸው ገብተዋል።

«እዚህ ከደረስኩ በኋላ አንተ ከአገረ ገዥው ጋር ጉዳይህን እንድትፈፅምና ከዚያ በኋላ ከመልቀቅህ በፊት ራሴን ሳጋልጥ ፈለግሁ። እናም ምን ታስባለህ? ቅፍለቱን መቀላቀል ያስቸግረኝ ይሆን?»

«እስቲ እየዋለሁ። አሁን ዳግም ተገናኘን፣ እንግዲህ መለያየት የለብንም» አለ ፖንሴ።

ሁሉም የራሣቸውን አስደሣች ገጠመኞቻቸውንና ምሬቶቻቸውን ተጨዋወቱ። ሜትር ዠረሚ፣ ብርጭቆዎቻቸውን ለሁለተኛ ጊዜ ሞላው። የተቀዳላቸውን በአንድ ትንፋሽ ጨልጠው፣ መሣቅና መቃለድ ቀጠሉ።

«ስለንብህ ሁሉ ልትነግረኝ ይገባሃል? ለመሆኑ ተከትለኸኝ ለመምጣት የወሰንከው መቼ ነው? ከዚያም በላይ እንዴት መደበቅና መቆየት ቻልክ?»

ሜትር ዠረሚ ከመጠጡ በዛ አድርጐ ሣበና ለቀረበው ጥያቄ ፈጥኖ መልስ እንደሚሰጥ እጁን በማወዛወዝ ገለፀ። ነገር ግን እስከአሁን ፀጥ ብለው የነበሩት ጀስዊት፣ ከፍተኛ ድምፅ በማሰማት በድንገት ጣልቃ ገቡ።

«ይቅርታ አድርግልኝና የዚህ ሰው ከኛ ጋር መገኘት ከስምምነታችን ጋር የሚጣጣም እንዳልሆነ አምናለሁ»

የተለመደው የአዛኝነት ቅላጼያቸው የተመለሰ ይመስላል። እስከአሁን ድረስ እንደታዛዥ አሽከር ያከናወኑ እንደነበር አይደሉም። ሜትር ዠረሚ የሰውዬውን መኖር የተገነዘበው ይሄኔ ነበር።

«ይህ አሮጌ ቁራ፣ ከኛ ምን ይፈልጋል?» ሲል አባ ብሬቬደንትን በግልፅ ጥላቻ እየተመለከተ ተናገረ።

«እዚህ ያለው» ቄሱ ቀጠሉ «በንጉሡ ትዕዛዝና በቅድስተ ቅዱሳን ሊቀጳጳሱ አመራር ነው። ይህ ተልዕኮ የኛና የኛ ብቻ ሃላፊነት ነው። ከመነሣታችን በፊትም፣ ቆንሲሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተናግረዋል። ኤምባሲያችንን ሌላ . . . ማንነቱ . . . የሚደባለቅበት አንዳችም ጥያቄ እንደማይኖር . . . »

ሜትር ዠረሚ ፊቱ እጅግ አስፈሪ አስተያየት በማንፀባረቁ፣ ጀስዊቱ የጀመሩትን ዐረፍተ ነገር የመጨረስ ብርታት አጡ።

«አፉን እንዲዘጋ ንገረው። አሰበለዚያ ጭንቅላቱን ነው የምፈረክሰለት» ሲል ሜትር ዠረሚ በነጎድጓድ ድምፅ አምባርቆ የመደቡን ጠረጴዛ ደጋግሞ በሃይል መታው። ድምፁ እንደብረት ማህን መሰባበር ዓይነት በመሆኑ፣ የሻይ ቤቱን ባለቤት ሮጦ እንዲመጣ አደረገው።

ጀስዊቱ፣ እስከአሁን በርጋታ ባለውና ቀይቶ ለጉዳዩ ውሳኔ በሚሰጠው ጆን ባፕቲስት ላይ ጥቃታቸውን ከፈቱ።

«ሙሴ ፖንሴ፣ አክብረህ ልትጠብቀው የሚገባህ ግዴታ ገብተሃል። ምንም ያህል ርቀት የተጓዝን ብንሆንም፣ በመጨረሻው መመለሳችን አይቀርም። ስለዚህ፣ የምንሰራቸውን ሁሉ በኋላ ላይ ማሣመን መቻል ይኖርብናል። ይህን ሰው ከኛ ጋር ይዘነው ብንሄድ፣ አንተ ማታውቀው እንደተቀሳቀስን አድርጎ ማን ያምንሃል። እንዲያውም፣ አንተ ያቀድከው ነው ብለው ይናገሩብሃል» ሜትር ዠረሚ ጮኸና ጉራዴውን መዘዘ።

«ይህንን አይጥ ሁለት ቦታ እሰነጥቀዋለሁ» ሲል አጓርቶ ወደ ጀስዊቱ ተንደረደረ።

ፖንሴ በሁለቱ መካከል ገባ። ፖኹቱ ቀሰጠ። በሁለቱ ፈረንሣውያን መካከል የተፈጠረውን ያልተለመደ የፀብ ትዕይንት ለመመልከት አላፊ አግዳሚው ወደ መስኮቱ መኮልከል ጀመረ። ጆን ባፕቲስት፣ ፀቡን ለማብረድና ከጓደኛው እጅ መሣሪያውን ለመውሰድ ቻለ። ጓደኛውን ወደ ክፍሉ መጨረሻ ገፍቶ ከወሰደው በኋላ ወደ አባ ብሬቬደንት ዞረ።



«ዙሪያ ገባው ሁሉ ገደል የሆነበት ጓደኛዬን ልተወው አንዳችም ቃል አልገባሁም። ከዚህ ሰው እዚህ መምጣት ጋር እኔ አንዳችም ጉዳይ እንደሌለኝ ሊያወቁት ይገባል። ነገር ግን፣ ከእንግዲህ በኋላ ይህ ሰው ከኛ ጋር የመቆየቱን ሃላፊት እኔ እወስደዋለሁ።»

ሜትር ዠረሚን እጁን ይዞ እየጐተተው፣ ዮሴፍንም ከፊት ለፊቱ አስቀድሞ እየገፋቸው፣ ጆን ባፕቲስት ወደበሩ አመራ።

«በሉ፣ አስፈላጊ የሆኑ ወረቀቶችን ለማዘጋጀት፣ አሁኑኑ ወደ አገሬ ገዢው ዘንድ እንሂድ?» አላቸው።

የተሰበሰበውን ሕዝብ፣ በሻይ ቤቱ በር ላይ ከሁለት ከፍሎው ጨለማ በዋጠው መንገድ፣ በቅድሙ ትንሽ መልዕክተኛ ልጅ መሪነት ወደመጠብት ተመሰሱ።

ፖንሴ፣ ትንሺን ሴት ልጁን ስለአዳነለት አገሬ ገዥው ውለታ አሰበትና ለዚህ ፈረንሣዊ ውለታ መመለስን እምቢ አይልም። በዚህ መሠረት ሜርት ዠረሚን ብቁ መሆኑን በመመስከር፣ ለሲናር ንጉሥና ለኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ደብዳቤ ፃፈለት። ሁለቱ ፈረንሣውያን፣ በሌላ ሦስተኛ አካል እንደገና መጠናከራቸውን ሃጂ አሊ ደስ ሳይለው ቢከታተለውም፣ በዚህ ላይ ቅራኔ መፍጠር ከንቱ መሆኑን ተረዳ። አባ ብሬቬዳንትን በተመለከተ እንደገና ተመልሰው ዮሴፍ ስለሆኑ አንዳችም ምክር መለገሳቸውን አቆሙ። የታችኛው ከንፈራቸው መውደቅና የአንገጫቸው እንደገና መርገብ የተለመደውን የትካዜ መልካቸውን አወጡባቸው። ከበፊቱ ይልቅ በጣም ዝምተኛም ሆኑ። ጀስዊቱ፣ ከዚህ በፊት ካሣዩት አነስተኛ ግቡቡነት ባሻገር፣ ለውዬው ሁለቱ ጓደኛሞች እንደገና በመገናኘታቸው ብቻ ቅናት ያለባቸው አልመሰል አለው።

በማንኛውም ደረጃ፣ እኒህ አገልጋይ፣ ፕሮቴስታንቱ ቅፍለቱን በመደባለቁ ተጠቅመዋል። ዠረሚ ያመጣቸው ሁለት ግመሎች አሉ። ለአገሬ ገዥውም ያቀረቡት ስጦታ ከጭነቱ ላይ ተቀንሷል። ስለዚህ እርሣቸው ከዚህ በኋላ በእግር አይጓዙም።

የሜትር ዠረሚ መድረስ ለራሱ ለፖንሴና ለጓደኛው ጥቅም ሲባል የተሠራ ትያትር እንደሆነ ቄሱ ማመናቸውን ቀጠሉ። በርግጥ እውነቱን መደበቅ አይቻልም። ቅፍለቱ በአዝጋሚ ጉዞው ወደፊት በሚንቀረፈፍበት ጊዜ ሁለቱ ጓደኛሞች በቅርብ የነበራቸውን

እያንዳንዱን ተግባራቸውን ያወሩ ነበር። ሜትር ዠረሚ፣ ጓደኛው ብቻውን ብዙ ችግሮችን እንዲጋፈጥ ስለተወው ፀፀት ተሰምቶታል። በዚህም ሳቢያ ቅፍለቱን ለመደባለቅ ከጅምሩ ላይ ወስኖ ነበር። ነገር ግን፣ ከቆንሲሉ ጋር ነገሮች እንዳይወሳሰቡና ችግር እንዳይፈጠር ለመከላከል፣ ጆን ባፕቲስትም ሃሰት እንዳይናገር ለመጠበቅ በማሰት ሜትር ዠረሚ፣ ድርጊቱን አጥብቆ ቢጠላውም፣ አንዳችም ነገር ሣይተነፍስ፣ ዘማቹ ግብዕን ሲያልፍ ሲቀሳቀል ወሰነ።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ በቅርባቸው ተደብቆ ስለነበረው አስገራሚ ፈረንሣዊ ፍንጭ ቢኖረውም፣ እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ግን በርግጠኝነት ማን መሆኑን አያውቅም ነበር።

ጓደኛው፣ ጉዞ ከጀመረ በኋላ፣ ሜትር ዠረሚ አንድ ቀን አድሮ ስለነበረ፣ ስለካይሮ አወሩ። ቤቱን ለቅቆ የወጣው፣ ጋሪው አሊስንና አባ ጋቦሪን አድርሶ፣ ተመልሶ ዋናው መንገድ ውስጥ ሲገባ መሆኑን ነገረው።

«ደብዳቤዬን እንደተቀበለች እርግጠኛ ነህ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀው።



# 5

ከዚህ በኋላ ለመነኩሴው የታዘዘላቸው መድሃኒት ምን እንደሆነ አወቀች። አባ ጋቦሪ፣ መጠኑን ከፍ እንዲያደርጉ ለመገፋፋትም ፈጠነች። በዚህ ዕለት በመድሃኒት መቀመሚያው ቤት ከመድረሣቸው፣ አንድ ትልቅ ብርጭቆ ሙሉ በአንድ ትንፋሽ እንዲጨልጡ አደረገቻቸው። ቁሱ፣ አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ እንቅልፍ ወሰዳቸው። በመጀመሪያው ማንኮራፋት፣ ዘልላ ወደ እርከኑ በመሄድ በተዘጋው መስኮት በኩል ተጣራች።

«ፍራንቾይዝ! መምጣት ትችያለሽ!»

መጋረጃዎቹ በፍጥነት ተከፍተው፣ ፍራንቾይዝ እርከኑ ላይ ወዳለችው ልጃገረድ ወርዳ መጣች። በጥግ በኩል ሁለት ወንበሮች አድርገው ጐን ለጐን ተቀመጡ።

«እና?» ስትል ፍራንቾይዝ ጠየቀቻት። «ትናንት የሰጠሁሽ ደብዳቤ አስደሰተሽ?»

አሊስ አፈረች። እንዲህ በርህራሄ የምትመለከታትን ሴት የማታውቃት ቢሆንም፣ በደመነፍስ ብቻ አመነቻት። የማለዳው ሰዓቶች ማብቂያ የሌላቸው ይመስላሉ። እንዲህ ልትረዳት ለምትችል ሴት ምስጢሯን ሁሉ ጐልጉላ ለመናገር ትዕግስት አጥታ ተቃጠለች።

«ይኸውልሽ» አለቻት ወረቀቱን ለጓደኛዋ እያሳየቻት። «ራስሽ አንብቢው።» በጆን ባፕቲስት የእጅ ፅሁፍ የተሞሉትን ሁለት ገፆች ፍራንቾይዝ ተቀብላ የሚከተለውን አነበበች።

ለተወዳጇ አሊስ፣

*የምፅፍልሽ በጣም እየተቻኮልኩና በአንድ ሻንጣ ላይ ተቀምጬ ነው። ኢቃዎቼ ሁሉ በዙሪያዬ በትንትን እንዳሉ ናቸው። አዕምሮዬ፣ ለጉዞው በሚያስፈልጉ አንድ ሺህ ትንንሽ ጥንቃቄዎች ጭንቀት ተሞልቷል። በርግጥ፣ ውስጣዊ ስሜቴን ይህ ሊገልፅልኝ አይችልም። ይሁንና፣ በዚህ ሰዓት፣ የኔ የሆኑት ሁሉ በግልፅ ይታወቁኛል። በነዚህ የኔዎች በምላቸው ነገሮች ምክንያት ያቀድኩትም በጣም ትክክል ነው። እነዚህን ነገሮች ስወስናቸው ቢሣራ አልጠብቅም። እነዚህን ውሳኔዎች ለመስማት ባልተዘጋጀሽባቸው*

ለዓቶች እንዲነገሩ በማቅረቤ በጣም ፈርቻለሁ:: በዚህ ምክንያት ይህ ደብዳቤ ጥቂት ዘግይቶ እንዲደርስሽ ጥንቃቄ ወስጃለሁ:: ለዚህም፣ እባክሽ ይቅር በይኝ:: እነዚህን መስመሮች ስታነቢ እቤቴ መጥተሽ፣ እንደ ቤትሽ እየተሰማሽ ነው:: የምወዳቸው ተክሎቼ በዙሪያሽ ናቸው:: ፍራንቾይዝንም አግኝተሽታል:: እርሷ በአንች ላይ ከፍተኛ እምነት አላት:: ይህም ይገባታል:: እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ሆነው፣ ከአንቺ ጋር መነጋገሩን ቀለል ያደርጉልኛል:: ምንም እንኳ አንድ ላይ ባንሆንም፣ አንድ ቦታን እንጋራለን:: እንድንገናኝ ሊረዱን የሚችሉ ወዳጆች አሉን:: በጣም ቅርብ ለቅርብ በነበርንበት ጊዜ፣ እንዳንገናኝ ከሚያራርቁን ነገሮች አሁን በርግጥ የቦታ ርቀት ነፃ ሳላደረገን፣ ከመቼውም በበለጠ አንዳችን ለአንዳችን ቅርብ ነን::

በርቀት መገናኘቱ እንደመከላከያ ስለሚሆነን ምን እንደሚሰማኝ ለመናገር ብዙም አልፈራም:: ባለፉት ጊዜያት ይህን ለማድረግና ለመደፈር አልፈለግሁም:: ሁኔታዎች ሁሉ አላመቹኝም ነበር:: ይሁን እንጂ ለሌሎች በምናገርና በምመልስበት ጊዜ የማናግረው አንችን ነበር:: ሌሎችን የማያቸው በምመስልበት ጊዜ የምመለከተው አንችን ነበር:: በሁለመናዬና በሃሳቤ ውስጥ አንች ነበርሽ::

ሁሉንም ደረጃ እንዳናስታውስ እርስ በርሳችን ከተዋወቅን በጣም አጭር ጊዜ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ በክሣሊጅ ድልድይ ላይ ካየሁሽ ቅፅበት ጀምሮ በውበትሽና በተከለ ሰውነትሽ ተማርኬያለሁ:: ቀርቤ ላይሽ ከቻልኩበትና የአይን ዕይታ ከተለዋወጥንበት ጊዜ ጀምሮ ያ የመጀመሪያው ስሜቴ ይበልጥ መጠንከር ጀመረ:: ራሴን በደስታ ከማስማረኬ በፊት እንዲህ ያለ ጠንካራ ስሜት ኖሮኝ ስለማላውቅ በመጀመሪያው ላይ ተጨንቄ ነበር:: እንዲያውም ተናድጄ ነበር:: ባንች ላይ ያለውን የደስደስ ሁሉ ለመግለፅ በቂ ጊዜ በኖረኝ ምንኛ በተደሰትኩ:: ገለፃዬንም የወረቀቶች ክምርም ቢሆን ሊሸከመው አይችልም:: እያንዳንዱን ያንችን ጥራት ለመግለፅ ትርፍ ጊዜ ስለሌለኝ ንቁ የተውኳቸው እንዳይመስልሽ፣ ምንም ላለማለት መረጥኩ:: ውድ አሊስ፣ አንችንና ያየሁብሽን ሁሉ አመልካለሁ:: እስካሁን ሸሽገሽው በበርታት የያዝሽውንና በቅርቡ የሚታየውን ጥንካሬሽን በፍቅር እንደምወደው እገልፅልሻለሁ::



ርቀሽ በመሄድ ላይ እያለሁ ይህን ሁሉ ለምን እነግርሻለሁ? ስሜቶቼ በርግጥ ጠንካሮች ቢሆኑ ኖሮ፣ ካንች የማልለይበትን ምክንያት ለምን አይሰጡኝም ነበር? መሄዱን የመግለፄስ ጥሩነቱ ምኑ ላይ ነው? ባለፉት ቀናት በአዕምሮዬ የሚጉላሉት ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው:: እነዚህ ደግሞ ይበልጥ ያባስጉኛል:: ምክንያቱም፣ በህይወቴ ውስጥ ለሃዘንና ለትካዜ አንዲት ቅንጣት ቦታ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለሁም:: እያንዳንዱን ነገር በአዕምሮዬ ውስጥ ያለፍርሃት ሳመላልስ፣ ሁኔታውን በተለየ መልክ ለማየት ቻልኩ:: በዚህም የተነሣ መለየቱ ጥሩ አጋጣሚ ይመስለኛል:: አዎን፣ አሊስ፣ በትክክል አንዛበበሽኛል፣ እኔም ላሳምንሽ እሻለሁ:: ይህ ጉዞ ለሁለታችንም ታላቅ እድላችን ነው:: ካይሮ የምቆይ ብሆን ኖሮ፣ በሁለታችንም መካከል አንዳችም የሚሆን ነገር አይኖርም ነበር:: ከፊት ለፊቴ የሚደቀንብኝ ፈተና ቢኖርና እኔም የሚሣካልኝ ቢሆን ተስፋ የማላደርገው ነገር አይኖርም ነበር:: ድሉ ወደ አንቺ አንሳፎኝ፣ ሊሆን ያደርሠኛል:: ፈቃድሽ ከሆነ ነፃና እኩል አድርጊኝ:: ይህን ተልዕኮ ለማሣካት ቃልኪዳን የገባሁት ላንችና ለአንች ብቻ ነው:: በኔና በዓላማዬ መካከል ሊመጣ የሚችለውን ማንኛውንም እንቅፋት ድል ለማድረግ ብርታት ይሰማኛል:: ካንቺ እየራቁ የሚወስደኝ እያንዳንዱ እርምጃ ይበልጥ ወደ አንቺ ያስጠጋኛል:: ተስማምቼ የተቀበልኩት ሃላፊነት ስለሚያስከትለው ውጤት ምንም ጥርጣሬ የለኝም:: እመለሳለሁ:: ብቸኛው ተስፋዬ ግን፣ ልትጠብቂኝ የሚያስችልሽ በቂ ትዕግስት ይኖርሻል የሚል ነው:: አሊስ! ይህን ደብዳቤ እያነበብሽ ባለሽበት ጊዜ አሁን በምንዘባቸው አገሮች ውስጥ ሆኜ ከኔ ጋር መገናኘት ካልቻልሽ፣ ልትታይኝ አለመቻልሽን ማወቅ ይኖርብሻል:: አሁንም አጅበሽኝ ያለሽ እየመሰለኝ ያልተቋረጠ ደስታ ይሰማኛል::

እዚህ ህግ በማይገዛቸው በምድረበዳው ጉዳናዎች ውስጥ ሙጭጭ አድርጌ እየሣምኩሽ ነው::

«ደግ!» አለች አሊስ ደብዳቤውን አንብባ ስትጨርስ

«ብዙ ግራ የሚያጋባ፣ ረዥምና ሊሆን ከሚገባው በላይ የተወሳሰበ ቢሆንም፣ እንደሚያፈቅርሽ የሚገልፅ ነው»

«ማን» አለች ልጃገረዲቷ ተረብሻ «ይህ ሰው እምብዛም አግኝቶኝ አያውቅም። ጭራሽ አልተገናኘንም . . . »

«እንዳንቺ ከሆነ ታዲያ ሰዎች እንዴት ነው በፍቅር የሚወድቁት? ከማይወዱት ጋር በየዕለቱ ብዙ ሰዓቶችን አብረው መቆየት ነው?»

«የለም በእርግጥ እንደዚያ አይደለም። ነገር ግን ከልቡ መሆኑን እንዴት ማወቅ ትችያለሽ?»

አሊስ ከባለፈው ምሽት በፊት የተጋፈጠችውን ሃሣብ አውጥታ ለመናገር፣ የሚያስታውቅ ጥረት ታደርጋለች።

«አገር ለቅቆ በጉዞ ላይ የሚገኝ ሰው፣ እንዲህ ያለ ውሸት ለመናገር ምክንያት አይኖረውም» አለች ፍራንቾይዝ

«ምናልባት ደብዳቤውን የፃፈው የኔን ፍላጐት ለመቀስቀስ ይሆናል ወይም ትዝታ ይዞት ይሆናል። ወይም ለጉራም ይሆናል። ሆነም ቀረም እንድጠብቀው መጠየቁ ምንም አይጐዳውም»

«ለአፍታ እንኳ ይህን ታምኛለሽ?» ፍራንቾይዝ ጠየቀች

ወጣቷ ልጃገረድ ዓይኖቿን ሰበረችና ከስተር ብላ በጥንቃቄ አሰበች። የእንባ ዘለላዎች ጉንጮችዋ ላይ ቁልቁል ወረዱ።

«በእርግጥ አላምንም» አለች «ራሴን በተቃራኒው ለማሳመን እየሞከርኩ ነው እንጅ እያንዳንዱ እኔነቴ ልክ እኔ እንደማፈቅረው እርሱም እንደሚያፈቅረኝ ይነግረኛል።»

«በቀላሉ ይህን መቀበል መጥፎ ይሆናል?»

«ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ» አለች ወጣቷ ልጃገረድ ሃሳቧ ውሣኔ ላይ እንዲደርስ እየሞከረች።«የፈለገው ቢሆን እንኳ አዝናለሁ»



«ይህስ ቢሆን ለምን ይሆናል» አለች ፍራንቾይዝ

«እስቲ አስቢው» አለች አሊስ ጉላ ባለ ድምፅ፣እንባ የቋጠሩ ዓይኖችዋን ወደ ጓደኛዋ መልሳ። «ከጉዞው ሣይመለስ ቢቀር ለዘላለም ልቤ እንደተሰበረ ሲቀር ነው። ከተመለሠ ደግሞ . . . »

«ከሁለት አንዱ ሊሆን ይችላል። እርሱም ያለው ይህንኑ ነው»

«አባቴን አታውቂውም አይደል?!»

ምን አይነት ልጅ ነች! ስትል ፍራንቾይዝ አሰበችና ተንቀሳቀሰች «ጉና እሩቅ ያለ ነገር ትመለከቻለሽ?» አለቻት ረጋ ብላ። «እስኪመለስ ድረስ ብቻ ጠብቂው። ለሌላው ነገር ሁሉ እመኚው። የማይታወቅን ግዛተ ዘውድ በሮች ለማስከፈት የሚችል፣ የአካባቢውን ተወላጅ መሣፍንት እመኔታ የሚያገኝ፣ የፈረንሣይን ንጉስና የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱን ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ የሚችል ሰው፣ አንድን መንቻካ አባት ማግባባትና ማሣመን የሚችል ሊሆን ይችላል።»

ልንሰማው የምንፈልገውን በታማኝነት ለሚገልፁልን ሰዎች ፣ ቶጥበን እንደምናቆይላቸው ፍቅርና የእምቢተኝነት ስሜት፣አሊስ፣ ድብልቅልቅ ባለ ርህራሄ ተመለከተቻት።

«በየዕለቱ ጧት ጧት ነይና እንጫወታለን። ጊዜውም ፈጥኖ ያልፋል» አለች ፍራንቾይዝ።

ከዚህ በኋላ ወጣቷን ልጃገረድ በክንዶችዋ ውስጥ ይዛት ፀጉሯን በማሻሸት ትንሽ እንድታሰቅስ አደረገቻት።

ሴናር እስኪደርሱ ድረስ ሁሉም ነገር በሰላም ተካሂዷል። ቅፍለቱ፣ ከተማ የደረሰው በባዩዳ ምድረበዳ አስር ቀን ሙሉ ከተጓዘ በኋላ ነው። ጉዟቸው ወደ ደቡብ አቅጣጫ በቀጠለ

ቁጥር ቀስ በቀስ ሣር ቅጠል መታየት ጀመረ። አረቦች፣ ራህማት አላህ «የእግዚአብሔር ምህረት» እያሉ የሚጠሩት አገር ገብተዋል። የእግዚአብሔር ምህረት፣ በዚህ ቦታ ላይ መቀመጡ የሚታየው፣ እንደ ዶንጎሎ ሰዎች መሬታቸውን በመስኖ ማልማት የለባቸውም። መሬቱ የሚለማው በዝናብ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ አረንጓዴ የግጦሽ መስኮች፣ መካከለኛ ቁመት ያላቸው ዛፎችና እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ደን ይታያል። ለመስኮታዊው ችሮታው ምስጋና ይግባውና፣ ገበሬዎች የተወሰነ ትርፍ ጊዜ ኖሯቸው ከአህዮቻቸው ጋ ን እየዘመሩና እየዘፈኑ ይጓዛሉ።

ዋና ከተማዋ ሲናር፣ በጥቁር አባይ ዳር የተመሠረተች ናት። ጥቁር አባይ፣ ከአቢሲኒያ ተራሮች ቁልቁል ሲምዘገዘግ፣ ውሃው በደቃቅ አፈር ደፍርሶና ከብዶ ነው። ሲናር፣ ታላቅ የንግድና የግብርና ከተማ ስትሆን፣ በደማቅ የባዛር ትርኢቶች፣ በውብ መስጊዶችና ለንጉሡና ለቤተመንግስቱ በቋሚ መኖሪያነት በሚያገለግል ድንቅ ቤተመንግስት የተዋበች ነች። ሁለመናዋ በድንጋይ የታነፀ ሲሆን፣ በቀይ ሸክላ ተለስናለች።

በምድረ በዳው የመጨረሻ ክፍል ላይ ጉዞው ያላንዳች ግጭት አልፏል። ዳግም ሲገናኙ ከተፈጠረው ደስታ በኋላ፣ ሜትር ዠረሚ ወደተለመደው ጋግርታምነቱና ብስጦነቱ ጉብቷል። ከጆሰዊቱ ጋር የመሳሪያ ፍልሚያ ላለማድረግ ተስማምተዋል። አንዳቸው ሌላቸውን ለመሸሽ ሲሉ የሚናገሩት ሁሉ ለፖንሴ ብቻ ነው። ፖንሴ ደግሞ ሁለቱን ሰዎች ለመሸምገልና ለማስታረቅ በማያመችው ሁኔታ ላይ ሆነ። የዮሴፍን ሁኔታ እንቀበለው ካልን ከሁሉም ይልቅ ፍፁም ደስ የማይል ነበር። በሌላ በኩል፣ ጠላቱ፣ ራሱን እንደ ጌታ እዩኝ እያለ ነው። እርሱ ደግሞ የትሁት አሽከርን ሚና በማከናወን፣ በመጫን፣ በማራገፍ፣ በያንዳንዱ ማረፊያ ምግብ በማዘጋጀትና የውሃ መያዣ ቀርበታዎችን መሙላት ይገደዳል። ከዚህም በላይ ሃጅ አሊም ትዕዛዞችን ይሰጠው ጀመር። ትዕዛዝ እንዳይሰጥ ፖንሴ ጠይቆት ነበር። ነገር ግን፣ በዚህ ጊዜ በባዕድ አገር ውስጥ በመሆናቸው፣ ግመል ነጂው፣ ለፈረንሣውያኑ የነበረውን ፍርሃት ሁሉ ርግፍ አድርጐ ጥሎታል። ለጆን ባፕቲስት ካለው ግልፅ አክብሮት ባሻገር፣ በየአጋጣሚው ሁሉ ትንሽ ገንዘብ እያስከፈለው፣ በመጨረሻ ላይ ትልቅ ወጭ እንዲሆን አድርጓል። በባዕድ ምድረ በዳ መሃል ላይ ለአፍታ ቆም እንዳሉ፣ ሃጅ አሊ፣ በአዲስ አይነት ዘዴ አስፈራርቶ ገንዘብ ሊቀበል ሞከረ። አሸዋ ያቀላውን ዓይኑን ብቻ ማሣየት እንዲችል በማድረግ፣ ፊቱን በጥምጣሙ ግጥም አድርጐ ከሸፈነው ከሃሰን አልቢል ቤሲ ጋር መጣ።



«በሁለት ቀን ውስጥ፣ ጉራዕ፣ የፈንጣጣ ምርመራ የሚደረግበት ቦታ እንደርሳለን።» አለ ሃጂ አሊ።

በሽታን አጥብቆ የሚፈራው የሲናር ንጉስ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ በሽተኛ ተጓዦችን ላለማስገባት በድንበሩ ላይ የተገለለ ቦታ አዘጋጅቷል። ሲል ገለፀ።

«ሃሰን የኬላውን አዛዥ እንደሚያውቀው ይናገራል፣ ይህ ሰው አረቦችን እንዲያልፉ ይፈቅድላቸዋል። እናንተን ግን ማሣለፉን ይጠራጠራል። በዚህ የተነሣ እናንተን እዚያው ትተናችሁ ልንጓዝ ነው። በስተቀር . . . » ሲል ሃጂ ቀጠለ

«በስተቀር ምን?»

«በስተቀር፣ የዚህን ነገር ሠሪ አስተሣሰብ፣ የሚለውን ነገር ካልሰጣችሁን» ሃጅ አሊ ከመጠን በላይ የሆነ ገንዘብ ጠራ። ይህን ከተናገረ በኋላ ግመል ነጂው አፀፋዊውን ሃሣብ በዘፈንና በዳንስ ዘዴ ለሃሰን አል ቢልቢሲ አስረዳው። ሃሰን አል ቢልቤሲ፣ በበኩሉ በግትር እምቢተኛነት አለመስማማቱን ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ይገልጽለታል። ብሎ ብሎ ዋጋው ዝቅ አለ። ይህን ለመክፈል ግድ ሆነባቸው። ከሁለት ቀናት በኋላ በወሰን ኬላው ላይ ሲደርሱ፣ ቦታውን እና ሆኖ አገኙት። የወረርሽኝ ፍርሃት በግልፅ በመወገዱ፣ የተገለለው ቦታ ተነስቷል። ሃጂ አሊና ሃሰን ገንዘቡን ተካፍለው ስለነበር ሊመልሱ አልቻሉም።

ሲናር ላይ ነገሮች በመልካም ሁኔታ ተጀመሩ። ለንጉሡ ደብዳቤአቸውንና ገፀ በረከታቸውን ለማቅረብ በቀጥታ ወደ ቤተመንግስት ሄዱ። ልክ ደንጐሎ እንደሆነው ሁሉ፣ የጆን ባፕቲስትን ሐኪም መሆን ንጉሡ ስላወቀ፣ እንደ ዘመዱን እንዲያክምለት ጠየቀው። ከዚህ በኋላ ነገሮች ሁሉ መበላሸት ጀመሩ።

ንጉሡ፣ ከዙፋን ክፍሉ በስተጀርባ በምትገኝ ክፍል ውስጥ፣ ፖንሴንና የድጋፍ ደብዳቤው መድሃኒት ቀማሚ መሆኑን የሚመሰክርለትን ሜትር ዠረሚን ጠራቸው። እሄው፣ ቀጭንና ተልባሩ ነው። ቆዳው፣ እንደ ከሰል አመድማ ነው። ብዙ አሥቃቂ ተግባር እንዲፈፅሙ ያዘዘና እንዲያውም እርሱ በፈለገበት በማንኛውም ጊዜ እጅግ የከፋ ዘግናኝ ቅጣት እንዲፈፅም የሚያገዙ ትንንሽቹ ዓይኖቹ ጭካኔ የተሞሉና ዕረፍት የለሽ ናቸው። ለምክክሩ ሃጅ አሊ አልተጠራም። ንጉሡ፣ ሁኔታውን ፖንሴና ዠረሚ በሚገባ በሚረዱት አረብኛ ያስረዳቸዋል።

አንድ ዘብ፣ ምናልባት ከአስራ አራት ዓመት የማይበልጠው፣ ቁመቱ ግን ከሁለቱም ፈረንሣውያን የሚረዝም ጉረምሣ፣ አስከትሎ ገባ። በንጉሡ ትዕዛዝ ይህ ወጣት በሽተኛ፣ በወርቅ የተዘመዘመውን ጥቁር ጃኬቱን አውልቆ፣ እጅግ ያልተለመደ ቀጭን ሰውነቱን አሣየ። የማርሽ ጥርሶቹ እንደሚታይበት መሣሪያ፣ የዚህም ልጅ ጡንቻዎች በስሱ የቆዳው ሽፋን ስር ይታያሉ። ሆዱ ክፉኛ ተወጥሮ፣ እምብርቱ በሃይል ወደ ውጭ ወጥቶ፣ አንገቱ የጫጉት አንገት ይመስላል። በጣም የሚገርመው፣ ልጁ ከሚገባው በላይ ከመቅጠኑ በስተቀር በጥሩ ጤንነት ላይ ይመስላል።

«ይህ የሶስተኛዋ ሚስቴ ልጅ ነው። ምን እንዳለበት አናውቅም። የበላው ሁሉ እንዳለ ይወጣል። ነጭ ማሽላ ቢበላ ነጭ ማሽላ ይወጣል። ቀይ ማሽላ ቢበላ፣ ቀይ ማሽላ ይወጣል። ሥጋ ቢበላ፣ ሥጋ ይወጣል» አለ ንጉሡ

ሐኪሞቹ የሚሰጡትን አስተያየት ለመስማት ጠበቀ።

«ምን ይመስልሃል?» ሲል ፖንሴ ጓደኛውን ጠየቀው።

በዚያን ማለዳ ከዮሴፍ ጋር የተጨቃጨቀው ሚትር ዠረሚ ግልፍቱ አልበረደለትም ነበር።

«ቀላል ነው» አለ «ሲፈልገው አበት ይብላ»

ጃን ባፕቲስት እንዲህ ያለ መልስ እሰማለሁ ብሎ አልተዘጋጀም ነበርና ሣቁን ለቀቀው። የሠራውን ስህተት ወዲያውኑ ቢያርምም፣ ጥፋቱ ግን ተፈፅሟል። ንጉሡ፣ እነዚህ ሁለቱ፣ በልጁ ወይም በርሱ ላይ የሚቀልዱ መስሎ ታሰበው። መድሃኒት ቀማሚው፣ ምን እንዳለ ፖንሴ ትርጉሙን እንዲነግረው ንጉሡ ጠየቀው። ፖንሴ፣ ይህ ምንም እንደማያስፈልግ ገልፆ ሌላ ታሪክ ተናገረ። ንጉሡ ግን ቅር እንዳለው ቆየ።

ፖንሴ፣ የንጉሡን ልጅ በጥንቃቄ ተከታተለው። እርሱ ያዘዘለት መድሃኒት ልጁ የበላውን ምግብ እስከሚቀጥለው ዕለት ሳይቀር አቆየለት። ነገር ግን ልክ እንደተሠነጠቀ፣ ግን ጨርሶ እንዳልተሰበረ አንድ ሳህን ያህል ንጉሡ ለነርሱ የነበረው እምነት በመሠረታዊነት ስለተበላሸ ይህን መልሶ የመገንባት ተስፋ ጨርሶ ጠፋ።

በማንኛውም ተራና አዘቦት ጊዜ እምብዛም ጉዳይ የማይባል ነገር ተከሰተ። መሠንጠቁ የማይታይን ነገር ስብራቱ እስካለበት ቦታ ድረስ ለማስፋት ተሞከረ። አባ ብሬቬደንት አደጋውን አፋጠኑት።



ማንነታቸውን የሚጋርደው ፈረንሣዊ መታወቅ ሲጀምር፣ ጀስዊቱ የሆነ እፎይታ ይሠማቸው ጀመር። ምንም እንኳን ካፑቺን ባይሆንም፣ አሁን ድረስ ከፕሮቴስታንት ጋር መጓዛቸው ያስጨንቃቸዋል። ካፑቼኖችንም ገፈታትረው ለመጣል በመቻላቸው፣ ፈጥነው ከካይሮ ለመልቀቃቸው ምስጋና ይግባውና ከተፎካካሪ የሃይማኖት መስመር ሊገጥማቸው ይችል የነበረው አደጋ ማለፉን ራሣቸውን ለማሣመን ችለዋል።

አባ ብሬቬደንት ልበ ሙሉ ስለነበሩ፣ ሲናር ላይ ለሚገኙት ጥቂት መነኮሳት፣ ማህበረሰባቸው ለካፑቼኖች የሠራውን ቤት ለመጐብኘት ሃሳብ አደረባቸው። ፖንሴ፣ አብሯቸው የሚሄድ ከሆነ እንደ ጌታና አሽከር ሆነው ለመሄድ ፈለጉ። በዚህም፣ ሁለቱ ስለአካባቢው መረጃ ለመሠብሠብና መነኮሣቱም፣ አቢሲኒያን በሚመለከት ምን መላ እያዘጋጁ እንደሆነ ለመረዳት ይችላሉ። ፖንሴ ተስማማ። ሁለቱ ሰዎች ወደ ገዳሙ በእግር ጉዞ ሲጀምሩ፣ ሜትር ዠረሚ፣ ከተማው ውስጥ ሃጂ አሊ በተከራየላቸው ቤት ቆየ።

የሙስሊም መንግስት ንጉስ፣ ለካቶሊኮች የሚሆን የእንግዳ ማረፊያ በዋና ከተማ ውስጥ ያፈቅዳል ማለት የሚገርም ቢሆንም፣ መልሱ ግን ቀላል ነው። የንጉሡን ፈቃድ ሲያገኙ ካፑቺኖች ከጳጳሱ ጋር ያደረጓቸውን ክርክሮች ፍፁም ተቃራኒውን ተጠቅመዋል። ሮም በነበሩበት ጊዜ፣ ተልዕኮአቸው፣ ከጀስዊቶች መባረር በኋላ ተሠድደው ሲናር ጥገኝነት የጠየቁትን የካቶሊክ ስደተኞችን ማዳን ነው። ሲናር ውስጥ ግን፣ ሁሉም በሚገባ እንደሚያውቀው፣ ንጉሡም በተለይ እንደሚረዳው፣ እንዲህ ያሉ የካቶሊክ ስደተኞች የሉም። ጀስዊቶች፣ አቢሲኒያ ውስጥ ከንጉሡ በስተቀር ይህም እንኳ ለአጭር ጊዜ ነው፣ አንድም ሰው ወደራሣቸው የሃይማኖት መስመር አልለወጡም። አቢሲኒያ ሲደርሱ እንደነበረው፣ ሲለቅቁም ብቻቸውን ነበሩ። ሲናር ውስጥ ካቶሊኮች ቢኖሩ ኖሮ፣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴን በመፍራት፣ የሶልጣን ጉዳይ ነውና ንጉሡ ሮማዊ ቄስ እንዲመራቸው አይፈቀድላቸውም ነበር።

ስለዚህ አንድም ካቶሊክ ባለመኖሩና ያሉትም ቢሆኑ የሥቃይ ቅጣት እንዳይገጥማቸው አንድም ሙስሊም ሐይማኖቱን ላለማስለወጥ መሃላ ገብተው ነው የሚኖሩት። ታዲያ፣ እነዚህ አባቶች ለማይሞሉ ለላማዊ የውጭ ዜጎች መኖሪያ መፍቀድ ምንም ጉዳት የለውም። ለህፃናት የሚሆን ትምህርት ቤት ከፍተዋል። ለታመሙት ይጠነቀቃሉ። የጳጳሱም ጆሮ ስለማይርቃቸው፣ የሲናር ንጉሥ ከአውሮፓ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ይረዳሉ።

ፖንሴ፣ ዮሴፍ ተከትለውት የገዳሙን የእንጨት በር አልፈው ሰፊ አደባባይ ውስጥ ገቡ፡፡ የተገረዙ የብርቱካን ዛፎች በትልቅ ክብ ቱቦዎች ውስጥ ተተክለው በአቧራማው ቀይ መሬት ላይ ተሰድረዋል፡፡ እንኳን ደህና መጣችሁ ያሏቸው ካፑቺን፣ በጉብኝታቸው ትንሽም መደነቅ አላሣዩም፡፡ እንደሌሎቹ ሁሉ አደባባዩን ቁልጭ አድርጐ ወደሚያሣየው መስኮት የለሽ ክፍል መሯቸው፡፡ በአጫጭር የጠፍር መቀመጫዎች ላይ አረፍ እንዲሉም ጋበዟቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አራት መነኮሣት ተደባለቋቸው፡፡ እንደቅዱስ ፍራንሲስ ይለብሱ የነበረው ልማዳቸው ቀርቶ እዚህ የለበሱት የአረቦችን አለባበስ ይመስላል፡፡ የጠቆረውን ፊታቸውን፣ ጥቁር ፂማቸውንና ከአብሩዚ የመጡ ገበሬዎች የሚያስመስላቸው አጭርና ወፍራም ቁመናቸው ሲታይ፣ በአንገታቸው ዙሪያ ያጠለቁት መስቀል ባይኖር ኖሮ፣ የዚህ የኑቢያ ግዛት ዘውድ ተወላጅ ናቸው ቢባል በቀላሉ ተቀባይ ያገኙ ነበር፡፡

ከመነኮሣቱ አንዱ ራሣቸውን የበላይ አድርገው አስተዋወቁ፡፡ ስማቸውም ራይሞንድ ይባላል፡፡ እንደርሣቸው ተራና የማይማርክ ልብስ የለበሱትን ጓደኞቻቸውንም አስተዋወቁ፡፡ በመቀጠልም ትንሽ ወደኋላ ራቅ ብለው ፖንሴን በጥርጣሬ አይን የሚመለከቱ መነኮሣትን አመለከቷቸው፡፡

«እነዚህ ሁለት ወንድሞች ኑብኚዎች ናቸው፡፡ ትናንት ጧት ነው ከካይሮ እዚህ የደረሱት፡፡»

«ትናንት ጧት!» አለ ፖንሴ፡፡ «በየት በኩል ነው የመጡት? ደንጉላ ላይ ልናያቸው ይገባን ነበር»

«ወደዚህች ከተማ ከአንድ ቅፍለት በላይ ይጓዛል» አሉ ወንድም ራይሞንድ፡፡ «እነርሱ የአባይን ሸለቆ ተከትለው እስከ ሁለተኛው ፏፏቴ ድረስ በመምጣት ከኛ በስተሰሜን ያለውን የአሸዋ ምድረ በዳ አቋረጡ»

«ይህ ያብልጥ ረጅም መንገድ ነው፡፡» አለ ፖንሴ

«እንደወቅቱ ይለያያል፡፡ አባይ በማይጐርፍበት ጊዜ አንድ ጋላቢ በሸለቆው ውስጥ መጓዝ ይችላል፡፡»

ካይሮን መቼ እንደለቀቁ ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው፡፡ ከርሱ በኋላ አስር ቀን ቆይተው መነሣታቸውን አሡሉ፡፡



# 6

ከገዳሙ፣ በሲናር ግላማ ጉዳናዎች ውስጥ ሲመለሱ ዮሴፍ የተባሉት ሠው ራሣቸውን ከፍተኛ ሽብር ውስጥ ከትተው ነበር፡፡ ጉዞ ከመጀመራቸው አንድ ቀን ቀደም ብሉ፣ አባ ቬርሣው የሰጡት ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ፣ በተደጋጋሚ ያደረጉት ቅስቀሣ፣ የካፑቺኖች ተንኮልና ቅን ያልሆነ ሴራ፣ ባልታሰበ መንገድ አሁን እውን እየሆነ መምጣቱን ያሣያል፡፡ ሞቃቱ ለሊት ሊገለፅ በማይችል ስጋት ተዋጠ፡፡ ጄስዊቱ፣ ወደዚህ አገር የመሩቸውን ዕለትና ወደዚህ አገር የጀመሩትን የጉዞ ዕለት ማሰብ ጀመሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ በርሣቸውና በብርሃን መካከል እጅግ ብዙ ክብደት ያለው ጥቁር ድንጋይ የተጫነባቸው መሰላቸው፡፡ ፈረንሣዮች ሊጮሁ፣ እሪ ሊሉና ሊያለቅሱ ይችላሉ፡፡ ወይም ሊሞቱ ይችላሉ፡፡ ታዲያ ማንም ሊያድናቸው አይመጣላቸውም፡፡ ይህ ክፉ ሃሣብ በአምሮአቸው ውስጥ እየተሽከረከረ ሣለ፣ ጄስዊቱ፣ እንደአሣነባሪ በከፍተኛ ድምፅ ትንፋሻቸውን ለቀቁ፡፡ ጆን ባፕቲስት፣ በጣም ስለተበሳጨ፣ ይህን ሊሰማ ወደማይችልበት ራቅ ያለ ቦታ በፍጥነት ሄደ፡፡ ወጣቱ ሰው፣ በካፑቺኖች ማስፈራራት ሳቢያ የተፈጠረበትን የቁጣ ስሜት ሳያገናዝብ ትክክለኛነት በሌለው ሁኔታ ሁሉንም ነገር በብሬቬደንት ላይ ይከምርባቸዋል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ አንዳቸው አውጋዥ በመሆን ሌላኛው ተስፋ በመቁረጥ ሜትር ዠረሚ ወደሚጠብቃቸው ቤት በእግር ተጓዙ፡፡

በቅጥር ግቢው ውስጥ ከስፌት በተሠራ የቅርጫት ክምር ላይ ተቀምጦ፣ ጭልጭል በምትል የፋኖስ ብርሃን መፅሐፍ ያነብ ነበር፡፡ ፖንሴና ዮሴፍ ከፊት ለፊቱ ባለው ግንዲላ ላይ ተቀመጡ፡፡

«ካፑቺኖች ሁሉንም ነገር አውቀዋል» አለ ጆን ባፕቲስት

አባ ብሬቬደንት አይኖቻቸውን አቡዘው መሬት መሬት ያያሉ፡፡

«ስትል . . . »

ሜትር ዠረሚ፣ የጄስዊቱን ቁስ ማለቱ እንደሆነ በሚል አይኖቹ ከጆን ባፕቲስት ላይ ሳይነቀሉ በአንገፓ አመለከተ

«አይደለም፣ እንደመታደል ሆኖ የማያውቁት የሚመስለው አንድ ነገር ይህ ነው»

«ታዲያ ምን አሉ?»

«ዋናው ነገር እኛ ለፈረንሣይ ኤምባሲ ሆነን መጓዛችን ነው»

«ዝም፣ ፀጥ እንዲሉ ልንጠይቃቸው ይገባል» አለ

ሜትር ዠረሚ፣ ከተደላደለው መቀመጫው ላይ እየተጐተተ ተነሣ። ቅጥር ግቢውን የሚያካልሉት ከጭቃ የተሠሩት ግድግዳዎች ቁመታቸው በሰው ራስ ልክ ነው። በርቀት ያሉ ጭውውቶችን፣ የህፃናት ልጆችን እሪታዎች፣ በቅርብ ያሉ ማጉረምረሞችን፣ የውሾችን ጐኽትና የኮቴ ድምፆችን ይሰማሉ። ለሊቱ ጠፍ ጨረቃ ነው። ከላይ፣ በጥልቁ ሰማይ ውስጥ ከዋክብት ከብደው አሸብርቀዋል፣ ከባድ ነፋስም ያፏጫል።

«በትክክል ምን ይፈልጋሉ?» ሲል ሜትር ዠረሚ ሳይንቀሳቀስ፣ እንደቆመ ጠየቀ።

«ሁለቱ መነኰሣቶቻቸው አብረውን እንዲጓዙ ይፈልጋሉ። እኛ ገብ ከጀመርን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ካይሮ ውስጥ ቆንሲሉን አነጋግረው ነበርና አሁንም ከሃጅ አሊ ተልዕኮ ጥቂት የማትረፍ ተስፋ አላቸው።»

«አሻፈረን ብንላቸውስ?»

«ለሲናር ንጉስ ሁሉንም ነገር ይነግራሉ። ይህ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ አስብ። ንጉሡ ሙስሊም ነው። ለአቢሲኒያ ንጉስ የራሱን አገር አቋርጦ ሐኪም እንዲሄድለት ሊፈቅድ ይችላል። ከክርስቲያን ንጉስ የተላከ ኤምባሲ ግን ከቶውንም አይሆንም»

«እናስ?»

«ከሁሉም አስቀድሞ ምናልባት እንታሰር ይሆናል። ጉዳዩ በዚህ እንደማያበቃ ካፑቺኖች ፍንጭ ሰጥተዋል። በተለይም ሌሎች የውጭ ዜጐችን በሚመለከት መጥፎ አሉባልታዎችን በማሠራጨት ረገድ ተራው ህዝብ በጣም ያምናቸዋል። እንዲያውም አስማተኞች እንደሆንን ሊነግሯቸው ይችላሉ። ይህን ደግሞ በሣጥኔ ውስጥ ያሉት ብልቃጦች ደጋፊ ማስረጃ ይሆኗቸዋል። ህዝባዊ ቁጣው አንገታችን እንዲቀላ ሊጠይቅ ይችላል። ንጉሱ ደግሞ በፈቃደኛነት ይፈፅምላቸዋል።»



«አንተስ ምን ነገርካቸው?» ሲል ሜትር ዠረሚ ጠየቀው

«እኔማ ነገሮችን ሁሉ ከሃጅ አሊ ጋር ሆነን ማቀነባበር ይገባናል። ለዚህ ደግሞ ሁለት ቀናት ያስፈልጉናል አልኳቸው»

«ብራቮ፤ ታዲያ በነዚህ ሁለት ቀናት ምን ማድረግ እንችላለን?» ሲል ሜትር ዠረሚ ጠየቀ።

ምንም ዓይነት ሃሣብ እንደሌለው ለማስታወቅ ፖንሴ ቅንድቡን ሽቅብ ገፋው። ሊሆን የሚገባውን ሃሣብ በዝምታ ማውጣትና ማውረድ ጀመሩ። ሁኔታው አሣሣቢ ቢሆንም፣ ጆን ባፕቲስት፣ በርግጥ ስጋት አልተሰማውም። በዚህ ጊዜ ጉዞአቸው ፍፁም ድርድር ውስጥ በመግባቱና ዕቅዳቸው መሰናክል ስለገጠመው ቢበሳጭም፣ በስተመጨረሻው ግን ጉዟቸው እንደሚሣካ ርግጠኛ ነበር። በዚህ ልበሙሉነት ውስጥ የሃሣቡን እምብርት የያዘው የአሊስ ጉዳይ ነው።

«አንድ ካፑቺን ይዘን እንሂድ» አለ ሜትር ዠረሚ፣ ፍፁም ከስተር ብሎ «እናም ከዚህ አካባቢ በቂ ርቀት ላይ ስንደርስ ቀነጣጥሰን እንጣለው»

አባ ብሬቬደንት በድንጋጤ ዘለሉ። እንደተለመደው፣ ንግግራቸው ለፕሮቴስታንቱ ከማድረግ ይልቅ ለፖንሴ ነሩት።

«የነዚህ ተሃድሶ ፍራንሲስካውያን በኛ ተልዕኮ ውስጥ መካተት ከተልኳችን መሰረታዊ ሁሉ ጋር በቀጥታ የሚፃረር ነው። ቀሣውስቱን የመግደሉ ጉዳይ ከሆነ፣ ሃሣቡ የሚመነጨው ፍፁም ፀረ ሃይማኖት ከሆነ አዕምሮ ብቻ ነው።»

«ሌላ የመፍትሔ ሃሣብ እንዲያቀርብ ንገረው» አለ ሜትር ዠረሚ።

ፖንሴ ከመቀመጫው ላይ ተነስቶ በትንሿ ግቢ ውስጥ ብርሃን እስካለበት ጠርዝ ድረስ ጥቂት እርምጃዎች ተራምዶ ተመልሶ ወደ ጓደኞቹ መጣ። ፊት ለፊታቸው ግትር ብሎ እንዲህ አላቸው።

«ዛሬ ሌሊት ለቅቀን መሄድ አለብን»

«ለቅቀን?» አሉ ሁሉቱም ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ላይ

«አዎ ለቅቀን። ይህ ማለት ሁለት ቀንና ሁለት ለሊት እናገኛለን ማለት ነው። የካፑቺኖች ሰላዮች፣ እኛ ከተማው ውስጥ መሆናችንን እንዲያስቡ የሚያደርግ ማሳሳቻ ዘዴ ግን ማግኘት አለብን። ይህ እስኪሆን ድረስ እኛም በነርሱ ላይ ብልጫ ልናገኝባቸው የምንችላቸውን ጉዳዮች ማሰብ ይገባናል።»

«ስለ አገሩ አንዳችም ዕውቀት የለንም» አሉ አባ ብሬቬደንት

«ቅፍለቱም እስከ አንድ ሳምንት አይንቀሳቀስም» ሲል ሜትር ዠረሚ አከለ።

«ቅፍለቱን እንጠብቅም። ሃጅ አሊ መንገድ መሪያችን ይሆናል»

አንድ የቃለ ምልልስ የሚያደርግና ለማሰብ የተጨነቀ ሰው፣ ትክክለኛውን መልስ ሲሰጥ ለራሱ እንደሚሰማው ዓይነት፣ ፖንሴም በተናገረ ቁጥር መልሶቹ ይመጡለት ጀመር።

«እዚህ ቆይታችሁ የግል እቅዎቻችሁን አዘጋጁ። በተቻለ መጠን ባዶ ይሁን። እኔ ሃጅ ዓሊን ለማግኘት እሄዳለሁ።»

እነርሱ ቃል ከመተንፈሳቸው በፊት እርሱ ተፈተለከ። በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በየጥላው ላይ እየነጠረ፣ በተነጠፈው ቀጭን የድንጋይ መንገድ ላይ እየተደነቃቀፈ ሄደ። እንደ እድል ሆኖ፣ ቅፍለቱ፣ ከተማ ሲገቡ ሲሉ የሚሠፍሩበት ቦታ፣ ትልቁ የመዝናኛ አሸዋ ሜዳ በቀጥታ ከፊት ለፊቱ ነው። ችምችም ብለው ከተተከሉት ድንኳኖች መሃል ወደ ሃሰን አል ቢልቤሲ ድንኳን የሚያደርሰውን መንገድ መረጠ። እንደገመተው፣ ሃጂ አሊ ከቅፍለቱ መሪና ከሌሎች ብዙ ነጋዴዎች ጋር መሬት ላይ በተዘረጉ ምንጣፎች ላይ ተቀምጦ አገኘው። ሁሉንም ዞሮ ሰላም አላቸው። ትግስቱ እስከፈቀደለት ድረስ ቀስ ብሎ የሚጠጣውን ሻይ ፉት እያለ ከጨረሰ በኋላ፣ ሃጅ አሊን ለአስፈላጊ ቁም ነገር እንደሚፈልገው ገልፆ ጠየቀ። ግመል ነጅው ከጓደኞቹ ተነጥሎ ለመሄድ ከመወሰኑ በፊት ጥቂት ጊዜ ወሰደ። በኋላ ግን ፈቅዶ እንደወጣ ፖንሴ በቀጥታ ወደ ቤቱ አመራ።



«እንዲህ በድንገት ምን የሚያስጨንቅ ነገር ገጠመህ?» ሲል ሃጅ አሊ በደረቅ ቀልድ ጠየቀው።

«ዛሬ ሌሊት መንቀሣቀ አለብን» አለ ፖንሴ

ሃጅ ዓሊ የተሰባበሩ ባዶ ጥርሶቹን በምፀት ፈገግታ ገለጣቸው

«ዛሬ ሌሊት?» ሲል ጠየቀው

«እየቀለድኩ አይደለም»

«አስመታደል ነው» አለ ሃጂ አሊ እያፌዘ

«እና ብቻህን ልትጓዝ ነው?»

«አይደለም ከአንተ ጋር»

«ድንቅ ነው። መጠጥ በሰው አዕምሮ ውስጥ ፍፁም ያልተለመደ ሃሣብ ስለሚፈጥር፣ ነብዩ የአልኮል መጠጥ እንዳይጠጣ በመከልከላቸው እናመሰግናቸዋለን።»

«አንዳችም የሚያሰክር መጠጥ አልቀመስኩም» አለ ጆን ባፕቲስት «እና የምነግርህን በጥንቃቄ እንድታዳምጠኝ እፈልጋለሁ። አለበለዚያ ነገ ጀርባህን ተተልትለህ እስር ቤት ነው የምትወረወረው።»

«ጀርባህን ተተልትለህ? በማን?»

«በንጉሡ»

ሃጂ አሊ ደነገጠ

«ካይሮ የሚገኘው የፈረንሳይ ቆንሲል፣ ከካፑቺኖች ጋር ወደ አቢሲኒያ እንዳትጓዝ መፈለጉን ታስታውሳለህ?»

«ደህና አድርጌ አስታውሳለሁ»

«ቆንሲሉ ልክ ነበር። የተናገረውም ዕውነት ነው። እነርሱ ጥበቅ ሰዎች ናቸው። አንተን እንደተከታተሉህና የበቀል ዕርምጃ ሊወስዱብህ ሁለት ሰዎቻቸውን ልከዋል። አሁን ደግሞ አግኝተውሃል»

«እዚህ?»

«አዎን እዚሀ። ቀማውስቱ እዚህ ከተማ ውስጥ ቤት አላቸው። ንጉሡ፣ እነሱን በጥሩ ሁኔታ ስለሚመለከቷቸው በማንኛውም ረገድ ከለላ ይሰጧቸዋል።»

ሃጂ አሊ የፍርሃት ጅማሮ ተሠማው። ሰውነቱ ሲሸማቀቅ ያስታውቃል። ፊቱም ቀስ በቀስ የሚያሣዝን ገፅታ እየተነበበት ምህረት ለመለመን የተዘጋጀ መሰለ።

«በኔ ላይ ምን ወንጀል ሊያቀርቡብኝ ይችላሉ?» ሲል ጠየቀ

«በሁላችንም ላይ የያዙት ወንጀል ስላለ እዚህ ሊገቱን ይፈልጋሉ። ነገ ጧት ዶክተሮች ሳንሆን አስመሳዮች መሆናችንን ለንጉሡ ይነግሯቸዋል። ንጉሱም ያምኗቸዋል። የፈረንሣዩ ንጉስ ሉዊስ አስራ አራተኛ መልዕክተኞች መሆናችንን ይነግሯቸዋል። እናም ወደ ወህኒ እንጣላለን።»

ኧረ! ኧረ! በማለት ከጠቅላላው ድርሻው የሚያጣውን አጠቃላይ እድል በፍጥነት ሲያሰላ ሃጂ አሊ አቃሰተ።

«እናም ለንጉሡ ፈረንሣውያን ዶክተሮች መሆናችንን በሃሰት ተናግረህ ስላቀረብከን ተገርፈህ ወደ ወህኒ ትወርዳለህ»

«ግን» አለ የግመል ነጅው «አላውቅም ነበር አላለሁ»

«ካፑቺኖች፣ ካይሮ ውስጥ ከቆንሲሉ ጋር ተነጋግረዋል። ሁሉንም ነገር እንደምታውቅ እነርሱም ያውቃሉ።»

በሃጅ አሊ ላይ ጠንከር ብሎ አፈጠጠበት



«እነርሱም ምንም ባይናገሩ፣ እውነቱን የምናፍረጠርጠው እኛው እንሆናለን እነርሱ ምንም ባይናገሩ እኛ እንጠቅሠዋለን»

ምንም እንኳን በፊቱ ላይ ይቅርታ የለሽ ጭካኔ ያለበት መስሎ አረፍተ ነገሮችን ቢናገራቸውም፣ ጀን ባፕቲስት የሚያምን አልነበረም። ሃጅ አሊ የሠዎችን ባህርይ በማንበብ የሰለጠነ ነው። በዚህም ላቢያ ፖንሴ መጨረሻው መጥፎ ጠላቱ ላይ እንኳ ቢሆን እንዲህ ያለ ነገር አይፈፅምም። የማስፈራራቱ ዓላማ በተዘዋዋሪ ዘዴ ግቡን መታ። የግመል ነጅው አለመታመን በፊቱ ላይ ጭንቀቱን ሲያጋልጥበት፣ የጀን ባፕቲስት የእውነት መንፈስ ደግሞ በንግግሩ ላይ ይታወቅ ነበር። ሃጅ ዓሊ፣ ሶስቱ ፈረንሣውያን በርግጥ በአደጋ ላይ መሆናቸውን አምኖ፣ የራሱ ጥቅም ምን ላይ ሊሆን እንደሚችል ገመተ። እነዚህ ሰዎች ጠፍተው ቢቀሩ አንዳችም ጥቅም እንደማይተርፈው ለመገንዘብ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። እንዲህ ያለ ችግር በምድረ በዳው መካከል አጋጥሞት ቢሆን ኖሮ ቢያንስ የነርሱን ንብረት በሙሉ ይወስድ ነበር። አሁን ግን የሲናር ንጉስ ካሠሯቸው ቀጣዩ ተግባር በነርሱ ሃብት ላይ እጃቸውን መጫን ነው።

አይሆንም! ቢል የርሱ ጠቀሜታ ሰዎቹን ንጉሡ ዘንድ በማቅረብ ላይ የሚመሠረት መሆኑን አረጋገጠ። የአቢሲኒያን ንጉስ፣ ፖንሴ በማግኘቱ በመደሰት ይቦርቅና፣ ሃጅ አሊን ደስ በሚያሰኝ መጠን ሽልማት ይሠጠዋል። ከዚህም ሌላ ይህ ነጋዴ፣ ካይሮ የሚገኙትን ፈረንሣውያን ምስጋና ያገኛል። በነዚህ ግልፅ ምክንያቶች ጥቅሙ ተጓዦችን በማዳን ላይ ይሆናል። በተጨማሪም ደግሞ፣ ፈረንሳውያኑ ከሲናር በግድ መሸሽ አለባቸው። ስለዚህ የተወሰነውን ሸንጣቸውን እንዲሁ መተው ይገደዳሉ። ከዚህም ሃጅ አሊ፣ ትርፍራፊ አያጣም። ስለዚህም ሳያቅማማ ውሳኔ ላይ ደረሰ። ይህን ሲፈፅም አስፈሪ መስዋዕትነት እየከፈለ መሆኑንም መግለፅ ይኖርበታል። በመሆኑም ፖንሴ በሚችለው መጠን በነፃነት ካሣ ያከፍለዋል።

ሃጅ አሊ ማቃሠት ጀመረ። የግርፋትና የእስራት ወሬ በተጀመረበት ጊዜ በፊቱ ላይ የፈሠሠውን ላቡን ጠረገና የገንዘብን ነገር ጠቀሰ። ከአስራ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ስምምነት ላይ ተደረሰ። አራቱም፣ ማለትም ሶስቱ ፈረንሳውያንና ሃጂ አሊ በአንድነት ይንቀሳቀሳሉ። አምስት ግመሎችንና በጣም ጥቂት ጭነት ይይዛሉ። እያንዳንዱ ተጓዥ የግል ንብረቱንና መድሃኒት ሸንጣውን ይሸከማል። ከዚህ የሚቀረው ሌላው ነገር ሁሉ ማለትም ሣይንሣዊ

መሣሪያዎቻቸው፣ ለየአካባቢው አስተዳዳሪዎች የሚሰጡ ገፀ-በረከቶችና የነርሱ የቀያሬ ልብሶች በዚያኑ ዕለት ምሽት ሃጅ አሊ ወደሚያውቃትና በሲናር ውስጥ በሚያልፍባቸው ጊዜያት በተለምዶ ሲያፅናናት የነበረች ባሏ የሞተባት ሴት ቤት ይመጣል። እርሱ እስኪመለስም ድረስ እነዚህን ትርፍ ንብረቶቻቸውን በጥንቃቄ ደብቃ ታቆየዋለች። በመጨረሻም ከዚህ እለት ጀምሮ ግመሎቹ የርሱ ንብረቶች እንደሚሆኑ ሃጅ አሊ ሙጭጭ አለ። ፈረንሣውያን ስለጥቅሙ ሲሉ ከፍተኛ የካሣ ገንዘብ ይከፍሉታል።

በአፀፋው፣ ሃጅ አሊ ካጋጠመው ጊዜያዊ ችግር ነፃ ለመውጣት ተስማማ። ሌላው ቀርቶ የነርሱን መጥፋት ሃሰን አል ቢልቤሲ ከለላ እንዲሰጠው ያደርጋል። ማንም ሰው ስለፈረንሣውያኑ ቢጠይቀው በወንዙ ዳር ያሉትን ዕፅዋት ለመመርመር ሄደዋል፣ ይላል። ሃጅ አሊም ሃይለኛ የራስ ምታት ስለያዘው በህመም ውስጥ ራሱን አግልሎ ተኝቷል። ሁሉንም ነገር በኋላ ያዩታል።

አንዳቸውም እንኳ ዕንቅልፍ ባይዛቸውም፣ እራቱም ዕረፍት ለማድረግ ጋደም አሉ። ከሃሰን አል ቢልቤሲ ጋር ለመመካከር የሄደው ሃጅ አሊ፣ በስምንት ሰዓት ላይ አንድ ግመል ይዞ መጣና ሁለቱን ሻንጣዎች በኮርቻው ላይ ጫነበት። የየግላቸውን ኮርቻ ተሸክሙና ግመል ነጅውን በመከተል፣ ሦስቱ ፈረንሣውያን መንገዱ ውስጥ ሹልክ ብለው ገቡ። ከቅፍለቱ ጥቂት ርቀት ላይ ታስረው የነበሩትን ግመሎቻቸውን ጥቁር ቀለም በሚመስለው ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ አቻኳቸው። ደግነቱ፣ ሃጅ አሊ መንገዱን ደህና አድርጐ ያውቀዋል። እንደ ሽሽት የሚያፅናና ስለሌለ የፍርሃት ስሜት የለባቸውም። ለብዙ ሰዓታት በጥንቃቄ ተጓዙ። ከዚህ በኋላ ከተማው ከነርሱ ብዙ ርቀት ወደኋላ ነው። የውሾች ጋኸትም አይሰማም። ወንዙ ካለበት በስተግራ በኩል ርጥበት አዘል ነፋስ ሽው ይላል። የጥቁር አባይን አቅጣጫ ተከትለው ሽቅብ እንደሚጓዙ ገመቱ። የማለዳው የንጋት ብርሃን ሲፈነጥቅ ፊት ለፊታቸው ከሸንበቆ ደን አጠገብ የጭቃ ጐጆዎች ብቅ ብቅ ሲሉ፣ በወንዙ ዳር ሆነው የሌሊቱን ቅዝቃዜ ለማባረር ሲሉ ደንግጠው የሚጯጯሁ መንጋዎች ተመለከቱ። በዚህ አካባቢ የአባይን ወንዝ ከዳር እስከዳር የሚያቋርጠው የእንጨት ድልድይ አለ። ይህን በሠላም ካቋረጡ በኋላ የተቀመጡባቸውን እንስሳት ወደ ሃምራዊው የምስራቅ ብርሃን እንዲጋልቡ ኮረኮሯቸው።



አሊስና ፍራንቸይዝ በመድሃኒት ቀማሚው ቤት በረንዳ ላይ በየዕለቱ ማለዳ የለመዱት የተደጋገመ ምስጢራዊ ግንኙነት እነርሱ ከገመቱት ቀደም ብሎ ስጋት ያንገብብበት ጀመር። ሰላማዊውና ሀክምናቸውን ሳይቃወሙ በመቀበል አንዳችም ችግር ያልፈጠሩባቸው አባ ጋቦሪ በድንገት ታመሙ።

ከእለታት አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት ላይ አሊስ ልታያቸው ስትመጣ፣ ግማሽ ሰውነታቸው ከተኙበት ረዥም ሶፋ ላይ ወርዶ፣ አንድ እጃቸው ከመቀመጫው ላይ ቁልቁል ተንጠልጥሎ፣ አንዱ አይናቸው ብልጥጥ ብሎና አፋቸው ተጣምሞ አገኘቻቸው።

ሽማግሌው ሰው በህይወት ቢሆኑም፣ መንቀሳቀስም ሆነ መናገር አይችሉም ነበር። የርሳቸው መጥፋት ማለት ገና በጅምር ላይ ያለውን፣ ሰጋውን የወይዛዝርት ጓደኝነትም እንዲያከትም የሚያደርግ ነው። ቆንሲሉ ይህንን መነሻ ሰበብ አድርጐ ስለ እፅዋቱ ሲባል ልጁ የምታደርገውን ወጣ ወጣ ማለት በአስቀያሚ ግዴታ ሊያዝዝ እና እንዲያበቃ ሊያደርግ ነው። ልጁ ግን ለስለስ ባለ ገለፃ «ለዚህ ቤተ ሙከራ ባለቤት» ቃል መግባታቸውን አስታወሰች። አባቷ ትከሻውን ነቀነቀ። ለጥንድ ሴቶች እነዚህ ጥሩ ውሎች ነበሩ። ጉዳዩ፣ አሊስ ባልተገመተ ጥንካሬ የአባቷን ምኞት ተቃውማ ጭቅጭቅ ተነሣ። በመጨረሻም፣ ከዚህ በኋላ በእናቷ በማዳም ዱ ማይሌ አጃቢነት በዚያ የሙከራ ቦታ ያለውን ተግባሯን እንድትቀጥል አግባባችው። እናቷ አጅባት በመጣችበት በመጀመሪያው እለት የዕፅዋቱን ሁኔታ በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ እንድትሰማ አደረገቻት። በእርግጥም ሌላ ሰው የሌለበትን የራሷን ግኝቶች ለዚሁ ዕለት ሲባል እንዲካተቱ ብዙ የላቲን ቃላትን በመጨመር አብራራች። በየአንዳንዱ ለጋ ተክል አጠገብ ለረዥም ሰዓት በመቆም በድንገት አንድ ፍፁም ልዩ የሆነ ዝርያ ዘንድ ደረሰች። ምስኪኗ እናት በጣም በከባዱ ተሰላቸችና የራስ ምታትና የእግር ቁርጥማት እያመማት ወደ ቤት ተመለሰች። ልጇን አጅባ ወደ መድሃኒት ቀማሚው ቤት ለሁለተኛ ጊዜ ለመሄድ ለራሷ ቃል ብትገባም ይህ የመጨረሻዋ ሆነ። በእፅዋቱ ማሳደጊያ ቤት ውስጥ ያለው አየር ለጤንነትዋ መጥፎ መሆኑን ብታስታውቅም፣ ለልጅዋ ግን ከፍተኛ ጥቅም እንዳስገኘላት መቀበሏን ገለፀች።

አሊስ ለእፅዋት ያላት ፍቅር ጉዳት የሌለው ነው። እንዲያውም ይህን ፍቅሯን በማርካት ፋንታ መቃወሙ ሌላ ስጋት ሊፈጥር እንደሚችል፣ ማዳም ዴ ማይሌ ባሏን አግባባችው። ቆንሲሉም ለማመን ፈቃደኛ ሆነ። የሴት ልጁን ጉብኝት በተመለከተ ከውጭ ዜጐች ማህበረሰብ አንዳችም ያለመስማማት ሽክሽክታ አልደረሰም። እንዲያውም የአንድ የሆነ ነጋዴ ወንድ ልጅ፣ የራሱን ደርቀው የሚቀመጡ እፅዋት የማቆየት ስራ መጀመሩን እያመሰገኑ ይነግሩት ጀመር። አሊስ፣ ይህንን ጉብኝቷን ፍፁም እንዳታቋርጥ ወይም በቅርብ የሚደረግባትን አጀብ ፈርታ ነበር። ከዚህ ይልቅ አባቷ ብቻዋን እንድትሄድ ስለፈቀደላት ፍራቾይዝን ያለተቆጣጣሪ ማግኘት ቻለች።

ጊዜው የደስታ ወቅት ነበር። ወጣቷ ልጃገረድም ፍፁም የመለወጥ ስሜት አደረባት። የመጀመሪያው ምልክት ይህን ጉዳይ በመምራት ረገድ በጥንካሬና በቀራጥነት አባቷን መጋፈጧ ነበር።

በመጀመሪያ ላይ ሁሉም ላይ ላዩን ባሉ ሁኔታዎች ተመስጠው ነበር። ጓደኛ እጅግ ያስፈልጋት በነበረበት ዕድሜዋ ላይ፣ አሊስ ጓደኛ ተከለከለች። አሁንም ምኞት የሚነካትን የአካሏን ውበትና አዲሱን ቁመናዋን፣ አንዳች ከፍተኛ የመንፈስ ሃይል ጥንካሬ ቢያስፈራራትም በክብር ልትጠብቀው ፈለገች።

አዲስ የፀጉር አሠራር ዘዴ ለመሞከር ጊዜው ስለነበር፣ አሊስ ወደቤት ከመመለስዋ በፊት ቀትር ላይ ነባሩን አሠራር በችኮላ ፈታችው። የናቷን ቀንጆ፣ ቀንጆ ሙሉ ልብሶች በድብቅ በከረጢት ይዛ ከቆንስላው እየወጣች ታመጣለች። በብርቱካን ዛፎች ስር፣ ጥላ በጣለበት እርከን ላይ እየለበሰች ለጓደኛዋ እያሣየችና እየሳቀች ትራመዳለች። ወጣቷ ልጃገረድ አጠቃላይ የሆነ የውበትና የቁንጅና አስተሳሰብን ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱን ዝርዝር እንደምን ዋጋ ልትሰጠውና የሚገባውን ሙሉ ድርሻ እንዳታሳንስበት ፍራንቾይዝ ታስተምራታለች። አሊስ እያበበች ነበር።

ይህን ዘመን ወደኋላ መለስ ብላ ስትመለከተው፣ ራሷን ለማግኘት በሞኛ ሞኝ ስሜት ተውጣ በነበረበት ጊዜ፣ ፍራንቾይዝ ያን ያህል ትዕግስትና ደስታ ስላሳየቻት ፍፁም የማይረሣ ውለታ አለባት።



ቀስ በቀስ ይህ ነው በማይባል ጉዳይ ውስጥ ገቡ። አሊስ ስለንብረቶችዋ ጠንቃቃ የነበረች ቢሆንም ልካቸውን ስለምታውቅ መጨነቋን ትታለች። ከዚያ ጊዜ ወዲህ አዲስ ሰላም ለራሷ ፈጠረች። ጥልቅ የሆነ የራስ መተማመን አዳበረች። እነዚህን ሁሉ በንግግሯና በባህሪዋ ትህትና ሽፍና ለማቆየት ብልህነቱ ነበራት። በተለመደው ሁኔታ እናቷ ምንም አዲስ ነገር አታስተውልም። ምንም እንኳ እናቷ ባለመቀረቧ ብታዝንም ምስኪኗ ሴት ያስተማረቻት ነገር አለመኖሩን ተገነዘበች። ታላቅ ልብወለድ ሊፃፍበት ከሚችለው የፍራንቾይዝ ሕይወት ጋር የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት አላት።

የተወለደችው ግሬኖብል ውስጥ ሲሆን፣ አባቷ ሞልቶ የተረፈው የእህል ነጋዴ ነበር። ወላጆችዋ እምብዛም ስለማይከታተሏት ብድሯን ለመመለስ በእድሜው ሠላሣ አመት ከሚበልጣት ጋር ፍራንቾይዝ ኮበለለች። ሰውዬው የንግድ ስራ ላይ ቢሰማራም ጠበቅ አድርጐ አልያዘውም። ሃብታምም ባይሆን ገንዘብ ያባክን ነበር። ይህ ደግሞ ከፍራንቾይዝ አባት ባህርይ ጋር ፍፁም ተቃራኒ ነበር። ይህ ፍቅረኛዋ፣ ንግግር አዋቂ፣ ምስራቃዊውን ዓለምና ኢጣሊያንን የሚያውቅ ነበር። ሰውዬው ይዟት ሄደ። ይህ ማለቂያ የሌለው የጀብዱ ሕይወታቸውን የጀመሩበት ጊዜ ነበር። ፍራንቾይዝ፣ ያንን ወቅት እንደ አንድ ሺህ አንድ ለሊት ተረቶች፣ በትንሽ በትንሹ ትተርከዋለች። በኩብለላ ተጀመረ። ሃብት ተገኘ። ዙረት ተጀመረ። በድህነት ተደመደመ። ሁለቱ የጦፈ ፍቅር ነበራቸው። በኋላ ግን ለስደት ተዳረጉ። ቅጥፈት ተጀመረ። ቁማር ተለመደ። የከፋ ድህነት ሰተት ብሎ ገባ። ካይሮ ከደረሱ በኋላ ዳግመኛ አይን ሳይን አልተያዩም። የሚቀጥለው ምዕራፍ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ፣ ከገደል ወደ አዘቅት ወረደ። ሰውዬው በቆሻሻ የአረቦች መኖሪያ ብቻውን ኖሮ ሲሞት ምዕራፉም ተዘጋ። ከዚህ የማይታመን የአኗኗር ታሪክ፣ ፍራንቾይዝ የሰዎችን ስዕል ትስላለች። ታሪኮችን ትጽፋለች። ጥቂት ስለ ፀባይ ትገልፃለች። እርሷ ልትጠቀምባቸው ባትችልም ምክሮችዋን ትለግሳለች። ትንታግነቷ በዕድሜና በግዴለሽነት ሳቢያ ጠፍተውባታል። ፍራንቾይዝ በመደሃኒት ቀማሚዎች ስለተቀጠረችበት ባወራች ቁጥር፣ ሜትር ዠረሚን ያለስሜት ጠቅማው እንደማታውቅ አሊስ ልብ ብላች።

«ታፈቅሪዋለሽ?» ስትል ወጣቷ ልጃገረድ ጠየቀቻት

«ግልፅ እንድትሆኚ ጠይቄሽ ነበርና እኔም በግልፅ እነግርሻለሁ።» አለቻት ፍራንቾይዝ «ጥሩና ወኔ ያለው ሰው ነው። አዎን፣ አፈቅረዋለሁ ብዬ አምናለሁ»

«ነግረሽው ታውቃያለሽ?»

«አ! በርግጥ አታውቂውም ማለት ነው። አኩራፊና ግልፍተኛ ሰው ነው። ልንገረው እያልኩ ከሃያ ጊዜ በላይ አስቤያለሁ። ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በአይኔ ሣይዞር ምን እንደምናገር አስባለሁ። እንዳይነጋ የለም፣ ሲነጋ እዚሁ እደርሣለሁ። በነዚያ ጨፍጋጋ አይኖቹ ሲያየኝ፣ ወኔዬም ድራሹ ይጠፋል። አየሽ፣ የዚህ አለም ሴት እንደሆንኩ አስመስላለሁ እንጅ፣ ያንቺ ያህል እንኳ ላከናውን የምችል አይደለሁም. . .»

ይህች አነስተኛ እውነት፣ ፍራንቾይዝ በነገረቻት ሁሉ ላይ የሚታከለውን ግምት ከፍ ያደርግላታል። በልጅነት ዘመኗ የፈፀመችውን አደገኛ ሁኔታ ስትናገራቸውና የውድቀት ጊዜያቶቿን ስትገልፃቸው፣ ፍፃሜውን ለማሣወቅ የተከተለችው ስልትና ገና ደፍራ ያልገለፀቻቸውን ሁሉ የምታስረዳው በንፁህ መንፈስ ነው።

አሊስ ታደንቃታለች። ይህን አይነት ስሜት በአንድ አገልጋይ ላይ ማሣደር፣ አባቷን ያስቀይመው ነበር። ነገር ግን አሊስ በተለየ መልክ ተመከለተችው። ፍራንቾይዝ ነፃ ሴት ነበረች። ነፃነቷን ለማግኘት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ከፍላለች። የደረሰባትን ሁሉ ፈፅሞ አዝናበት አታውቅም ።

እስከዚህች ሰዓት ድረስ አሊስ የምታስበው፣ የአንዲት ሴት ምርጫ ሽንፈት ብቻ ይመስላት ነበር። የፍራንቾይዝ ሕይወት ግን አማራጮን አቀረበላት። በዚህች የዕድሜ ባለፀጋ ሴት ማነሣሣት የአሊስ ሕልሞች ይበልጥ ለጀብዱና ለምስቅልቅልነት ተዘጋጀ። አሊስ የራሷን ነፃነት እንደቀዠች ስታስበው፣ ከጆን ባፕቲስት ጉን ፈረስ ስትጋልብ ይታያታል። በመጀመሪያ ነገር በርስዋ ዙሪያ እርሱን ልታወዳድረው የምትችለው ሰው ስለሌለ ይመስላት ነበር። ነገር ግን ፍራንቾይዝ በተለየ መልክ አግባባቻት።

«ሕልሞችሽን ፍፁም አጠንክሮ የሚይዝብሽ ወንድ ካለ፣ እንዲህ በቀላሉ የሚለቀቅ አይደለም» አለቻት ራሷን እየነቀነቀች።



# 7

ለሃያ አንድ ቀናት በእግራቸው ተጓዙ። ሽሽት በጀመሩባቸው የመጀመሪያ ሰሞን፣ በሲናር ንጉስና በሰራዊቱ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ። ካደረባቸው ፍርሃት በመነጨ ንጉሡ ካላቸው ስልጣን በላይ የትም ቦታ የሃያልነታቸውን ምልክት እንደሚያዩ ይገምቱ ነበር። ክትትል እንደማይደረግባቸው ራሣቸውን ለማሣመን የአንድ ሣምንት ጊዜ ወስዶባቸዋል። ክንፍ አላቸው ብለው በሚያስቧቸው በንጉሱ ምስጉን ወኪሎች ተቀድመው እንዳይሆን ሁሉ ይሰጉ ነበር። እውነታው ግን፣ በሰፊው የምድረበዳ ግዛት ውስጥ እነርሱ ራሣቸው ጠፍተዋል። እውነተኛው ጠላታቸው፣ የማይታየው ገዥ ወይም ቅንነት የሌላቸው ካፑቺኖች ሣይሆኑ፣ ውሃ፣ ምግብና ዕረፍት ሳያገኙ የሚያቋርጡት አገር ነው።

ምድሩ ለጥ ያለ ሜዳ ነው። አልፎ አልፎ በሚታይ፣ ፀሐይ የጋገረችው የሚመስል የቋጥኝ ነጠብጣብና የአሸዋ ወንዝ ሸለቆዎች እየተፈራረቁ ያሉበት እጅግ ሰፊ የሆነ ደረቅ አገር ነው። በዚህ ሸለቆ ውሃ የሚወርደው በዓመት አንድ ጊዜ ታላቅ ጎርፍ ሆኖ ነው። ነገር ግን ይህ ጎርፍ ከሌሎች የውሃ መስመሮች ጋር ከመቀላቀሉ በፊት አፈሩ መጥጦ ያስቀረዋል። በዚህ እንግዳ በሆነ ሸለቆ ውስጥ ያለው ሣር ቅጠል በሽመል፣ በመቃ፣ በማበብ ላይ ባሉ የቆንጥር እሾሆች፣ ብዙ ውሃ በማይዙ ሹል ወፍራም ቅጠል ባላቸው ተክሎችና በግራር ዛፎች የተሞላ ነው። የክሽሽላ ቁጥቋጦና የቀንጠፋ እሾት በምድሩ ላይ ወፍራም ምንጣፍ ሆነው በዚያ ቦታ መቆየትን አስቸጋሪ ከማድረጋቸውም በላይ አንዳንድ ጊዜ ጉሏቸውንም ይጉቱባቸው ነበር።

ጭንታቸውን እጅግ በጣም ቀንሰው ስለነበር፣ ኮብላዮቹ መከላከያ የሚሆናቸው ድንኳን ወይም ተንጠልጣይ የጨርቅ አልጋ ወይም ብርድልብስ አልነበራቸውም። መሬት ላይ ይተኛሉ። በምድረ በዳው ውስጥ ከናዝራ፣ ከጊንጥና ከመርዘኛ እባቦች መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ሣር ቅጠሉ ጥቅጥቅ ባለበት ቦታ መንገድ እየጣሱ ሲጓዙ በጣም ትልቅ ዘንዶ አጋጥሟቸው ነበር። ከዚህም በላይ የሰው ልጅ ምንም ያህል ቢፈራቸውም፣ ፈጣሪ የፈጠራቸውና ሰውን ከመኖሪያ ጫካቸው ውስጥ አሣድደው ወደ መሠሎቹ እንዲሄድ የሚያባርሩት ትንኞችና ሌሎች ዓይነቶች የተባይ ዘሮች ነበሩ። ከሲናር በሸሹ በመጀመሪያው ሰሞን አንድ ቀን አባ ዱ ብሬቪደንት ቁርጭምጪምታቸው ላይ በአንድ ትልቅ ናዝራ ተነድፈው ነበር። ሕመሙን

ለማስታገስ ፖንሴ መድሃኒት ቢሠጣቸውም፣ እብጠቱ በእግራቸው ሁሉ ላይ በመሠራጨቱ ትኩሣት ፈጥሮባቸው ነበር። በዚህ ግቢያ ጉዞው ፍፁም የስቃይ ሆነባቸው። ሆኖም ቀስ በቀስ ህመሙ እየቀነሠና እየተሻላቸው ቢመጣም ከዚያ ወዲህ እየደከሙ፣ እየደከሙ መጡ።

እየተጣደፉ መሆናቸውን ባሰቡ ቁጥር፣ መንደሮችን ለዚያውም ጥቂት የከብት አርቢዎች ጐጆዎች ያሉባቸውን ሰፈሮች መተው ጀመሩ። የውሃ ቀርበታዎቻቸውን ለመሙላት ወደ ጉድጓዶች የሚሄዱት በሌሊት ሆነ። ከሲናር የያዙት አንድ ጆንያ ደረቅ ባቄላ ሳያልቅባቸው፣ ከመንጋዋ ተነጥላ የጠፋች ጥጃ አግኝተው ይይዛሉ። ሣጅ አሊ በእምነቱ ስርዓት ካረዳት በኋላ ዮሴፍ እንዲገፍፉት አዘዛቸው። ሙስሊም አርዷት፣ ካቶሊክ በልቷትና ፕሮቴስታንት ተመግቧት ያበቃችውን ጥጃ የአይሁድ ራባይ አጥንቶችዋን እንዲቀረጣጥፍ ካልተጋበዘ በስተቀር፣ ሌላ የክርስትና መስመር ተከታይ አይገኝም። ያልተበላውን ቀሪ ክፍል በኮርቻቸው ላይ ጫኑ። እንደአለመታደል ሆኖ አንድ እረኛ አይቷቸው ስለነበር የማስጠንቀቂያ ምልክት አሰማ። ወዲያውኑም ጦርና አጫጭር የነሃስ ጐራዴ የያዙ የጥቋቁር ሰዎች ሠራዊት ወረራቸው። ፖንሴ፣ የቁጥራቸውን መብዛት አይቶ መሸሽ የሚሻል መሆኑን ሲገምት ሜትር ዠረሚ ዘልሎ ጐራዴውን ያዘና ጮኸ።

«ኑ ወደኔ ጌቶቼ!»

ጆን ባፕቲስትም መሣሪያውን አፈፍ አድርጐ ጓደኛውን ለመከላከል ገባ። አስቀድመው የደረሱባቸውን ሁለት የአካባቢው ተወላጆችን አጠቋቸው። እጅግ ፈጣን በሆነው ለአይን በማይታየው የረዥሙም ስለታምና ሹል ጐራዴ የእንቅስቃሴ ፍጥነት፣ ሁለት አጥቂዎች አይኖቻቸውን ጐልጉለው፣ ሰውነታቸው እንዲወጋ የፈቀዱ ያህል ዘለው ገብተው ተወግተው ወደቁ። በዚህን ጊዜ ሁለት ሌሎች አጥቂዎች ተኳቸው። በተግባር፣ ቁጥር ውስጥ ሲገቡ በማይችሉ ተጋጣሚዎቻቸው እንቅስቃሴ ተደነቁ። የጐራዴዎች መፈጨት አሸበራቸው። ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች አንድ በዓል የሚያከብሩ ይመስል እነዚህን ነጠላ ውጊያዎች ከብበው ይመለከቱ ጀመር። ሁለቱ እንግዶች እንደ የውሃ ተርብ ክንፎች በሚርገበገቡት በረዣዥም የብረት ዘንጐቻቸው ላይ አካላዊ ብርታታቸውን ተጠቀሙ። ተቃዋሚዎቻቸው የሚደርስባቸውን ሞት ለመከላከል ከባድ ጦሮቻቸውን ተጠቀሙ። አንዳንዶቹ የቆዳ ጋሻ አንግበዋል። አንድ ምት ሲያርፍባቸው፣ በሁለት ሌሎች ይተካሉ። የቆሙት ጥቋቁሮቹ ሰዎች ቁጥራቸው ከሁለት መቶ በላይ ስለሚሆን ውጤቱ የሚያጠራጥር አይደለም። በባዶ እግራቸው



መሬቱን እየደመደሙ በእግራቸው ቁርጭምጭሚት ላይ ያሰሯቸው አምባሮች እንዲንቃጨሉ ያደርጋሉ። ፖንሴና ጓደኛውን እየከበበ ያለው መስመር ፍፁም ጠበበ። ድካም ሲያሸንፋቸው አጥቂዎቻቸው በቀላሉ አንገቶቻቸውን እያነቁ መሳሪያዎቻቸውን በመማረክ ሲጥ ያደርጓቸዋል። በዘቡ መካከል ፖንሴ በአጋጣሚ ዮሴፍን ተመለከታቸው። ሕዝቡ እርሳቸውን አልከበባቸውም። እጆቻቸውን በጐናቸው ላይ እያወዛወዙና ምን ማድረግ እንዳለባቸው መወሰን ሳይችሉ ከግመሎቻቸው አጠገብ ቆመዋል።

«ሽጉጡን» ሲል ፖንሴ ጮኸባቸው

ጀስዊቱ ግራ የተጋቡ ይመስላሉ

«ኮርቻዬ ቦርሣ ውስጥ የተቀባበለ ስላለ ይተኩሱ!»

ክቡ በዝግታ ግጥም አለ። ቅላፄ ካለው የእግር እርግጫ ስር እርቃናቸውን ያሉ፣ ለቁጥር የሚያታክቱ ቀጫጭን እግሮች ከሚያነሱት አቧራ በስተቀር ፖንሴ ሌላ ማየት አቃተው።

በድንገት ሁለት የተኩስ ድምፅ ምድሩን አናወጠው። የአካባቢው ተወላጆች በያሉበት ፀጥ አሉ። ለሠላሣ ሴኮንዶች ያህል ሁሉም ነገር ፀጥ አለ። ከዚያ በኋላ ቁስለኞቻቸውና መሣሪያዎቻቸውን ጥለው እግሬ አውጭኝ አሉ።

ከአፈሙዞች እየበለለ የሚወጣውን ጭስ እየተመለከቱ ጀስዊቱ በፍርሃት ሽጉጦችን እንደያዙ ናቸው።

«ደግ» አለ ዠረሚ ወደ የውሸቱ ዮሴፍ እየተራመደ «ይህን ድል አድራጊነት ብለህ ልትጠራው ትችላለህ። በሁለቱ ሽጉጦች እዚህ ለራስህ ግዛተ ዘውድ መመስረት ትችላለህ»

ለጀስዊቱ ፈገግ አለላቸው።

«እርግጠኛ ነኝ፣ በቀላል መግባባት ሁሉም ወደ ካቶሊክነት ሊለወጡ ይችላሉ።»

ጀስዊቱ ትከሻቸውን ነቀነቁ። ግጭቱን በርቀት ለመመልከት የወሰነውን ሃጅ አሊን በአንድ እሾሃማ ቁጥቋጦ ስር ሆኖ አገኙት። ብዙና ጠለቅ ብሎ የተበጫጨረውን ሰውነቱን

እንዲያከምለት ፖንሴን ለመነውና የቁስል መጥረጊያውን እንደ ሀማዕት ተቋቋመው:: ከአራቱ ተጓዦች መካከል ከዚህ አጭርና የድል አድራጊነት ተጋድሎ በኋላ ቆስሎ የተገኘው እርሱ ብቻ ነው::

የንጉሱ ብቀላ ሊደርስባቸው ከሚችለው እጅግ እርቀው መገኘታቸውን በመገመት፣ በየመንደሩ ጥጋጥግ እያንዣበቡ መኳዝ የአካባቢውን ተወላጆች ጥርጣሬ ከሚያስፈልገው በላይ ስለሚቀሰቅስ፣ እንደ ሰላማዊ ተጓዦች በግልፅ መሄድ እንደሚሻል ጆን ብሮቴስት ገለፀ:: ከዚህ በኋላ ሕይወታቸውም ይበልጥ የተመቻቸ ሆነ:: የሚያገኟቸው ጕሳዎች፣ ጥቃት የሌለበት መስተንግዶ ያደርጉላቸዋል:: ከርቀት ቦታዎችም፣ ነጭን ቆዳቸውን ለማየት ይመጡ ጀመር:: አንዳንዶችም እየፈሩ ይነኳቸዋል:: የአካባቢው ተወላጆች ሞቅ ያለ አቀባበል ያደርጉላቸው ጀመር:: የተጣሏቸው ጕሣዎች የተጋጯቸው፣ ንብረታቸው በድብቅ በመወሰዱ ተቆጥተው ነው:: በወዳጃዊ ስሜት ከተጠየቁ ያላቸውን ለመስጠት ወደ ኋላ የማይሉ ናቸው:: ለተጓዦቹ የማሽላ ቂጣዎችና አፍሪካውያን ከፍተኛ ጥራት ያለው የሚሉትን ትኩስ የላም ደም ተደባልቆበት የተመታ ትልቅ ወጪት ወተት ይሰጧቸዋል:: እንደ ቀላል የመልካም አቀባበል ማረጋገጫ ከዘመዶቻቸው ውብ የሆኑ ኮረዳዎችንም ያቀርቡላቸዋል:: ፖንሴና ሜትር ዠረሚ ለረዥም ሰዓታት በኮርቻ ላይ ስለሚውሉ አልጋ ላይ ከወደቁ በኋላ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ከመተኛት ሌላ የሚያስቡት የለም:: የተመረጡላቸው ሴቶች ከጐናቸው እንዲተኙ ቢጋበዙም፣ ጥቂትም ሣየቆዩ ማንኮራፋት ይጀምራሉ:: ከማንቀላፋታቸው በፊት ግን ተጓዳኞቻቸው ሙሉ አካላዊ ክፍላቸውን ያሳዩዋቸዋል:: በኋላ እንደገለፁላቸው ከሆነ እነዚህ አብረዋቸው እንዲያድሩ የሚደረጉት ወጣት ሴቶች አብይ ተግባራቸው፣ በሚቀጥለው ቀን ለማህበረሰቡ በሞላ የነዚህ የተጓዦች ፍፁም የግላቸው የሆነው የአካል ክፍላቸው ምን አይነት ቀለም እንዳለው ሪፖርት ማቅረብ ነው:: ለእነዚህ ተወላጆች ይህ እንግዳ የሆነው ነጭ የቆዳ ቀለም ከባዕዳኑ ሰውነት ላይ፣ ከላይ እስከታች ድረስ መዝለቁን የአይን ምስክር ሆኖ የሚያረጋግጥላቸው በስሌስ ለማሣመን አስቸጋሪ ነበር::

አባ ብሬቬደንት የሚደረግላቸውን ክብር በምንም መልክ እምቢ እንዳይሉና እነርሱ የሚያርጉትን እንዲከተሉ ጓደኞቻቸው መክረዋቸው ነበር:: እርሳቸውም፣ ለዘንዶ እንዳይጣሉ በመፍራት ሌሊቱን ሙሉ የፀፀት ፀሎት ሲፀልዩ ያድራሉ:: በእግራቸው ላይ ካለው እብጠት በዘላል ቢድኑም፣ ቢጋጠማቸው መከራ ቢደክሙም፣ የቀራቸውን የጤንነት ጉዳይ ይበልጥ



አባባሉት:: ሜትር ዠረሚ እያሾፈ ክብረ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ የቅዱስ አግናጢዮስን ትዕዛዝ በመውሰድ፣ እንደሬሣ መሆን ነውና ጥቅም የለውም ይላል::

ሃጅ አሊ፣ እንዲህ ባሉ ትክክለኛውን ነገር በመፈፀም ጉዳይ ራሱን አያስጨንቅም:: እርሱ አሁን እየተጨነቀ ያለው በወጉት እሾሆች ሲሆን ለአመል ሲነኩት ይጮሃል:: የሚያደርገው ቢኖር የነዚህን ያልሰለጡኑ ሰዎች ባህል ማንኳሰስና እስልምና እስካሁን እነርሱን ባለማሰልጠኑ በማዘን የሚሰጠው አስተያየት ነው::

በዚህ አይነት ሁኔታ ከአንዱ መንደር ወደ ሌላው ለአምስት ቀናት ከተጓዙ በኋላ፣ ገሬፊም ከተባለ ትልቅ ከተማ ደረሱ:: ገሬፊም፣ በዘንባባ ዛፎች የተከበበች፣ በጉዋባ፣ በሮማን፣ በአቦካዶና በብርቱካን አበባዎችና ፍሬዎች የተዋበች ነች:: በቀቀኖችና ሌሎች ብሩህ ቀለማት ያሏቸው አዕዋፋት በየዛፎቹ ውስጥ አርፈው ሲታዩ ለብዙ ቀናት የተጓዦቹ ብቸኛ አጃቢዎች ሆነው በሰማይ ላይ ይታዩ ከነበሩት ጥንብ አንሣዎች ይልቅ ተስማሚ ለውጦች ናቸው::

አሁንም ረዥሙንና ለሙን የሰሜን ሸለቆ እስኪደርሱ ወደ ሰርከ የሚወስዳቸው ገና የሁለት ቀናት አጫጭር የምድረበዳ ጉዞ ይቀራቸዋል:: የጥጥ ተክል በለበሱ ነጫጭ ኮረብታዎች ዙሪያዋን የተከበበችው ከተማ፣ ትልቅ የንግድ ቦታ ነች:: በከተማዋ መካከል እረፍት የለሽ ገበያ አለ:: ከአካባቢው በሚጕርፈው የስራ ውጤት የሚያማምሩት ደማቅ የጥጥ ልብሶች፣ በከተማው ውስጥ ተሸምነው በጥሬ ማቅለሚያዎች፣ በከርሚን፣ በጥቁር ሰማያዊ፣ በብርቱካንማ ቀለማት ተሰርተው ይታያሉ:: የቅመም መዓዛ በገበያው አየር ውስጥ ይንሣፈፋል:: በየመደብሩ፣ ውብ ሽታ ያላቸው የኢትዮጵያ ሸቀጦች ይታያሉ:: ከተማዋ፣ የመሸገሪያ ድልድይ ባላት በአንዲት ቀጭን ምንጭ አጠገብ የተመሠረተች ናት:: በርቀት ያለችው አገር አቢሲኒያ ነች:: የረዣዥርም ተራራዎች ምድሮች ቅርፅ በአቧራማው እይታ ውስጥ ሲጠፋ ይታያል::

❧

ድልድዩን እኩለ ለሊት በስድስት ሰዓት ላይ አቋረጡት:: በዙሪያቸው ከነበረው አንዳችም የተለወጠ ነገር ባይኖርም ከወንዙ ማዶ እግራቸው መሬቱን ሲረግጥ መንፈሣቸው ተነሳስቶ

በደስታ ጮኹ። ፖንሴ፣ የመድሃኒት ሻንጣውን ከፍቶ በተለይ ለዚህ ልዩ ወቅት ሲል ያስቀመጠውን ልዩ ፋሽኮ ጠርሙስ አወጣ። በአንድ ሥሩ ላይ፣ ባለ ሦስት ማዕዘን የሻርክ ክንፍ ቅርፅ ኖሮት የእጅና የጀርባ መደገፊያ ያለው ዛፍ ሥር ተቀመጡ። ጆን ባፕቲስት ጠርሙሱን ከፈተውና አቢሲኒያ ስለመድረሳቸው ለጤንነታቸው ጠጡ። ጆን ባፕቲስት፣ አንድ ጉንጭ ሙሉ በአንድ ጊዜ ሳበና ጠርሙሱን ለዝርጋሚ ሰጠው። እርሱም በተመሣሣይ አንድ ጉንጭ ሙሉ ሣበ። መጠጡ፣ አባ ጋብሬን በዚያ ረዥም ፎቴ ላይ በደስታ እንዲጋደሙ የሚያደርጋቸው ዓይነት ነው። በዚህ ወንዶች ባላባት በሆኑባት በክርስቲያን ምድር ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ብዙም ስለሃይማኖቱ ያልተጨነቀው ሃጅ አሊ፣ ሁለት ጊዜ ተጐነጨ። የሴፍ ለመጠጣት እምቢ አሉ። እነርሱ ግን አደፋፈሩዋቸው። ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ደም አስታወካቸው። የነህኑ ሁኔታ በጣም ያስጨነቀው ፖንሴ፣ ህመምተኛውን ሰው አረፍ አድርጐ፣ ሊያይ የሚችልበት ትልቅ ዛፍ ወይም ከተቻለ የመኖሪያ ጐጆ ሲያገኙ የሚችሉበትና በአቢሲኒያ አገር ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው ከተማ ምን ያህል እንደሚርቅ ግመል ነጂውን ጠየቀው።

በቅርቡ ምንም መንደር እንደሌለ፣ የሚሻለው መንገዱን መከተልና ከዋናው ከተማ ብዙም እንደማይርቁ ሃጅ አሊ ነገሩቸው። ነጋዴው፣ የኒህ አገልጋይ ሕይወት እጅግ በጣም ጠቃሚ ባይሆንም፣ ጉዟቸውን እንዳያዘገይባቸው በማሰብ በተቻለ መጠን በፍጥነት ከተማ ለመድረስ ይፈልጋል።

ሕመማቸውን ቀላል በማስመሰል ጄስዊቱ ተስማሙ።

«ከዚህ በኋላ ወደ ደጋው አገር ልንወጣ ነው። እዚህ ከሚያነድደን የምድር በዳ ሐሩር ይልቅ ላይ ያለው ቀዝቃዛ አየር ሣይሻል አይቀርም» አለ

ከአንድ ሰዓት ጉዞ በኋላ ከተራራው ግርጌ ደረሱ። በለምለም የቀርከሃና የጥቁር እንጨት ኔት የተሞላውን ሸለቆ ተከትለውም መጓዝ ቀጠሉ። ቀጭኑን የእግር መንገድ ይዘው ሲጓዙ የሳሳዋቱ መጠን ይበልጥ ጫካና ደን እየሆነ ይመጣል። ጀምበር ስትጠልቅ በመንገዱ ዳር ባለ ገላጣ ቦታ ላይ አረፉ። እኩለ ሌሊት ሲሆን እጅግ አስፈሪ የሆነ ግሣትና ከፍተኛ ድምፅ ያለው ፖኸት ከእንቅልፋቸው ቀሰቀሣቸው። ጨረቃዋ ስለጠለቀችና ምሽቱም ድቅድቅ ያለ ስለሆነ፣ ለደህንነታቸው መልካም የሚሆነው አብረው በመቆየት የሆነውን ሁሉ ባት መመልከት



እንደሚሻል ወሰኑ። ንጋቱ ላይ ሁለቱ ግመሎቻቸው እንደሌሉ አወቁ። አንደኛው፣ ከአንበሣ ጋር ታግሎ መበላቱን የሚያሣይ እጅግ ብዙ የሆነ የደም ነጠብጣብ አዩ። ሌላኛው ግመል በአንበሶቹ ጥቃት ፍርሃት የታሰረበትን የገመድ ለኮ በጥሶ ከርሱ በታች በመቶዎች የሚቆጠሩ ርምጃዎች ራቅ ብሎ ተገኘ።

ሌላም ግመል ስለጠፋባቸው ከተጓዦቹ አንዱ የግድ በእግሩ ሊጓዝ ነው። ጄስዊቱ ለዚህ ፈቃደኛ ሆኑ። ፖንሴ ድርቅ ብሎ አይደረግም አለ። ሰውዬው፣ ከስት ጥቁር ብለው ትኩሣታቸው ተነስቶባቸው እግራቸውም ማበጥ ጀምሯል።

«እባክህ ፍቀድልኝ» አሉ አባ ብሬቬደንት «ምንም አይነት አድልዎ አታድርግልኝ። አሽከር መሆኔን አስታውስ። በተለየ መልክ ከታየሁኝ ጥርጣሬን ትቀሰቅሳለህ።»

በዚህ ጊዜ ማናቸውም ንግግራቸውን አልተቀበሏቸውም። ሜትር ዝርጋሚ፣ ካህኑን በራሱ ኮርቻ ላይ አስቀመጣቸውና እርሱ ከቅፍለቱ ጋር በእግሩ መጓዝ ጀመረ።

በሸለቆው ውስጥ ለቀጣይ ብዙ ቀናት ተጓዙ። ሣር ቅጠሉ ይበልጥ ጥቅጥቅ እያለ ሲመጣ አንዳንዴ አስር ጫማ ያህል አጠር ያለ ዋርካ ያጋጥማቸዋል። ሲመሽ ሽጉጣቸውን አቀባብለው ይይዙና ግመሎቹ ከታሰሩበት ጥቂት ጫማ ፈቅ ብለው በእሳቱ አጠገብ በመቀመጥ፣ በተራ መጠበቅ ጀመሩ። ከሸለቆው የመጨረሻ እናት ላይ ከበፊተኛው የሚተልቅና ቀጣይ የሆነ ትልቅ ሸለቆ አገኙ። የመሬቱ ከፍታ፣ አየሩን በማለዳ ቀዝቀዝ ያለና ተስማሚ እንዲሆን ሲያደርገው ምሽቱ ግን ቀዝቃዛና ርጥበት አዘል ነው። አንዱን ሸለቆ ከሌላው የሚከፍለውን ትንሽ የከረብታ ከፍታ፣ መለስ ብለው ሲመለከቱት እጅግ ድንቅ የሆነ የመሬት አቀማመጥ መመልከት ቻሉ። በአረንጓዴ መቀነት የተጠቀለለው የተራራው ምድር እነርሱ የተጓዙበትን የእግር መንገድ መልሶ የሚያሣይ በረዥምና ወገቡን የሚጠመጥም ሉላ ጠባሣ ዓይነት ምልክት ይታይበታል። አሁን ካሉበት እጅግ ከፍ ካለው መሬት ላይ ሆነው በዙሪያቸው ያለውን የቋጥኝና የዛፍ ክምችት ሲመለከቱት በአሸዋማ የባህር ዳርቻ ላይ እንደሚጋጭ ሞገድ ተጠቅልሎ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጉብ ብሎ፣ በግራጫው የት እየለሌ ምድረበዳ ላይ የተንበለጠለ ያስመስለዋል። በርቀት የሚታዩት እዚህም እዚያም የተበታተኑ የዘንባባ ዛፎችና እራፊ ጨርቅ የሚመሣስሉ ጥቂት ነጫጭ የእርሻ ማሣዎች፣ በሣር ቅጠሉ የርጭት ሞገድ የተወረወሩና ሞገዱ ወኋላው ሲመለስ የተበተኑ ይመስላሉ።

በአዲሱ ሸለቆ ግራና ቀኝ በብዛት የሚታዩት የጥድና የዱር ወይራ ዛፎች ናቸው። በአየር ውስጥ እየበረሩ የሚዘምሩ ወፎች፣ የቁራ ዘሮችና ግንደቆርቆሮች በዛፎች መካከል ይሰማሉ፣ ይታያሉም። የእግር መንገዱ በጣም ዳገታማና ወዲያው ወዲያው የሚጠማዘዝ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ሁለቴ ወይም ሶስቴ ከበላያቸው የተሸነቀረ ይመስላቸውና ያዩታል። የአበሻን ምድር እግራቸው ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ አንድም የሠፈራ ቦታ አላለፉም። ከአንዳንድ ፀጉራቸውን አጕፍረው፣ ግማሽ ርቃናቸውን ሆነው ከሠል የተሞላባቸው ጆንያዎችን ተሸክመው በመንገድ ላይ ኩስ፣ ኩስ ከሚሉ ምስኪን ሰዎች በስተቀር ሌላ ሰው አላጋጠማቸውም።

የዱር አውሬዎች አስፈሪነት የቀነሰ ቢመስልም፣ ሌሊት የጥበቃ ተራቸውን ተግባር ቀጥለዋል። ቀን ቀን የሚያዩዋቸው እንስሳት ትላልቅ፣ ጥቋቁር፣ ሠውነታቸው ቀጭን፣ እጆቻቸው የእግሮቻቸውን ያህል የሚረዝሙ የዝንጀሮ መንጋዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ዝንጀሮዎቹ በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው ቀልባጮች ይመስላሉ። በመጨረሻም ጫካውን ጨርሰው፣ የቢጫ አበባዎች ምንጣፍ በለበሠ ግራጫ የሣር ምድር ውስጥ ገቡ። እዚህ ቦታ ጥቂት ቅጠለ ቀጫጭንና የባአባብ ድንክዬ ዛፎች እዚህም እዚያም የበቀሉበት ነው። ከፍ ብሎ፣ ኾርው ያለውና እንደግርግዳ ቀጥ ያለው ገደል ወደ ተርተሩ ያመራል። ይህ የከፍተኛው የደጋ ምድር ሜዳ ጠርዝ ነው። እየቀረቡ ሲሄዱ፣ ይህ ጥቁር አጥር ከበላያቸው እንደምሽግ ግድግዳ ከአንድ ጥግ እስከሌላው ጥግ ይዘልቃል። ከዚህ ግዳግዳ መሠረት ላይ ተፈልጠው የተንከባለሉና የቆሙ የጥቁር ድንጋይ ቋጥኞች ይታያሉ። በጣም ንፁህ ቀዝቃዛ ምንጭ፣ በቡናማው ቋጥኝ ላይ ይቋጠርና ወዲያውኑ ቀጥሎ ባሉት ለምለም ሣሮች ውስጥ ይንቆረቆራል። በዚህ አረንጓዴ የሜዳ ላይ ትያትር ቤት ለከፍተኛው የደጋ ሜዳማ አገር እንደዘርፍ የሆነው የባልጐት ድንጋይ ቀለበት ሙሌት አቀማመጥ፣ ለነፍስ ሃሴትን የሚፈጥር ነው። በለስላሣው ሣር ላይ ተጋድመው፣ ንፁሁን ውሃ ተጐንጭተው፣ የፀሐይዋን ግለት ሞቀው፣ ለስለስ ባለው ነፋስ ቀዝቅዘው፣ ቀኑን ሙሉ በሃሣብ አርቀው እየተመለከቱ በከፊል እንደመተኛት እያደረጋቸው ዋሉ። እስከዚያች ሰዓት ድረስ ሃሣባቸው ሁሉ በህይወት ስለመኖራቸው ነበርና አይኖቻቸው ከፊት ለፊታቸው ባለው መሬት ላይ ተተክሎ ነበር። አሁን ግን ሰማየ ሰማያትን በማድነቅ ተውጠዋል።



ጆን ባፕቲስት፣ እያንዳንዳቸው በፀሎት ላይ ያሉ መሰለው። በተለይ ደግሞ ሃጅ አሊ ፊቱን ወደ መካ መልሶ ተንበርክኮ ስላየው ትክክል ነው። አባ ብሬቬደንት፣ አይኖቻቸውን በከፊል ጨፍነው፣ በሃያሉና በተመስጋኙ ፈጣሪ አጠገብ ስለክብሩ የሚዘምሩትን የምስጋና መዝሙሮች፣ የእምቢልታና የመለከት ድምፆችን ተስተጋብት የሚያዳምጡ ይመስላሉ። ከደማቁ የቤተክርስቲያን የፀሎት ስነስርዓት የተለየው እርሱ ብቻ ይህን በብቸኝነት የሚባክን ጊዜ ሊላመደው አልቻለም።

ሜትር ዠረሚ በአንድ ትልቅ ቋጥኝ ላይ ተቀምጦ፣ ሰማይ ሰማዩን እየተመለከተ በከባድ ተመስጦ ጭንቅላቱን ያወዛውዛል፣ ከንፈሮቹን ያነቃንቃል። ይህ የርሱ የፀሎት ዘዴው መሆኑን ፖንሴ በሚገባ ያውቃል። ዠረሚ በበኩሉ እርሱ ምንጊዜም በእግዚአብሔር እይታ ውስጥ መሆኑን ያምናል። ፀሎት፣ እሱና እግዚአብሔር የሚነጋገሩበት የተለየ ጉዳይ ያለበት ወቅት ነው። ፕሮቴስታንቶችም የርሱን ቃላቶች ጨርሶ አይሰነጥቋቸውም። እርሱ እንደሚለው ፈጣሪ ለፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ብዙ ሃላፊነቶች አሉበት ወይም የበለጠ ያስብልናቸዋል ይልና «ከሁሉም በፊት እርሱ ጀመረው።» ይላል። ምንጊዜም በደል መፈፀሙን ካመነ፣ ሜትር ዠረሚ የራሱን የመራከሪያ ሃሣብ እያቀረበ እግዚአብሔርን ይገስፃል፣ ወይም ለፈጠረው አምላክ ትዕዛዝ እስከ መስጠትም ይደርሳል።

ጆን ባፕቲስት በበኩሉ፣ ስማቸውንና መልካቸውን ለማያውቃቸው የሠማይና የምድር፣ የማይታዩ ሃይሎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እየተናዘዘ ምስጋናውን ያቀርብላቸዋል። ለረዥም ጊዜ መንገዱ ፍፃም ወደርስዋ እንዳመጣው በማሠላሠል አሲስን በሚያስደስት ስሜት ያስባታል።

# 8

በነርሱና በከፍተኛው ደጋማ ሜዳ መሃል ያለውን ያገጠጠውን የመጨረሻውን አለት ከመጋፈጣቸው በፊት፣ ሦስቱ ፈረንሣውያን የለበሷቸውን የተቀዳደዱትንና የቆሸሹትን ሱሪዎቻቸውን፣ ከመቶ ጊዜ በላይ በየውሃ ጉድጓዱ፣ በየኩሬውና በየተራራው ምንጮች ውስጥ እየተነከሩ በእድፍ የወፈሩትን አውሮፖዊ ልብሶቻቸውን አወለቁ። ሦስቱም፣ ረዣዥም ሰማያዊ ጃኬቶችንና የጭንቅላት ጥምጣም የአረብ ልብሶችን ለበሱ። ሃጅ አሊ፣ ሦስቱንም እንደተራ ግመል ነጂዎች አድርጎ እንደሚያስተዋውቃቸውም አስጠነቀቃቸው። እንዲህ ያለውን ቅፍለት የሚያውቁት አበሾች በሰላም ያልፏቸዋል።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ እንደምሰሶ በተገተረ የጥቁር ድንጋይ ግድግዳ መሬት ሥር ደረሱ። በዚህ ቦታ የመተንፈሻ ቀዳዳ የመሰለ የእግር መውጣጫና መንጠላጠያ ደረጃ እስኪያገኙ ስር ስሩን ተጓዙ። ከዚህ እጅግ ቀጥ ካለው አቀበታማ መንገድ መጨረሻ ላይ፣ በጥቁሩ ድንጋይ መካከል እንደ እባብ እየተጠማዘዘ የሚሄድ መተላለፊያ አግኝተው፣ በደጋማው መሬት የመጨረሻ ጠርዝ ላይ እንደ ቆጥ የተንጠለጠለች መንደር አገኙ።

ከዚህ በጣም አስቸጋሪ ከሆነው ምድር በላይ አስቀድመው ያዩት፣ በጠር መሠል ጣሪያው ላይ መስቀል ያለበት ባለስምንት ማዕዘን ቅርፅ ቤተክርስቲያን ነበር። እነርሱ ሲያልፉ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ስርዓተ ፀሎት ይካሄድ ነበር። በዚህ ፀጥና ረጭ ባለው ንፁህ አየር ውስጥ ከፍተኛ የሆነው መዝሙረ ዳዊት ሲዘመር የሙዚቃው ድምፅ የገደል ማሚቶው ይስተጋባል።

ከተማዋ ባሮችና ከብት ጠባቂ ነዋሪዎች ያሉባት ትልቅ የገበያ ማዕከል ከመሆን የበለጠች አይደለችም። ተወላጆቹ፣ በትከሻቸው ላይ ደበሎ ጣል አድርገው፣ በወገባቸው ዙሪያ የነጭ ጥጥ ጨርቅ አገልድመው፣ ጭንቅላታቸው ላይ ምንም ሳይለብሱ የሚጓዙ ናቸው። እስካሁን ካዩዋቸው ጥቋቁር ሰዎች ይልቅ የነዚህኞቹ የቆዳ ቀለም ፈካ ያለ ነው።

ሲናር የክርስቲያን አገር በነበረችበት በጥንት ዘመን ይህች ከተማ በሁለቱ አገሮች መካከል የጉምሩክ አገልግሎት የምትሰጥ ነበረች። ወደ ከተማዋ ለመግባት ሲሉ ያቋረጡት የግንብ ግድግዳ ይህን ያረጋግጣል። ሃጅ አሊ ቀደም ሲል ወደሚያውቀው ፀጥ ያለ የነጋዴ ቤት



ወሰዳቸው። ባለቤቱም፣ የአድመኛ ሹክሹክታ በመሠለ አነጋገር ሰላምታ ሰጣቸው። በአረቦች አለባበስ ስለቆዩ ደንገዝገዝ እስኪል ድረስ ማንም እንኳን አላስተዋላቸውም። በከተማዋ ውስጥ የሚታወቀው ሃጅ አሊ ማንነቱ እንዲታወቅ ለማድረግ ፊቱን ሳለማሸፈን ጥንቃቄ አድርጓል።

ከእንግዲህ በኋላ የሚያቋርጡት ምድረ በዳ ስለሌለ ያስተናግዳቸው ነጋዴ በሚቀጥለው እለት ግመሎቻቸውን በበቅሎ ሲለውጥላቸው ሁኔታዎችን አመቻቼ። ልውውጡ እነርሱ በሚጨምሩት መጠነኛ ገንዘብ ስምምነት ተቋጨ። አባ ብሬቬደንት፣ በነጋዴው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከቃጫ ገመድ በተሠራ አልጋ ላይ አዳራቸውን ከዋክብት እያዩ ውብ ሌሊት በማሣለፋቸው ይሁን ወይም በቤተክርስቲያኑ ጉልላት ላይ መስቀል በማየታቸው፣ በማግስቱ ጧት በጣም የተሻላቸው መስለው ታዩ። ሃጅ አሊ፣ንጉሱን በመወከል የኬላ ቀረጥ ለሚቀበለው ሠራተኛ ለመክፈል ፈጠን ብሎ ሄደ። እንደተመለሰ በጣም በማለዳ መንገዳቸውን እንደገና ተያያዙት።

በአጀማመራቸው ላይ፣ ዝግ እያለ የሚያድግ፣ በሃምራዊና ነጭ አበቦች፣በወፍ ዘራሽ አጃና ሌሎች አረሞች በተሸፈነ ኮረብታ ላይ ተጓዙ። ከዚያ በመቀጠል ነፋስ እንደልብ በሚያልፍበት ልክ አማንያን እንደሚቀመጡበት የካቴድራል ረዥም መቀመጫ ያለው በሚመስል ለውበት ሲባል እንደተሠራ ወጋግራ፣ በዛፎች ግንዶች፣ በተዋቀረና በቀስት ቅርፅ ከፍ ብሎ በቅርንጫፎች በተሠራ ጣሪያ መሠል የጥድ ጫካ ውስጥ መግባታቸውን አወቁ። ግራ የተጋባውና ደካማ ከሚመስለው የግመሎች መንቀራፈፍ ይልቅ በቅሎዎቹ ሳይጣደፉ በዝግታ ያስግራሉ። ቀጥታ ሃይሏን በምታሣርፈው ፀሐይ ውስጥ አየሩ ሞቃት ቢሆንም፣ ከበረሃው አፒራማ ሙቀት ይልቅ የሚያነቃቃና የሚያስደስት ነው። አንዳንድ ጊዜ በዛፍ ስር ሲያልፉ ወይም በሠማይ ላይ የሚንቀሣቀስ ደመና ጥላውን ሲያሣርፍባቸው ያልጠበቁት አዲስነት በውስጣቸው ሲፈጠርባቸው አውሮፖን ያስታውሳቸዋል። ይሁንና ይህ የአካባቢያዊ ባህርይ ለውጥ ውጤት፣ ለተጓዦቹ የሚስማማ አልነበረም። በምድረበዳው እጅግ አስቀያሚ የአየር ጠባይና ድርቀት ሰውነታቸው ክፉኛ ተጎድቶ ስለነበር፣ አሁን ደግሞ በእንግሊዊነት የተረጋጋና ቀዝቀዝ ያለ ሲሆን በጤናቸው ላይ ሲደርስባቸው የነበረው ጉዳት ሁሉ መውጣት ጀመረ። በመጀመሪያው ቀን ሌሊት ጥቂት ጎጆዎች ባሉበት አንድ መንደር እረፍት ለማድረግ ሲሉ ሰፈሩ። ሜትር ዡርሚ፣ ሥንሴን ጠርቶት እግሩን ገልጦ አሳየው። ከቁርጭምጭሚቱ ከፍ ብሎ ሲሠረጉድ የሚፈልግ የመሰለ የቀላ ቆዳው ላይ የጊኒ ትል እንደ ነጭ ክር ጫፍ ጭንቅላቱ

ብቅ ብሏል። ጆን ባፕቲስት፣ የዶሮ ላባ እንዲመጣለት ካደረገ በኋላ፣ የዚህን ደም መጣጭ ትል የመጀመሪያ አካል በዘግታ ጠቅልሎ አነሣውና ሁሉንም ነገር በቦታው አድርጎ ጠቅልሎ አሠረው።

ጆን ባፕቲስት ራሱም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበረም። ያንቀጠቅጠዋል። መገጣጠሚያዎቹን ይቆረጣጥመዋል፤ ራሱንም ያመዋል። ሴሲቱን ሙሉ ጥርሶቹን ሲያንገጫግጫቸው ነበር ያደረው። ማለዳ ላይ የጆስዊቱ ሁኔታ ጭራሽ እንደባሰበት አዩ። ከንፈሮቻቸው ደርቀው፣ ደረቅ ሣል እያሣላቸው፣ ግንባራቸው በላብ ተዘፍቆ ተመለከቱ። ሌላው ቀርቶ ለዚህ አይነት ጉዞ ልምድ ያለው ሃጅ አሊ ሣይቀር፣ ለሆድ ሕመም መድሀኒት እንዲሰጠው ፖንሴን ጠየቀው።

በዚህ መንደር የሚቆዩበት ጊዜ የላቸውም። ደህንነታቸው የሚረጋገጠው የአምስት ቀን ጉዞ በሚቀራቸው በዋናው ከተማ ጐንደር ሲደርሱ ብቻ ነው። በከፊል ብቻ ንቁ ሆነው፣ ስሜታቸው በትክሣት ተጐድቶ፣ በድንዛዜ ተውጠው፣ የአገሩ ድንቅ ባህሪያት ብቻ አጅቧቸው የጉዟቸውን የመጨረሻ ክፍል አጠናቀቁ። በትውስታቸው ውስጥ ያለው፣ ከአስተሳሰባቸው ጋር ተምታትቶ ደብዝዞ እያጠፋባቸው፣ በሠውነታቸው ውስጥ የሚሠማቸው ህመም የፈጠረባቸው፣ የስሜት ስሜቱ ጠፍቶባቸው የምድሩ መልክ ብቻ ጠንካራ አሻራውን አሣረፈባቸው።

ከፍያለው፣ እያደገ የሚሄደውና የሚጓዙበት ኮረብታ በባህር ዳርቻ እንደሚገኝ ተራና ግልፅ የትያትር ቦታ፣ የመሬት የተፈጥሮ መሠረቷ ይመስላል። እየተከተሉት የሚሄዱበት የእግር መንገድ ወደ ኮረበታው የመጨረሻ ጠርዝ ሲያደርሣቸው፣ ቁልቁል የሚመለከቱት ሸለቆ የአቧራና የውሃ እንፋሎት ጭጋግ ሸቅብ የሚነሣበት፣ የነርሱን የት እየለሴ ከፍታ የሚገልፅ ሳይሆን በተቃራኒው በሚጨስው የመሬት የውስጥ አካል ላይ አፉን የከፈተ ጭራቅ መስሎ ይታያል። ለቅፅበት ያህል መንገዱ ከገደሉ ከንፈር ትንሽ ለወጥ ብሎ ቢሄድ ከራሱ ከደጋማው ምድር ላይ ሽቅብ የሚነሣ፣ ግርጌው በተለያየ ሣር ቅጠሎች የተሞላ፣ ጫፉ ግን አንዳች ነገር የሌለበት ደራቂቻ፣ ቀዝቃዛና ሕይወት አልባ የቋጥኝ ተራራ ያያሉ። አንዳንድ ቦታዎች ላይ እነዚህ የተራራ ጫፎች ግዙፍ የቋጥኝ መጠን፣ ከውስጣቸው ሊወድቅ የተቃረበ የግራጫ ድንጋይ ሃውልት ይመስላሉ።



አልፎ አልፎ፣ ሁለት ጉዳዮች በአንድ ጊዜ ያጋጥማሉ። የመንገዱ አንደኛው ጠርዝ ተንዶ እልም ያለ ገደል ሲፈጠርበት፣ ሌላኛው ጐኑ ደግሞ ብቻውን የተመዘዘ የቡግር ድንጋይ ተራራ ይሆናል።

ባለፈው ምሽት ባረፉበት በገበሬው ጐጆ ውስጥ ካዩዋቸው ሰዎች ሌላ አንድም ሰው በመንገድ ላይ አልተመለከቱም። ከአናታቸው ላይ ቀኑን ሙሉ ጥንድ ንስር አሞራዎች ሲያንዣብቡባቸው ዋሉ። ምንም እንኳ እንስሳውን ባያዩትም የገዘሆን ፋንድያ ተመለከቱ። ከእለታት አንድ ቀን ደግሞ በእበሻዎቹ ዘንድ አጅግ ጣፋጭ ናቸው ተብለው የሚገመቱ አጋዘን የሚባሉ የዱር ፍየሎች መንጋ አጋጠማቸው። ሃጅ አሊ፣ ከነዚህ የዱር ፍየሎች አንዱን በሽጉጡ እንዲገድልላቸው ፖንሴን አጥብቆ ቢጠይቀውም፣ ፈረንሣዊው ሰው ይህን ለመሞከር የሚዘገንን ጉዳይ ሆነበት።

በመጨረሻም ከጐንደር የግማሽ ቀን የእግር ጉዞ ርቀት ላይ ከምትገኘው ከባርካ ከተማ ደረሱ። በዚህ ወቅት ንጉስ ነገስቱ በግዛታቸው ውስጥ ከተቀሰቀሰባቸው አመፅ አንዱን ለመደምሰስ ከዋና ከተማዋ መውጣታቸውን ሃጅ አሊ አወቀ።

«ቀደም ብለን ጐንደር ለመድረስ የምንጣደፍበት ምክንያት የለም። ንጉሡ እስኪመለሱ እዚህ ሆናችሁ ብትጠብቁ የተሻለ ነው። ወዳጄ የሆነ ሰው ከቤቱ ደብቆ ያቆያችኋል። እኔ ወደ ከተማ እሄድና ጊዜው ሲደርስ ልወስዳችሁ እመጣለሁ» አለ ሃጅ አሊ

የግመል ነጂውን አነጋገር ፖንሴ እምብዛም አላመነም። ያላቸውን ሁሉ በማጭበርበር ስለወሰደባቸው ይቅር ሊለው አይችልም። ለንጉስ ነገስቱ ካመጡላቸው የእጅ መንሻ በስተቀር ሁሉም ንብረታቸው በነጋዴው እጅ ወድቋል። ሌላው ቀርቶ አሁን የለበሷቸው የአረብ ሸሚዞች ሳይቀሩ የርሱ እንደሆኑና ንጉሱ የመጀመሪያውን ወርቅ ሲከፍሏቸው እንደሚመልሱለት ሲያስታውሳቸው አላፈረም። ሃጅ አሊ ጭራሹኑ ትቷቸው እንዳይቀር እየሰጋ፣ ጆን ባፕቲስት እያዘነ፣ ሲሄድ ግን ዝም ብሎ ተመለከተው።

እንደ እድል ሆኖ ጤንነታቸው መሻሻል ጀመረ። በሜትር ዝርጋሚ እግር ላይ ወጥቶ የነበረው የጊኒ ትል ዕለት በዕለት ትንሽ በትንሽ እየተጠቀለለ ይወጣል። በዚህ የተነሣ በቅርቡ ይድናል። የጆስዊቱ ሁኔታ ግን በጣም አሣሰባቸው። ሃጅ አሊ ያገኘላቸው ቤት ከእንጨት

ተሠርቶ፣ በጭቃ፣ በጥድና በክብት እበት ድብልቅ የተመረገ ነው። ወለሉ በቆሻሻ የተሞላ ነበር። በአጠቃላይ አንድን በሽተኛ ሰው ለማስታመም የሚሆን አመች ቦታ አልነበረም። ጊዜያዊ በሆነችው ጠባብ አልጋቸው ላይ የተኙት ምስኪኑ ዮሴፍ፣ ዕለት በዕለት ይበልጥ ወደ መቃብራቸው ይጠጉ ጀመር። ሰውዬው ብርታታቸውን ከሚገባው በላይ ገምተው ነበር። ለተልዕኳቸው የነበራቸው ፍፁም ታዛዥነት፣ እንደርሣቸው ያለ ፀጥ ያለ የቤተመፃሕፍት ምቹትን የለመደ ምሁር፣ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ጉዞ ላይ የሚገጥማቸውን ፈተና በሰንሰለት ተቆራኝተው እንደተፈረደባቸው ሰዎች በፅናት እንደሚወጡት እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። ነገር ግን እያደር የሚጨምረው ድቀታቸው ሰውነታቸውን ለበሽታ ስላጋለጣቸው፣ የጥድ እንጨት እሣት ቀኑን ሙሉ እንዲነድና እንዲሞቃቸው ግድ ሆነ። ጂስዊቱ በርግጥ በሚያሣዝን ሁኔታ ላይ ነበሩ። ረኀብሙና ግዙፉ ሰውነታቸው እንደዛረገ ጥምልምል አለ። የሚተነፍሱት በአፋቸው ስለሆነ ከራሳቸው ሰውነት የሚመጨነው የትኩሣት ሙቀት ከንፈሮቻቸውን አደረቀባቸው። ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ በካህኑ አልጋ አጠገብ ተራ በተራ መቀመጥ ጀመሩ። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ፕሮቴስታንቱ ሲያደርግላቸው የነበረው ርህራሄ እየተዘነጋቸው፣ ይህ መናፍቅ አጠገባቸው መሆኑን ህሊናቸው መለስ ሲል ሲያውቁ፣ ፍፁም የጥላቻ ርግማናቸውን ይገልፃሉ። ጤናቸው እንደሚመለስና እንደሚድኑም ስለሚያምኑ ተልዕኳቸውን እንደሚፈፅሙ ያምናሉ። አንዳንድ ጊዜ በሚያስደስት ቅላፄ ከውስጥ፣ ከአንጀታቸው መንጭቶ አቢሲኒያን እንደምን የሃይማኖታቸው መስመር ተከታይ እንደሚያደርጓት ታላቁን እቅዳቸውን ለረዥም ሰዓት ያብራራሉ።

«አስቀድሞ የምንፈልገው የአቢሲኒያን ህዝቦች ባህል፣ ጠባይና ቋንቋ መገንዘብ ነው። አዎን፣ ቋንቋቸውን ማወቅ ነው። እዚያ እንደደረስን እኔ ቋንቋውን ማጥናት እጀምራለሁ። ስለቋንቋው ፈረንሣይ ውስጥ መጠነኛ ነገር ተምሬአለሁ። በርግጥ የሚናገረው ሰው የለም። ሰዎችን ለማግባባት የሚያስችለው ጉዳና ቋንቋ ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ እምነታቸው . . . አስቀድመህ ግን በትክክል ልታውቃቸው ይገባሃል። ትልቁ ምስጢርም ይኸው ነው። አውሮፖ ውስጥ እምነት ያልነበራቸውን አረማውያን ባህላዊ ክብረ በዓላት፣ ቀናቱ፣ ቦታዎቹና አስተሣሰቦቹ ተመሣሣይ ሆነው የቤተክርስቲያን ስርዓቶች ተክተዋቸዋል።»

አንዳንድ ጊዜ በአልጋቸው አጠገብ ያለው ማንም ይሁን ማን ጨበጥ ያደርጋሉ። በመጨረሻም ፖንሴ እየመሠላቸው በስህተት ከሜትር ዠረሚ ጋር ሣይቀር ያወሩ ነበር።



«በእያት ቅድመ አያቶቻችን የተፈፀሙትን ስህተቶች እንደግማቸውም። ልክ አይደለም እንዴ? አስቀድመን ሕዝቡንና ካህናቱን ሳንለውጥ በፊት ንጉሡ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ መደረግ የለበትም. . . »

ጂስዊቱ በጣዕረሞት ተይዘው ሣሉ እንኳ፣ ውርደትን በትህትና ለመቀበል የነበራቸው ፈቃደኝነት፣ ይህም የታላቅ ክብራቸው መገለጫ መሆኑን ያሣዩ ነበር። የሃይማኖት ማህበራቸውን ደንብ በፍፁም ታዛዥነት ሲቀበሉ ሁሉንም አይነት ግላዊ ምኞቶች ይክዱናሉ። ይህን የሚያደርጉት ሥልጣንን በሙሉ ሃይል ለመጠቀም ከዘመናት በፊት የታቀደውን የተጠራቀመ ጉጉት ለማገልገል ሲሉ ነበር። አንድን ንጉስና ግዛቱን ለመግዛት አስቀድሞ በውሃ ቀጅነት ማገልገልን የሚመርጡ ሰው ነበሩ። ጆን ባፕቲስት፣ ለካህኑ አኳኋን፣ ጥንካሬና ብስለት አትኩረት ቢሠጥም፣ የጂስዊቱ ህመም እየጠናባቸው መጣ። ቄሱም በቅርብ እንደሚሞቱ አወቀ። የመሞታቸውን ሁኔታ ሲረዱ የታዛዥነት ፍቅራቸው አዲስ መስመር አበጀ። ለቅዱስ ተልዕኳቸው ፍላጐት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ቢያስገዙም፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የሚለውን ሃሣብ ተቀበሉ። ራሣቸውን ሙሉ በሙሉ በህመማቸው ስር በመጣል፣ የተወሰነው ዕጣ ፈንታቸው ለዚህ እንደላካቸው መግለፅ ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ቀጣይ ህክምና መስጠት ጥቅም አልነበረውም። ሃጅ አሊ እያምባረቀባቸው ትዕዛዝ ይሠጣቸው እንደነበረው ሁሉ ለሞት ጥሪም ታዛዥ ሆነው ከሁለት ቀን በኋላ አረፉ።

ፖንሴና ዠረሚ በግቢው ውስጥ ያለው የግራር ዛፍ ባጠላበት ቦታ ቄሱን ለመቅበር ፈለጉ። ይሁን እንጂ ያረፉበት ቤት ባለቤት፣ ቤቱን የሠራው ቅድመ አያቱ አጅግ ከፉኛ ታመው ሲሞቱ የተቀበሩበት ቦታ በመሆኑ አይሆንም አላቸው። ይህንን መጥፎ የጉዞ ጓደኛ አስከሬን በዚያ ውስጥ በመጨመር፣ መቃብሩን ለዘላለም ማርከስ ከጥያቄ ውጭ ነው ሲል ባለቤቱ ተቃወመ።

በዚያን እለት ማታ ወደ ባቂላ ማሣ በሚወስደው ጠባብ መንገድ፣ ጠፍ በሆነ መሬት ዳርቻ ላይ ጠለቅ ያለ ጉድባ ቆፍረው የጂስዊቱን አስከሬን ቀበሩ። የተከፈኑት በለበሱትና ሃጅ አሊ ሁጊዜም እየተቆጩ በሚያጠራበት የአረብ ሸሚዛቸው ነው። መፅሃፍ ቅዱስን በመጥቀስ ሜትር ዠረሚ አጠር ያለ ፍትሃት ሲያደርግ፣ በዚያ ቦታ የነበረው ብቸኛው ካቶሊክ ፖንሴ፣ እንዲህ ላለው ሥነ-ስርዓት ልምድ የሌለው በመሆኑና ምን ማድረግ እንዳለበትም ስለማያውቅ

ሜትር ዠረሚ የጀመረውን መዝሙር ሳይጨርስ በፊት በእጁ አፈር መመለስ ጀመረ። ዠረሚ ለረዥም ዓመታት መከራቸውን ሲጋሩቸው ቢሰነብትም፣ አሁን ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመቃብር ውስጥ ሲጠልቁ ተመለከተ። ወዳጅነቱን ሲሰጣቸው የነበረው ጆን ባፕቲስትም፣ ይህ ውለታው ፍፁም እንደማይረሣበት ርግጠኛ ሲሆን አልቻለም።

መፅሐፍ ቅዱሱን ካጠፈው በኋላ «ከነፃነት ለመሸሸ የዚህን ያህል ርቆ የተጓዘ ሰው የለም» አለ ሜትር ዠረሚ። ይህ መግለጫ በምስኪኑ ቄስ መቃብር ላይ የሚፃፍ ታሪክ መሆኑ ነው።

ሁለቱ ጓደኞች ወደ ቤት ሲመለሱ ስለምስጢራዊው አህጉር፣ ስለጠፋው ህፃን፣ ስለሞቱ ተስፋዎችና ስለተረሱት ያለፉ ዘመናት በሃሣብ ተውጠው ነበር። ምንም እንኳን በቄሱ ሞት ክልብ ቢያዝኑም፣ አጣናቸው የሚል ስሜት አልነበራቸውም። እንደገና መነጋገር ሲጀምሩ፣ የቄሱ ህይወት ከዕረፍታቸው የባሰ አሣዛኝ እንደነበረ ተስማሙ።

በሚቀጥለው ቀን ስለቄሱ የነበራቸው ሁኔታ በሙሉ ተወግዶላቸው ነበር። ይልቁንም ከእንግዲህ በኋላ እንዳያመልጣቸው አጥብቀው የሚይዙት አዲስ የፍስሃ ስሜት በመሃከላቸው ተፀነሠ። ሃጅ አሊ ከሄደ ከሶስት ቀናት በኋላ ተመለሠ። በአበሻዎች የአለባበስ ዘይቤ ብሩህ ቀለም ባላቸው ክሮች የተጠለፈ ነጭ ቀሚስ ለብሶ፣ ሽቶ ተቀብቶ፣ ፀጉሩን ወደ ኋላ ለቅቆትና ሌላ ሰው መስሎ ተመለሰ። የዮሴፍን ዜና እረፍት ሲነግሩት ልክ አንድ በቅሎ የጠፋው ያህል ስሜት አሣየ። ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጥ በቀጥታ የሚያነጋግራቸውን ጉዳይ ጀመረ።

«ንጉስ ነገስቱ ዛሬ ጐንደር ይገባሉ። ስለዚህም ሕዝቡ እንዲሰበሰብ መጠየቅ ይኖርብናል።» ሲል ጀመረ

«በስንት ሰዓት?» ሲል ፖንሴ በፍጥነት የመልቀቅ ሃሣብ በውስጡ ተፈጥሮ በደስታ ጠየቀ።

«ይህ የሰዓታት ጥያቄ ሳይሆን የቀናት ነው»

«የቀናት? ንጉሱ ለመታከም ጉጉት የላቸውም?»



«በርግጥ አላቸው። ነገር ግን ፈረንሣውያን ሃኪሞች እንዲመጡላቸው ማድረጋቸውን ከመግለፃቸው በፊት የሹማምንቶቻቸውን አዕምሮ ዝግጁ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እስከ ዛሬ ድረስ እናክምዎታለን እያሉ ሲያታልሏቸው የነበሩትንና ያልተሳካላቸውን ሰዎች ማረጋገጥም ይኖርባቸዋል።»

«እኛ ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዘን ልናድናቸው ወይም ልንገድላቸው መምጣታችን እስከንደርስ ድረስ እነዚህ የተባሉት ሰዎች ረዥም ጊዜ ነበራቸው» አለ ጆን ባፕቲስት

«ምን አልባት» ሲል ሃጅ አሊ ከአዲሱ አኳኋኑ ጋር መረጋጋትን ለመጠበቅ ሲል መልሱን ጀመረ። «ተመልሼ ወደዚህ አገር መምጣቴንና የተሠማራሁበትንም ተልዕኮ አውቀዋል። የንግስቲቱ ደንገጡሮችና አሽከሮች፣ ለፈረንሣውያን ጥላቻ ስላላቸው አንድ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ወስነዋል። ቀሣውስትና ትንቢት ተናጋሪዎች ነን የሚሉት እነዚህ ቡድኖች፣ ንጉሡ ላደረሱባቸው ውርደት ብቀላ እንደሚፈልጉ ማወቅ አለባችሁ። የመጨረሻውን ወታደራዊ ዘመቻቸውን ለማድረግ ሲንቀሣቀሱ ሲሉ ከተለመደው የበለጠ ብሩህ የሆነና እጅግ በጣም ረዥም ጅራት የነበረው ተወርዋሪ ኮከብ ታይቶ ነበር። ትንቢት ተናጋሪዎቹ፣ ንጉሡ እንደሚሸነፉና ጭራሹንም እንደማይመለሱ ተንብየው ነበር። ይሁን እንጂ ድል አድርገው ተመለሱ። አሁን ደግሞ የርሳቸውን ፍቅርና ድጋፍ መልሰው ለማግኘት ሌላ ዘዴ እየፈለጉ ናቸው።»

«እና አሁን ደግሞ ምን ዘዴ ሊጠቀሙ ነው ያቀዱት?»

«ባለፈው ዓመት አንድ ታላቅ ቅዱስ ሰው ከላሊበላ በሰልፍ ታጅበው እንዲመጡ አቅደው ነበር። ሰውዬው ላለፉት ሃያ ዓመታት ምግብ ሳይበሉና ውሃ ሳይጠጡ የኖሩ መነኩሴ ናቸው»

«ሃያ አመት!» አሉ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ፣ ቅዱስነታቸው ላይ በሚቀለድ የድምፅ ቅላፄ

«ይህ የሚቀለድበት አይደለም፣ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው። ቅዱሱ ሰው በማንም ሊታዩ የማይችሉ ናቸው። በአንድ አጉበር ውስጥ ተኝተው ነው ያሉት። ቃሬዛቸውን የሚሸከሙ

አራት መነኮሣት ናቸው። ከፊት ለፊታቸው ፖትርያርኩና ረዥም የወርቅ መስቀል በመያዝ እየዘመሩ የሚራመዱ ደርዘን የሚሞሉ መነኮሣት ከብበዋቸው ይጓዛሉ። ከኋላቸው ደግሞ በባዶ እግራቸው የሚጓዙ ሠላሣ ወጣት ተዋጊዎች ተከትለዋቸዋል።»

«እናም የጠጅ በርሜሎችን የተጫኑ ደርዘን በቅሎዎችም አሉ?» አለ ሜትር ዠረሚ በማሽሟጠጥ ሣቅ።

«መነኩሴው እዚህ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ በፀሎት ላይ ናቸው?» በማለት አተካሮውን ወደጐን በመተው ሃጅ አሊ ቀጠለ «ዛሬ በጠዋት ንጉሱን አይተዋቸው፣ የድንግል ማርያምን ምስል ጭነውባቸው ነበር። ነገ ተመልሰው የእግዚአብሔር ቃል የተደገመበትን ፀበል እንዲጠጡ ይሰጧቸዋል»

«እንዲጠጡ በምን መልክ» ሲል ጆን ባፕቲስት ኮስተር ብሎ ጠየቀ።

«ጉዳዩ በምስጢር ተሸፍኖና ተደብቆ ነው የሚከናወነው። መነኩሴው ሌላ ሰው ሊይዛቸው የማይችላቸውን ብዙ ቃላት ያኘጉድጉዳሉ። የምስጢሩ እምብርትም ይህ መሆን አለበት፣ አለበለዚያማ ድርጊቶቻቸው ቀላልና የሚታወቁ ናቸው። ንጉሡ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው መኮንኖች ሥርዓቱን በሚገባ አይተው ነው የገለፁልኝ። ቅዱስ መነኩሴ፣ የእርሣስና የቀርቆሮ ቅይጥ በሆነ ክታብ ላይ ባህርይውና ምንነቱ ምስጢር ሆኖ የሚቀር አንድ ቃል ይፅፉበታል። ከዚያ በኋላ ይህን ብርቱ ቃል ፀበል በያዘ ጉድጓዳ ሣህን ውስጥ ይከቱትና በሰሁፍ ላይ ያለው ቀለም ይሟሟበታል። ከዚያም ውሃውን ንጉሡ ይጠጡታል።»

«ይህን አይነት ተግባር ለምን ያህል ጊዜ ነው ተደጋግሞ የሚከናወነው?» ሲል ጆን ባፕቲስት ለስለስ ብሎ ጠየቀ

«ሁለት ጊዜ ብቻ»

«ለውጥ ማሣየት ከመቻሉ በፊት ምን ያህል ቀናት ነው በዚህ ላይ የሚሰነብቱት?»



«በአንድ ሣምንት ውስጥ የማይሻላቸው ከሆነ ንጉሡ ያሣውቁኝና እናንተ እንድታክሟቸው ይጠሯችኋል»

«በሆነ መልካም ዕድል ቢድኑስ?»

«በሆነ መልካም ዕድል ቢድኑስ?» አለ ሜትር ዠረሚ። «በእርግጥ ይሆናል አይባልም፣ ሕክምና ነው። በአንድ ጊዜ የማይሠራ ከሆነ መጠኑን ከፍ ለማድረግ መሳውን መፅሃፍ ቅዱስ በአንድ ኩባያ በጥብጦ እንደመጠጥ ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ነው»

«ከዳኑ ግን እኛ እንመለሳለን» አለ ሃጂ አሊ

«ማናያቸው»

«ምንም እንኳን እናንተ እንድትመጡላቸው የላኩት ንጉሱ ራሣቸው መሆናቸውን ህዝቡ ቢያውቅም፣ እናንተን ለማየት ግን ሊገጥማቸው የሚችል ከባድ አደጋ ሊኖር እንደሚችል ልትረዱ ይገባል። በአያታቸው ዘመን፣ ጀስዊቶች አገሪቱ ሃይማኖትዋን እንድትለውጥ ካደረጉት ሙከራ በኋላ ንጉሦቹ ሙሉ በሙሉ ነፃ አይደሉም። ካህናቱና ካቶሊካዊነትን የሚቃወሙ ሁሉ በጥብቅ ይከታተሏቸዋል። አንዲት እጅግ አነስተኛ የስህተት እርምጃ ካዩ፣ ከንጉሡ የብረት እጅ ራሣቸውን ነፃ ለማድረግ ማንኛውንም ዓይነት ሴራቸውን ያድማሉ። ፈረንሣውያን ቀሣውስት አሁንም ቢሆን አግባብነት ባለውም ይሁን በተንኮል ወደ አገሪቱ ለመግባት ተስፋ እያደረጉ መሆናቸውን እያንዳንዱ ስለሚያውቅ ይጠነቀቃሉ። የአገራቸውን የውስጥ ሰላም ለማስጠበቅ ሲሉ ንጉሡ የህክምና ክትትል እየተደረገላቸው ነው የሚል የይቅርታ መጠየቂያም ሣያስፈልጋቸው ሊያባርሯችሁ ይችላሉ።»

ይህን የሚረብሽ ዜና ከነገራቸው በኋላ፣ ሃጅ አሊ ወደ ቤተመንግስት ለመመለስ ትቷቸው ሄደ። እነርሱም ብቻቸውን ቀሩ። በራስ መተማመናቸው አሁንም ጥብቅ ቢሆንም፣ በአጥር ግቢያቸው ውስጥ ተዘግቶባቸው በመቀመጣቸው አልተደሰቱም።

ከአስተናጋጆቻቸው ልጆች አንዱ፣ ወደ ገበያ ወጥቶ እዚያ ከሚሸጠው ከያንዳንዱ የእፅዋት ዝርያ ናሙና አመጣላቸው። ሁለቱ ጓደኛሞች በከፍተኛ ትጋት በምድር ላይ እንደዚህ ያለ ጠንካራና ውብ መዓዛ ያላቸው ዝርያዎች፣ ጥሩ ሽታ ያላቸው መድሃኒቶች፣ ማቅለሚያዎችና

ቅመሞች ያሉት አንድም አገር የሌለውን እነዚህን እፅዋቶች በየወገናቸው መለየትና ማስቀመጥ ጀመሩ:: መውቀጫቸውንና ማጣሪያዎችን አሻሽለው በሠሩት እንገተ ረዥም ጠርሙስ በመጠቀም ሜትር ዠረሚ የጓደኛውን የፖንሴን አመራር እየተከተለ ይወቅጣል፣ ያነጥራል፣ የሚበጠብጥና የሚደባለቀውን ሁሉ ይሠራል:: ጉዟቸው በጣም የጨረሰባቸውን መድሃኒት በክፊል የመጠባበቂያ ክምችት ሣጥናቸው ውስጥ ያስቀምጣሉ:: ንጉሡን ሣያዩዋቸው በዚሁ የሚመለሱ ከሆነ እነዚህን ያትክልትና የአዝዕርት ዝርያዎች ማግኘታቸውን ብቻ ይዘው ይመለሳሉ::

ሃጅ አሊ ካያቸው ከሶስት ቀናት በኋላ፣ ያረፉበት ቤት ነጋዴ በዚያኑ ዕለት ምሽት ወደ አዲስ ቤት መዛወር እንዳለባቸው ሊነግራቸው መጣ:: ሲመሽም ማንነታቸው እንዳይታወቅ ረዥሙን የአረብ ቀሚሳቸውን ለብሰው ከዋናው ከተማ የሚለያቸውን ርቀት ተጓዙ:: አነስተኛ ውን ጭነት የተሸከሙት በቅሎዎቻቸውም ከኋላቸው ተከተሏቸው:: ጉንደር ውስጥ በአረቦች ሰፈር ነዋሪ የሆነ ሌላ ሙስሊም ተቀበላቸው:: ለማረፊያነትም በጥሩ ሁኔታ የተጌጡ፣ መስኮቶቻቸው በጥልፍልፍ ብረት ተሠርተው ወደ ጠባቡ መንገድ የሚያሣዩ ሁለት ክፍሎች ተሰጧቸው:: ባለቤቱ ራሱ ምግብ ይዞላቸው በመምጣት ትዕግስት እንዲኖራቸው መከራቸው::

ከአንድ ሣምንት ጥብቅ ቆይታ በኋላ ሃጅ አሊ ፈልጓቸው መጣ:: ከአንድ ቀን በፊት የአበሻ ልብሶችን እንዲለብሱ በማለት ከነጭ ናይለን የተሰሩ አጫጭር ቀሚሶችና በትከሻዎቻቸው ላይ የሚደርቧቸው በጥጥ የተሰሩ ካባዎችን ልኮላቸው ነበር:: በማግስቱ ጧት፣ ሃጅ አሊ፣ የከርቻ እቃው በትላልቅ ላባና የሱፍ ኳሶች በቄንጠኛነት በተጌጠ አጭር ዳማ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ብቅ አለ:: ለኮ የጠለቀላቸውን ሁለት ፈረሶች እየመሩ የሚመጡ ባሪያዎችም ተከትለውት ነበር::

በሃጅ አሊ አመራር መሠረት ፖንሴና ሜትር ዠረሚ የአበሾችን ልብስ ለብሰው ተራ በተራ በፈረሶቹ ላይ ወጥተው በሰያፍ የዝግታ ሰግሪያ ወደ ቁስቋም ቤተመንግስት ተጓዙ::



# 9

«ቀጥል» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ በብስጭት:: «ደብዳቤው በሚቀጥለው የፖስታ ጉዞ እሌክሣንደሪያ መድረስ ካለበት ዛሬውኑ መጠናቀቅ እንዳለበት አትርሣ»

ሙሴ ማቹ ብዕሩን ይዞ ጠረጴዛው አጠገብ ተቀመጠ:: ባሣለፈው መጥፎ ለሊት ምክንያት አይኖቹ ደመና እንደለበሱ ናቸው:: በጨዋታ ሰዛ ያፈሰሱት የለቅሶ እምባ በበጋው ወቅት ከተማዋን ለወረራት የትንኝ መንጋ፣ ጥሩ የምግብ ፍላጐታቸውን የሚቀሰቅስላቸው ነበር:: ወንዶችም ሴቶችም አጠገቡ እንዳይደርሱ ሲደረግ ነፍሣቶቹ ግን እየተሣቡ ይመጡበት ነበር:: እንዳስመታደል ሆኖ የተለመደውን ቅነሳ ባለማድረጉ የራሱን ግላዊ የጤና አጠባበቅ ዘዴም ሰወጠው::

«ቆይ! ቆይ! እንይ» አለ ማንበብ ያቋረጠበትን ቦታ እየፈለገ «እዚህ ላይ ግን . . . ለክቡርነትዎ ልናዘዝና . . . እኒህ ባለፈው ጊዜ ከኤምባሲያችን ጋር የርሳቸውን የሃይማኖት ማህበረሰብ አባል መነኩሴ አብሬ እንድልክላቸው የጠየቁኝ ካፑቺን አባት፣ ትናንትና ከኔ ጋር ለመገናኘት ችለው ነው::»

«የለም፣ ይህ የዲፕሎማቲክ ቋንቋ አይደለም፣ አንድ ቆንሲል ለአንድ ቄስ አይናዘዝም»

«እንዲህ ብንለውስ፣ ክቡርነትዎ ሊያውቀው እንደሚችለው . . . »

«መጠነኛ ማሻሻል ነው:: ቀጥል»

«ክቡርነትዎ ሊያውቀው እንደሚችለው ቃለ ምልልሳችን ምንም አይነት ትህትና አልነበረበትም:: ምንም እንኳ አባ ፖስኳል ስለ እራሳቸው ብቻ በመናገር ትህትናና አክብሮትን የሚጠይቁ ውይይቶችን ብዙ ጊዜ ቢጥሉም፣ ሳዳምጣቸውና ሳግባባቸው ሞክሬአለሁ::»

«ይህ መጥፎ የሚባል አይደለም» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ አንድ እግሩን እየዘረጋ፣ በደብዳቤው መንፈስ ተደስቶና በዚያውም አሁን በቅርቡ ከፈረንሣይ በጀልባ የመጣለትን አዲስ አረንጓዴ የሐር የእግር ሹራቡን እያደነቀ::

«የመጨረሻውን ቃለ ምልልሣችን ተከትሎ የመልዕክተኞቻችንን ቅፍለት የሚከታተሉ ሰዎችን ላኩ። ካፑቺኖች የኛን መልዕክተኞች ሲናር ላይ ደርሰውባቸው ጥያቄዎቻቸውን ደጋግመው ገሰፁ። መልዕክተኞቻችን የጠፍ ጨረቃ ለሊት አግኟቸው ሸሹ። ይህም ሆኖ እነርሱን ለማግኘት ሁሉም አይነት ሙከራ ቢደረግም ዱካቸው ሊገኝ ሣይችል ቀርቷል»

«ለመሆኑ ነጠላ ቁጥር ነው እየተጠቀምክ ያለኸው?»

«ይቅርታ ክቡር ሆይ፣ አልሰማሁዎትም»

«ዱካ የሚለው «ቃል» »

«አዎን እንደዚያ ነው የፃፍኩት ፣ክቡር ሆይ»

«የብዙ ቁጥር አድርገው። በጉዟቸው ላይ በአንዳንድ እግራቸው ጡብ ጡብ እያሉ በአንድ ነጠላ ዱካ ላይ የሚሄዱ ይመስል ዱካ በማለት የማስረዳት ችግር አለ መሰለኝ»

«. . . እነርሱን ለማግኘት ሁሉም አይነት ሙከራ ቢደረግም ዱካዎቻቸው ሊገኙ ሳይችሉ ቀርተዋል።» በማለት «ዎቻቸውን ጨመርኩበት»

«ግሩም ድንቅ»

«የፈረንሣይ የልዑካን ቡድን በድንገት በመሸሹ የነቁት ካፑቺኖች ምርመራቸውን በመቀጠል አሸከር የተባለውን የዮሴፍን ማንነት ለማረጋገጥ ቻሉ። ጉዳዩን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ እንዲያውቁት ይደረጋል ሲሉ አባ ፓስኳል አረጋግጠውለኛል።»

«የኒያን ጅላጅል ሰው ስም አሁንም አሁንም ባንጠቅስ ጥሩ ነው። በቀላሉ . . . ይደረጋል ሲሉ ካፑቹኖቹ አረጋግጠውልኛል በለው»

ሙሴ ማቼ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣብ በማስታወሻው ያዘ

«ይህን ያልታደለ ጉዳይ በተመለከተ ክቡርነትዎ ሊመዝኑ የሚችሏቸው ሁለት የማጠቃለያ ሃሣቦችን ባቀርብ። አንደኛው መልክተኞቻችን እስካለፈው አንድ ወር ድረስ



በህይወትና በጥሩ ጤንነት ላይ ሲናር ውስጥ እንደነበሩ መግለፅ በዚያን ዕለት የት እንደነበሩ ተስፋ ማድረጋችንን ያስረዳል።»

ሙሴ ዱ ማይሌ እየተንጐራደደ ወደ መስኮቱ ሄዶ ውጭ ወደ አትክልቱ ውስጥ ተመለከተ።

«እናም ሁለተኛ፣ ምንም እንኳን በጣም ደካማና ሊቀየሩ የሚችሉ ቢሆኑም እነዚህ የሃይማኖት ጥያቄዎች በዲፕሎማሲያዊ ተግባራችን ውስጥ ውስብስብ ነገሮችን ማስከተል ጀምረዋል። በሁለቱ የሃይማኖት ማህበራት መካከል ያለው ፉክክርና አበሾች ለካቶሊክ ካህናት ያላቸው ግልፅ የሆነ ጥላቻ፣ ተልዕኳችንን ያውም የራሱ ችግሮች እያሉበት፣ በአደጋ ላይ እንዲወድቅ የሚያደርጉ ናቸው። በሌላ አነጋገር በጣም ቁልጭ አድርጌ ባስቀምጠው፣ ይህን ፕላን በራሣቸው ጥረት የተጠቀሙበት ጀስዊቶቹ ዛሬ ተመልሰው ይደራደሩበታል። በበኩሉ፣ ግርማዊነታቸው ይህን ተልዕኮ ሲያዝዙ ለመላው የክርስትና እምነት ጥቅም እንዲሰራ ተመኝተው ይመስለኛል።»

ካለፈው ምሽት ወዲህ ይህን ደብዳቤ ሲያነብቡት አራተኛ ጊዜያቸው ነው። ቆንሲሉ ይህንን ድፍረት የተሞላበትና ወደፊት ሊደርስ እንደሚችል የሚያምኑበትን የደብዳቤውን ፖለቲካዊ ክፍል ለመስማት አልሰለቹም። በዚያን ሰዓት፣ ሴት ልጁ በቆንስላው ጽሕፈት ቤት ለአጭር ጊዜ ብቅ በማለቷ ሃሣቡ ተበታተነበት። ጊዜ ጠልቶትና በቃህ ብሎት ለዘላለም ሲያስወግደው እንድታስታወሰው ማድረግ እንዲቻል የአባቷን ብልህነትና አርቆ አስተዋይነት አሰምሮዋ ትክክለኛውን ምስል ቀርፆ እንዲያስቀምጥላት፣ ይህን ዓይነት ድንቅ ዲፕሎማቲክ ሥራ ከርሷ ጋር ቢጋራው ምን ያህል ደስ ባለው።

«ስለዚህም የፈረንሣይ ንጉስ በዚህ ጉዳይ ላይ ከካቶሊክ እምነት ጋር እንደሚስማሙ ማሣረጊያ ግዴታችን ይሆናል» ሲል ሙሴ ማቼ ቀጠለ። «የምንጠብቀው ኤምባሲ እንደተመለሰ አንደኛ መቀበል እንደሚገባኝ ከክቡርነትዎ ለማወቅ አማክርዎታለሁ። የመንግስትን ጉዳይ ከሃይማኖት ጋር መደባለቃችንን እንቀጥልበት? ወይስ ዲፕሎማሲያዊና ሌላው ቀርቶ የንግድ ቁርኝቶች እንኳ ሚዛናቸውን ጠብቀው እንደሚተገበሩ እኛም ግርማዊነታቸውን ሙሉ በሙሉ በመወከልና ለግዛተ ዘውዳቸው ቀዳማይ ጥቅም ስንል እንስራ?»

«አሁን በጣም ትክክል እንደሆነ አምናለሁ» አለ ሙሴ ዱ ማይሌ በመመፃደቅ ዓይነት «እርማቶቹን ካስገባህ በኋላ እንደገና አንድ ጊዜ እናነበውና ከዚያ በኋላ ይላካል።»

ሙሴ ማቼ ብድግ አለና እንደ ፅሕፈት ቤት ወደምታገለግለውና ወደምታፍነው የእቃ ማስቀመጫ ክፍሉ አመራ።

ቆንሲሉ፣ ከወፍራሙ የመስኮት መጋረጃ በስተኋላ ትንሽ ፈቅ ብሎ ልጁ በመኖሪያ ቤቱ ያሉትን እፅዋት ልትንከባከባቸው ስትሄድ በስስት ተመለከታት። የደስደስ ያለውን ቁመናዋን፣ ረጋ ያለ አረማመዷንና ከሕፃንነት ወጥታ ኮስተር የማለቷን ሁኔታ አደነቀ።

ጋብቻ እንድትፈፅም መወሰን ያለብኝ ጊዜ ነው።

## ፳

«ይህች አውሬ የምትችለውን ሁሉ በማድረግ ልትጥለኝ ትፈልጋለች»

ሜትር ዠረሚ, ትንሿን ፈረስ ለመቆጣጠር ከብደቱን ሁሉ ተጠቀመ። ፈረሷ ግን በፍርሃት ዓይኖች ዘለለች። ሃጅ አሊ አንዱን አገልጋይ ሲያመለክተው ወዲያውኑ ለከንፈውን ያዘ።

«አሁን የመዝናናትና ግጼለሽ የሚሆንበት ጊዜ አይደለም።» አለ ጆን ባፕቲስት ልጓሙን በሁለት እጆቹ ጨብጦና ፈረሱ እንድትራመድ ጥረት በማድረግ ሲሳካለት።

ከአረቦች መኖሪያ ወጥተው፣መንደሩን ከዋናው ከተማ የሚለየውን አነስተኛ ምንጭ ተሻገሩ። ከዚህ በኋላ በሙስሊም ጥምጣም መሸፈናቸው ቀርቶ፣ ለሁሉም ሰው አውሮፓውያን መሆናቸውን በግልፅ ማሣየት ጀመሩ። በጠቦቹ የከተማው መንገዶች ውስጥ የሚጐርፈው ህዝብ እነርሱን በተመለከተ አንዳችም ጉጉት ሣያሣይ ረጋ ያለ ነበር። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶችም ነበሩ። በመጀመሪያ ደረጃ ለምድረ በዳው የፀሐይ ቃጠሎ ለረዥም ጊዜ ተጋልጦ የነበረው የሁለቱ ፈረንሣውያን ቆዳ ጠቆር ስላለ፣ ይህ ቀለም ከአቢሲኒያ ክርስቲያኖች ጋር ይቀራረባል። ሁለተኛ፣ ጐንደር ውስጥ በቁጥር ብዙ የውጭ ዜጐች ስለሚኖሩ ሕዝቡ የመልኩን ቀለምና ቅርፅ ለምዶታል። ብዙዎቹ ግሪካውያንና አርመናውያን ሲሆኑ ጥቂት



ደቡባዊ እስላሞች አሉባቸው። እነዚህ ሠዎች የአቶማንን የአገዛዝ ቀንበር ሲሸሹ፣ በአበሻው ንጉስ ጥገኝነት የተሠጣቸውና ጥበቃም የሚደረግላቸው ናቸው። በመጨረሻም እንግዶቹ ቀስ በቀስ የሚያውቁት አንድ ነገር አለ። አቢሲኒያውያን ስሜታቸውን ወይም አስተሣሠባቸውን በግልፅ ማሣወቅ አይወድዱም። በዚያም አለ በዚህ፣ ሁለቱ ጓደኛሞች ስለነዚህ ጉዳዮች ምንም ሳያስተውሉ ለረዥም ጊዜ ሲያልሟት የነበረችውን የዚህችን የተረት ተረት ያህል የምትታወቅ አገር አካል መሆናቸውን በደስታ እያሰላሰሉ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ጥቅጥቅ ያለውና ግራጫ መሆን ዳጀመረው የሜትር ዠረሚ ጺም፣ የብልህና የአዋቂ ሞገስ ሲሰጠው፣ የጆን ባፕቲስት በጣም ጥቁርና የተጥመለመለው ፀጉሩ፣ ትኩስ ቁመናው፣ ግርማ ሞገስ ያለው ዛላውና፣የመጓጓትና በደስታ የመሞላት ስሜቱ ጉን ለጉን ሲጓዙ ወጣት ሃብታም አስመስሎታል።

ወደ ቤተመንግስቱ በዝግታ እየወጡ ሳሉ፣ የተሠበሠበው ሕዝብ በመሃል እንዲያልፉ መንገድ ይለቅቁላቸው ነበር። ወንዶችም ሴቶችም አንድ አይነት ተራ ካባ፣ አንድ ውጥ በሚመስለው ቀጭን ትከሻቸው ላይ ለብሰዋል። ምጥጥ ያለው፣ የታወቀ ቅርፅና መጠን ያላቸው ትልልቅ አይኖቻቸውና ቀጥ ያለው ቁመናቸው፣ ጆንን ባላባቶች ያስመስላቸዋል። ድል ከተመቱ አገሮች የመጡ ባሮች ፊታቸው ሻክሮና ጐብጦ እርስ በእርሳቸው እየተለፋለፉ ሲጓዙ መለየት በጣም ቀላል ነው።

ከተማው አሁንም ቢሆን ጦራቸውን፣ የቆዳ ጋሻቸውንና በቅርቡ በተደረገው ዘመቻ የተያዙ እስረኞችን ይዘው በመንገዶች መሃል በሚንቀሣቀሱ የታጠቁ ወታደሮች እንደተሞላ ነው። አንድ ገለጥ ያለ፣ ከዚያም ሣር የሸፈነው አካባቢ ምናልባትም የስልፍ ወይም የስብሰባ ቦታ ሣይሆን የማይቀር ሲያልፉ ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ዞር አለ።

«ከትናንት ወዲያ ስለሠማነው ጉዳይ መግለጫው ይኸውና»

በቅርቡ ንጉሡ ድል ያደረጋቸው አንድ ሃያ ምርኮኛ ተዋጊዎች፣ አደባባዩ ውስጥ ያቃስቱ ነበር። ጥቂቶች ስብርባሪ ድንጋዮች ላይ ተቀምጠዋል። ሌሎች ደግሞ ክንዶቻቸውን ዘርግተው ቆመዋል። አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ደግሞ ጭንቅላቶታቸውን በእጆቻቸው ሸፍነው መሬት ላይ ተጋድመዋል። ሁሉም በነዚያ ጥቋቁር ፊቶቻቸው መሃል ሁለት የደም ምልክቶች በአይኖቻቸው ላይ ነበሩባቸው።

«የከሃዲዎች ቅጣት ነው» አለ ሃጅ አሊ

በድል አድራጊው ሰራዊት ተይዞ የመጣው የአማፂያን መሪ ተከስሶ በከፍተኛ ፍርድ ሰጪ አካል ሁለት አይኖቹ እንዲታወሩ ተፈርዶበት ቅጣቱ ከሁለት ቀናት በፊት ተፈፅሟል። እስረኞቹ አይኖቻቸው እንዲጠፉ ሲደረጉ፣ እሪታቸው በከተማው ሁሉ ውስጥና ሌሳው ቀርቶ ሁለቱ ተጓዦች እንዲቆዩ እስከተደረጉበት ቤት ድረስ ይሰማ ነበር።

ጉዟቸውን ወደ ቤተመንግስት ቀጠሉ። ጆን ባፕቲስት በኮርቻው ላይ ሆኖ ብዙ ጊዜ እየተጠማዘዘ ይህን አስደንጋጭ ትርዒት ሲመለከት፣ የተሰበሰበው ሕዝብ ግን ስተጉጅ ሰለባዎች ምንም ቁብ የሌለው ለማስመሰል ሲሞክር አስተዋለ። አንድ እስረኛ በጨለማው ውስጥ ሲጎዝዝ፣ በዳበሳም ቢሆን ወደ አንድ አበሻ ለመድረስ ቢሞክር ወይም እርምጃውን በመንገድ ላይ ለማድረግ ቢጥር አላፊ አግዳሚው፣ ውሃ በቋጠረ መንገድ ላይም ቢሆን ይዘላል ወይም መንገዱን ስቶ ለመጣ እንስሳ ጉዳናውን በመልቀቅ ምንም እንደማይመለከተው ሁሉ ገሸሽ በማለት ይተወዋል።

ቤተመንግስቱ፣ ዙሪያውን ድንኳኖችና ጊዜያዊ ሕንፃዎች ግዳግዳውን ተጠግተው ስለሚከቡት፣ የሚታይ ያህል አይደለም። በጥርብ ድንጋይ የተሠራ ግዙፍ ሕንፃ ሲሆን ጉንና ጉኑ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው ባለጉልላት ግንቦች አሉት። ሃጅ አሊ እየመራቸው ትልቁን ባለቀስት ቅርፅ የመተላለፊያ ጣሪያ ከጠባቂ ዘቦች ጋር ቃል ሳይለዋወጡ ከፈረሶቻቸው ወርደው፣ ፈረሶቻቸውን ለጠባቂዎች ሰጥተው፣ በአንድ ጨለም ባለ መተላለፊያ በኩል ሄዱ። በጣም ቀዝቃዛ የሆነና እምክ እምክ በሚሸት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ለአጭር ጊዜ ከጠበቁ በኋላ፣ ሁለት ትላልቅ መስኮቶቹ ከታች ወደሚታየው ግቢ የሚከፈቱ፣ ትልቅ የህዝብ መሠብሠቢያ አዳራሽ ውስጥ ይዘዋቸው ገቡ። ደርዘን የሚሆኑ ሰዎች በግድግዳው ዙሪያ ተሰልፈው የነርሱን መምጣት ይጠባበቃሉ። ሃጅ አሊ በጣም ጐንበስ ሲል፣ ጓደኞቹም እርሱን ሙሉ በሙሉ በመከረጅ ተመሣሣዩን አደረጉ።

ከቡድኑ መሃል አንድ ሰው ተነጥለው ወጡ። ሰውዬው፣ ከሌሎቹ ትንሽ ቀደም ብለው ቆሙ። በወርቀ ዘቦ የተጠለፈ ጥቁር ካባ ለብሠዋል። የወርቅ ሃብልም አጥልቀዋል። ፊታቸው ክብ ነው። ፀጉራቸው ጥምዝ ሆኖ በአጭሩ የተከረከመ፣ ፂማቸውም እንዲሁ በአጭሩ የተቆረጠ



ነው። የሜትር ዠረሚን ያህል ባይረዝሙም በእድሜ እኩያ ሳይሆኑ አይቀሩም። ለሰዎች ክፍ ባለ ድምፅ ተናገሩ።

«ይጠይቋችኋል» አለ ሃጂ አሊ «በእርግጥ ፈረንሳውያን ናችሁ?»

«ሰመሆኑ ማን ናቸው?» ሲል መልስ ከመስጠቱ በፊት ጆን ባፕቲስት በሹክሹክታ ጠየቀው።

«ራስ ዮሐንስ ናቸው። የግዛቱ እጌ ጀኔራል ሲሆኑ፣ ከንጉሡ ነገስቱ በመቀጠል እጅግ ከፍተኛው ባለስልጣን ናቸው።»

«ፈረንሣውያን ሲሉ፣ ካቶሊኮች ማለትዎ ከሆነ መልሣችን አይደለም ነው። ክቡር ሆይ፣ እኛ የታላቁ ንጉስ የሉዊስ አስራ አራተኛ ህዝቦች እንጅ የሮማ ቤተክርስቲያን ጳጳስ ሰዎች አይደለንም»

ባለፉት ረዥም የቆይታ ቀናት ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ ሲቀርቡ ይችላሉ ብለው በጣም በገመቷቸው ጥያቄዎችና በመልሶቻቸውም ላይ በስፋት ተወያይተዋል። አባ ዶ ብሬቬደንት ስለሌሉ ማንም ጥቃት ሊሰነዝርባቸው አይችልም። እንዲያውም በካቶሊክነት ላይ የሌሎች ሰዎችን አስተያየት ከቁም ነገር ሳያስገቡ ጭራሹን ጠላትነት እንዳላቸውና ራሳቸውን ከጀስዊቶች ማራቅን እንደሚመርጡ ለመግለፅ ወሰኑ። ይህ አደገኛ ጨዋታ ቢሆንም የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም።

ከጥቂት ቆዘማ በኋላ፣ ራሱ ወይም ዋናው ባላባት «መጣንበት የምትሉት አገር የት ነው?» ሲሉ ጠየቁ። ሃጅ አሊ እንደተረጐመው የእንግዶቹ የመጀመሪያ መልስ ትንሽ ያደናገራቸው ይመስላል።

«ከሲናር፣ ከግብፅ ማዶ፣ ከታላቁ ባህር ሌላኛው ዳር ላይ ነው ክቡር ሆይ»

የአቢሲኒያውያን የጂኦግራፊ ዕውቀት እስከነዚህ ሁለት አገሮች ብቻ እንደሆነ ጆን ባፕቲስት ያውቃል። በርግጥ ሌሎች ሕዝቦች ስለመኖራቸው፣ ስለፖርቹጋሎችና ስለኢጣሊያን ሲወራ ያውቃሉ። ነገር ግን የነዚህ ሕዝቦች አገሮች የት እንደሚገኙ ምንም ሃሣብ የላቸውም።

«በነዚህ ምድሮች ውስጥ ራሱን የክርስቲያኖች አለቃ ብሎ በሚጠራው ሰው አገዛዝ ሥር ያልሆኑ መሬቶች አሉ?»

ከሃምሳ አመታት በፊት ጄስዊቶች የጳጳሱን ትልቅ ሥልጣን በምዕራቡ ላይ ለመመስረት ሲሉ ያሰራፖትን ፕሮፖጋንዳ ጆን ባፕቲስት አስታወሰው።

«ክቡርነትዎ በርግጥ እንደሚያውቀው እንደ እድል ሆኖ ብዙ አሉ። ጳጳሱ የሰውን ነፍስ እንዛለሁ ይላሉ። ስለዚህም እነዚህን አገሮች አይገዙም። ነገስታት ግን፣ ከነዚህም መካከል አንዱ የኛ ናቸው፣ ብዙ ዓይነት ሕዝቦች በግዛታቸው ወስጥ ስላሉ ሌላው ቀርቶ እንደኛ የጳጳሱን ስልጣን አናውቅም የሚሉትን እንኳ ይጠብቋቸዋል።»

ቀደም ሲል በጦር ሰለባዎች ላይ የተፈፀመውን የሥቃይ ቅጣት ስላዩ ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት የውይይቱን አስፈሪ አደጋ በመስጋት ሜርት ዠረሚ አሁንም አሁንም አይኖቹን ያሻሽ ጀመር።

«እንዲህ ከሆነ በክርስቶስ አታምኑም ማለት ነው» ሲሉ ሌላው ሰው በድንገት ጠየቁ። ጥያቄው የመጣው ከሬስ ዮሐንስ በስተግራ ከቆሙና ፀጉራቸውን በቀይ ሃር ካስጎነጎኑ አንድ ረዥም ሽማግሌ ሰው ነው።

«በርሱ እናምናለን፣ በትምህርቱም እናመልካለን» አለ ጆን ባፕቲስት «ይህን የምናደርገው በራሣችን ሥርዓት እንጅ በጳጳሱ አይደለም። በዚህ ሣቢያ የናንተው እንደተኮነነው ሁሉ የኛም እምነት በጳጳሱ ተኮንኖብናል።»

በተሰበሰቡት ባለስሥጣኖች መካከል አንዳች ስሜት ተሰራጭቶ ጉምጉምታ ተሠማ። የአቋማቸውን ግርማ በማሰብ ራሣቸውን ከገዙ በኋላ እነዚህ ባለሥልጣኖች ርስ በርሳቸው ተያዩ። ከዚህ በኋላ ማንሾካሾክ ተጀመረ።

«ለመሆኑ ቀሣውስት ናችሁ?» ሲሉ እኒያው አዛውንት ጠየቁ

«በጭራሽ፣ አይደለንም»

«ጉዳቱን እንፈውሣለን ትላላችሁ፣ ሲባልም እንሰማለን»



«በፍጥረት ጊዜ እግዚአብሔር ለሠዎች ልጆች መልካም ጠቀሜታ በማለት ያስቀመጣቸውን የእፅዋትንና የእንስሣት ቅመሞች ሰው ለሆነ ወገናችን በመስጠት እናገለግላለን እንላለን»

«እንዲህ ከሆነ ያለፀሎት መፈወስ ይቻላል ብላችሁ ታምናላችሁ»

«ፀሎት፣ ተአምራት እንዲፈጠር መለመን ነው። እኛ ይህን አናደርግም»

«በተአምራት አታምኑም?»

ጆን ባፕቲስት ቀደም ሲል ለኒያ ጄስዊት የሰጠውን ዓይነት መልስ ለመስጠት ከቃጣ በኋላ የተሻለ አሰበ።

«በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገበውን ተአምራት እናምናለን። በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመውንም እናምናለን። ሌላ ተአምራት አናውቅም»

«ታላላቅ ቅዱሣን ተአምራት ሠርተዋል» አሉ ራስ ዮሐንስ

«ይህ ምናልባት የኛን የእምነት እውቀት ውስንነት ያመለክት ይሆናል» አለ ጆን ባፕቲስት «ክርስቶስ የተናገራቸውን ሁሉና በአራቱም ወንጌሎች ላይ የተፃፉትን በጥብቅ እንከታተላለን። ነገር ግን ሟች የሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ የተናገሩትን ፍፁም ትክክል ነው ብለን አንስማማም። ለምሣሌ አንድ ጊዜ አንድ ቅዱስ ሰው ሰይጣንን እማኝ አደረገው የሚለውን አይነት፣ ወይም አንድ የታመመና የተራበ መነኩሴ በፀሎት ኃይል ብቻ መሶቡ የተጠበሰ የቆቅ ስጋ ዘንቦ ተሞላለት በሚሉት አናምንም»

እነዚህን ሁለቱን ምሣሌዎች ከአቢሲኒያ ተባረው ከወጡ ጄስዊቶች ከንፈሮች መስማታቸውን አስታውሰው ለጆን ባፕቲስት የነገሩት አባ ዴ ብሬቬደንት ነበሩ። በሰይጣን አለቃ በሉሲፈር ላይ ድል የተጎናፀፈው ቅዱስና የቆቅ ስጋ እንዲዘንብ ያደረገው መነኩሴ ታሪክ በኮፕቲክ ካህናት መካከል ውዝግብ ያስከተሉ ነጥቦች ናቸው። በዚህ ጊዜ በግልፅ የሚስተዋል ሁከት በተሠበሠቡት ባለሥልጣናት መካከል ተቀሰቀሰ። ጆን ባፕቲስት፣ እዚያ ከተሠበሠቡት መካከልም ቢሆን በጣም ጥልቅ አለመግባባት ያለባቸውን ሃይለኛ ነጥብ ስለነካው ይመስላል

ራስ ዮሐንስ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታ እንዲሰፍን አዘዙ። ሰዎችም ፀጥ አሉ። ከዚያም አንድ አጭር ሰው ከባለስልጣናቱ መካከል ወጥተው ወደፊት ተራመዱ። ቢጫ ብርቱካንማ የመነኩሴ ልብስ ለብሠዋል። ያበጡት አይኖቻቸው አጥርተው አያዩላቸውምና በዙሪያቸው የሚገኘውን በጭጋግ ውስጥ የሚያዩ ይመስላቸዋል።

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ እንደቃጭል በቀጠነ ድምፅ ጠየቁ።

የጥያቄዎቹ ሁሉ እምብርት ይህ ነው። ጄስዊቶች ለረዥም ጊዜ የተፋፖበት ጥያቄ ነው። ነጥቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሮማ ቤተክርስቲያን ከአስራ ሁለት ክፍለ ዘመናት በፊት እንዲለያዩና በየራሳቸው መንገድ እንዲጓዙ ያደረጋቸውና ሊገለፅ ያልቻለ ውስብስብ የመንፈሣዊ ትምህርት ጉዳይ ነው። ሁለቱ መንገደኞች ቀደም ሲል ባደረጉት መሠናዶ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ይነሣሉ ብለው ዝግጅት አላደረጉም ነበር። በጣም በግልፅ እንደሚታወቀው እንዲህ ያለ ከባድ ሃሣብ ይነሣል ብሎ የተጨነቀም ሰው አልነበረም። ሜትር ዠረሚ ወደ ጆን ባፕቲስት ሲመለከት ጥልቅ የመደነቅ ስሜት በፊቱ ላይ አስተዋለበት።



# 10

«ክርስቶስ ስንት ባህርያት አሉት?» ሲሉ መነኩሴው ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቁ።

ከባድ ዝምታ በክፍሉ ሁሉ ላይ ሰፈነ። ሁሉም ዓይኖች ምንም ወደማይናገረው ወደ ጆን ባፕቲስት ዞሩ። ከዚያም በድንገት እንዳች መንፈስ እንግሣውና ተበረታታ።

«ክርስቶስ ስንት፣ ስንት ባህርያት አሉት የሚለውንማ ጥያቄ አባቶቼ እኔ እናንተን የምጠይቀው ነው።»

ሃጂ አሊ ቃላቱን እንዲተርጉም ጊዜ ሠጠውና ቀጠለ።

«እያንዳንዳችን መናገር የሚገባን በራሣችን የሙያ እውቀት ዙሪያ ያለውን ነው። በበኩሌ እኔ ሐኪም ነኝ። ጓደኛዬም መድሃኒት በመቀመምና በማዘጋጀት ባለሙያ ነው። ከዚህ ውጭ የምናውቀው በጉናችን ታጥቀናቸው ያሉትና እያያዛቸውንም የምናውቅባቸውን ጉራዴዎቻችንን ነው። እፅዋትንና መሣሪያዎቻችን በተመለከተ፣ አባቶቻችን፣ ደስ ያላችሁን ጠይቁንና በተቻለን መጠን የሚያረኩ መልሶች እንሰጣችኋለን። ነገር ግን አሁን የጠየቃችሁን ጥያቄ በርግጥ እናንተን የመሰለ የመንፈሣዊ ትምህርት ሊቃውንትን የሚመለከት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመማር ደግሞ ዝግጁ ነን።»

ጆን ባፕቲስት በክብር ዝቅ በማለት መልሱን አጠናቀቀ። ነጭ ካባውን እንደለበሰ አንድ እጁን በልቡ ላይ አሣርፎ ወደ ራስና እዚያ ወደ ተሰባሰቡት ጓደኛቻቸው ትጥቅ በማስፈታት ታማኝነት መልክ ተመለከታቸው።

በአንድ ገደል ጥግ፣ በሁለቱም ጐን ስስ መድረሻ ባለው ጠባብ መንገድ ላይ የሚራመድ መስሎት ውስጡ ተሰቃየ። ልቡ ዘለለች። ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ቁልቁል ወረደ። ይሁንና ይህን ሁሉ ላለማሣየት ራሱን አበረታ።

ረዘም ያለ ፀጥታ ተከተለ። የሚሰማ ድምፅ ቢኖር በግቢው ውስጥ የተነሣው የሴቶችና የወንዶች የተደባለቀ የቅሬታ ድምፅ ብቻ ነበር።

«ንጉሰ ነገስቱን ለማየት ተዘጋጁ» አሉ ራስ ዮሐንስ በመጨረሻ በጨዋ ቅላፄ። «ልትፈውሣቸው የሚያስችልህ እውቀት እንዳለህ በመግለፅህና ግርማዊነታቸውም የህክምና ትዕዛዝህን እንደሚፈፅሙ በመግለፃቸው፣ ከፊታቸው እንድትቀርብ ይደረጋል። ይሁንና ሳስታውቅህ የሚገባኝ፣ ንጉሰ ነገስታችን ከማንም ጋር በቀጥታ ግንኙነት አይጀምሩም። ይህ በውጭ ሰዎችም ላይ ይሰራል። አትነካቸውም ወይም አትጠጋቸውም። ነገር ግን ታያቸዋለህ። በእንደራሴያቸው በኩልም የሚናገሩትን ትሰማለህ»

«ነገር ግን ይህ የሚቻል አይደለም። እርስዎም ቢሆኑ ይህ እንዴት ሲሆን . . .»

«አካሄዱ ይኸው ነው። ልትፈውሣቸው ችሎታው አለህ ወይስ የለህም?»

በቀረበለት አስገዳጅ ቃል ጆን ባፕቲስት ተስፋ ቆረጠ። ምክንያቱም ሃጅ አሊ የገለፀለትን የንጉሡን ህመም የማከሙን ሁኔታ ይጐዳበታል። ከዚህም ባሻገር የዲፕሎማቲክ ተልዕኮውንም ይጐዳበታል። ታዲያ ለንጉሰ ነገስቱ መልዕክቱን እንዴት ያስተላልፍላቸዋል? ይህንን ያህል ግልፅ ስለሆነ፣ ራስ ምንም ተቃውሞ አይፈቅዱም። ፖንሴም የቀረበውን ቃል እንደተባለው ተቀበለ። ባለሥልጣኖችም ከክፍሉ በሰልፍ ለቀቁ ። ሦስቱ ተጓዦች ተመልካቻቸውን እንዲጠብቁ ከዚያው ቀሩ።

«እነዚህን ዝርዝር ነገሮች በጭራሽ አልገለፅካቸውም» አለ ጆን ባፕቲስት፣ ለሃጅ አሊ በቁጣ «ንጉሡን ልናነጋግራቸው አንችልም»

«በህዝብ ፊት፣ ሰው የማይደርስባቸው ናቸው» አለ ግመል ነጂው። «ይህ ደንብ ነው። ሌላው ቀርቶ መሬቱን እንኳ እንዲነኩ አይፈቀድላቸውም። ዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ ሲሉ መጀመሪያ በበቅሎ ጀርባ ላይ ሆነው ይመጡና ሲወርዱ፣ እግራቸው መሬት የሚያርፈው ዙፋኑ የተቀመጠበት ምንጣፍ ላይ ሲደርሱ ብቻ ነው። በቅሎዋ ምንጣፉ ላይ ስትወጣ ሁልጊዜም በዚያ የፋርስ ጌጥ መሀሉ ላይ ፋንድያዋን ትጥላለች። ሁሉም የለመደው ነገር ስለሆነ ለውጥ አያመጣም። እንደእውነቱ ከሆነ እናንተ እድለኞች ናችሁ። ነገሮች በጣም ተለዋውጠዋል። በቀድሞ ጊዜ ንጉሥ ነገስቱን በፍፁም አታያቸውም። የኒህኛው አያት ለህዝብ የሚታዩት በአመት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ብቻ ነበር። ከዚህ በተረፈ ከሚያምረው መጋረጃ ጀርባ ነበር የሚኖሩት»



«ንጉሡ ለምንድን ነው የማይናገሩት?»

«ልማዱ ይኸው ነው። እያንዳንዱን ተግባር የሚያከናውኑላቸው አንዳንድ ሃላፊ አላቸው። ለምሳሌ የንጉሱ አይን የሚባል አለ። ይህ ሃላፊ በቤተመንግስቱ የሚያየውን ሁሉ ሪፖርት ያደርግላቸዋል። የንጉሥ ጆሮ የሚባልም አለ። እንደራሴያቸው ሆኖ ስለራሳቸው ይሠማል። የቀኝ እጃቸው እና የግራ እጃቸው አዛዦች የሆኑና ሠራዊታቸውን የሚቆጣጠሩላቸው አሏቸው። ሌላው ስማ በለው ይባላል። የንጉሡን ቃሎች በከፍተኛ ድምፅ ጮሆ ያሰማል።»

«ለመሆኑ ልጆቻቸውን የሚያሣድጓቸው ራሣቸው ናቸው?» ሲል ሜትር ዠረሚ አጉተመተመ።

«ቀልዱን ተወውና ወደ ቁምነገሩ እንመለስ። ብዙ ጊዜም የለንም» አለ ፖንሴ «ለመሆኑ ለአለፉት ሃምሣ አመታት ምንም ሣይበሉ የኖሩት ቅዱስ ምን አጋጠማቸው? ደግሞስ እኛ ከእርሣቸው ጋር ውድድር ውስጥ ነው ያለነው ወይስ እሳቸው ጓዛቸውን እንዲጠቀልሉ ተደርገዋል?»

«ሃያ አመቶች» አለ ሃጅ አሊ ጠንቀቅ ብሎ «ሃያ አመት ሙሉ ምንም አልቀመሡም። አቤቱ ነብይ! እንዲህ ያለውንስ ቀልድ አይቁጠሩበት . . . »

የጣቶቹን ጫፎች ሳማቸውና ዓይኖቹን ወደ ሠማይ አቀናቸው

«ንጉሰ ነገስቱ?» ሲል ቀጠለ «ቅዱሱን ሰው ከእንግዲህ በኋላ አምነው ምስጢራቸውን አያዋዩዋቸውም»

«እግርጠኛ ነህ? እንጀራቸውን አንነጥቃቸውም» ሲል ሜትር ዠረሚ ጠይቀ።

ፖንሴ በቁጣ ገላመጠው።

«ይቅርታ» አለ ዠረሚ «ረኸሾሙ ቆይታችን አበሳጭቶኝ ነው»

«ቀልደህን፣አይኖቻችንን ለሚያወጡበት ጊዜ አቆየው» አለ ጆን ባፕቲስት ትህትና በጐደለው መልክ። እንደ እውነቱ እርሱ ራሱ ከጓደኛው በባሰ ጨሷል።

ወዲያውኑ ሁለት ዘበኞች ሊመሯቸው መጡ። ሦስቱም ሰዎች ተከታታይነት ባላቸው ትናንሽ ጨለማ፣ ቀዝቃዛና አና ክፍሎች በኩል ተከትለዋቸው ሄዱ። ተጠቃልለው እስኪደርሱ ጠበቁና ወደ እንግዳ መቀበያው አዳራሽ ገቡ። አዳራሹ በጣም ሠፊ ክፍል ሲሆን፣ በአንድ አብይ ዋልታ ላይ የተዋቀረ ባለ ሦስት ቀስት ጫፍ ጣሪያው በአምስት ክብና ወፋፍራም ምሰሶዎች ላይ በመሃልና በጐንና ጐን በኩል አርፏል። ከቤተ መንግስቱ ባለሟሎች አብዛኛዎቹ ከኋላ በኩል ቆመዋል። ወደ ንጉሡ ቀረብ እየተባለ ሲመጣ ባለው ረድፍ ላይ ብዙ ሰዎች ተቀምጠው ይታያሉ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሁሉም በንጉሱ እይታ ውስጥ ስላልሆኑና በባህሉም ንጉሡ ሲያዩዋቸው የሚገባቸው ሁሉ፣ ስብሰባው ለሰዓታት እንኳ ቢቀጥል ቆመው መታየት ስለሚኖርባቸው ነው።

አፄው ጓዳ በመሠለ ቦታ፣ በምንጣፍ ላይ በተደረገ ዙፋን ላይ ከወደ ጥግ ተቀምጠዋል። በቅሎይቱ እንደተለመደው ፋንድያዋን ጥላለች። የአፄው አቀማመጥ ከፊት ለፊት ከተቀመጡት የአሻቢዎች መስመር ብዙ እርምጃዎች ራቅ ብሎ ነው። እነዚያ የውጭ ዜጐች በፀጥታ እየተመሩ ወደፊት ተወሰዱ። በዚህን ጊዜ ግቢው ውስጥ አንበሶች ሲያገሱም ሰሙ። በእነዚህ ተይዘውና ታስረው በሚገኙ አንበሶች የተነሣ ንጉሡ ነገስቱ ዝና አግኝተዋል። በአዳራሹ ሌላኛው ጠርዝ ቀደም ሲል ከራስ ዮሐንስ ጋር ቃለ ምልልስ ሲያደርጉ በነበረበት ጊዜ ያደመጡትን ዓይነት የሀዘን ዜማዎች ሰሙ።

ቀደም ሲል በተስማሙት መሠረት ፖንሴና ጓደኛው፣ ሃጅ አሊ የሚያደርገውን እያንዳንዱን አካላዊ እንቅስቃሴ በመከተል ይኮርጃሉ። ከንጉሡ ፊት ሲደርሱ ግመል ነጅው ተንበረከከ፣ ከዚያም ክንዶቹን ወደፊት እንደመዘርጋት አድርጐ በድንጋያማው ወለል ላይሙሉ በሙሉ የመዘርጋት ያህል ለጥ አለ። ሌሎች ሁለቱ በትክክል ይህንኑ ፈፀሙ። እንዳስመታደል ሆኖ ሜትር ዠረሚ ተንበርክኮ በጣም ወደፊት ስለተሳበ እጆቹ የቤተመንግስቱን ምንጣፍ ነኩ። ሁለት ባለስልጣኖች ወደ ኋላ ገፈተሩት። ሶስቱ ሰዎች፣ አፄው ከፊታቸው እንዲቀርቡ መፍቀዳቸውን «እፌ ንጉሱ» እስኪያስታውቋቸው ድረስ እስኪደክማቸው ቆሙ። ከዚያ በኋላ አፄውን ለማየት ቻሉ።



የአቢሲኒያው ንጉስ ነገስት አፄ እያሱ፣ የህንዳውያንን ጨርቅ ለብሰው ከፍ ካለ ቦታ በተቀመጠው ወርቃማው የእንጨት ዙፋናቸው ላይ ሆነው ይታያሉ። የአፄው ሰውነትም ይሁን ፊታቸው በትልቅ ደማቅ ቀይ ልብስ ስለተሸፈነ ሦስቱ ሰዎች በግልፅ ሊያዩዋቸው አልቻሉም። ረኸሙ ፀጉራቸው፣ በቀጭን የጥጥ ጨርቅ ሻሽ ከማጅራታቸው ላይ ታስሮ በግራና ቀኝ አንገጫቸው በኩል ወርዷል። በሚገባ የሚታየው ቀጠን ያለው ትልቅ አፍንጫቸው፣ የሚያበራውና ፈዘዝ ብሎ የሚመለከተው ዓይናቸው ነው። አፋቸው፣ በአንገታቸው ዙሪያ በተጠመጠመላቸው የታጠፈ ቢጫ የሃር ፎጣ ላላ ተደርጐ ተሸፍኖላቸዋል።

ሲናገሩ ድምፃቸው አይሰማም። ስለዚህም የንጉሡ ነገስቱ ፈቃድ የሚሠማው፣ ለዚሁ ሲባል ሃላፊነት የተሰጠው ባለሥልጣን ግልፅና ከፍ ባለ ድምፅ መልሶ ሲናገረው ነው። በንግግሩ መሃል፣ ሃጅ አሊ ማስተርጐም ማቆሙን ጆን ባፕቲስት አስተዋለ። ከአፈ ንጉሡ በስተቀኝ የቆመ አንድ አቢሲኒያዊ ተርጓሚ በይፋ የሚሰጡትን መግለጫዎች በሙሉ በአረብኛ ይነግራቸዋል። ከንጉሰ ነገስቱ ጋር የተደረገው ይህ ይፋ ስብሰባ በጣም አጭር ነበር። ንጉሡ፣ በሠውነታቸው ላይ ስላለው ህመም ከውጭ አገር ሰዎች ምክር እንደሚሹ ከማረጋገጣቸው ባሻገር ዝርዝር ነገር አልተነገረም። ፖንሴ፣ ከግብፅ ፓሻ የመጣውን የፅሁፍ መልዕክት «ለቀኛዝማች» አቀረበላቸው። ንጉሰ ነገስቱ፣ እንደህ ካለው ገዥ ጋር በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ሁኔታ አስመልክቶና ግብፅ፣ የእሌክሳንደርያው ፓትርያርክ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የምትተማመንበትን አቡን እንዲልኩ በመፍቀድ ጉዳይ ላይ መልካም ግን ትንቱ እንዲቀጥል እንደሚወድዱ መልስ ሰጡ።

የፓሻው ደብዳቤ በአረብኛ አስተርጓሚው ተነበበ። ደብዳቤው አጭርና በምስጋና የተሞላ ነው። በዚህ ውስጥ የፖንሴ ሐኪም መሆን በተለየ አፅንኦት ተገልጿል። በፓሻው ስላልተጠቀሰው ሜትር ዠረሚ ደግሞ ፖንሴ ሃላፊ ሆነ። ለንጉሠ ነገስቱ ያመጡላቸውን ገፀ በረከት ደግሞ ፕሮቴስታንቱ ለሌላ ባለስልጣን አስረከበ። እንደግለሰብነታቸው መድሃኒት ቀማሚዎች ድንቅ ገፀ በረከት እንዲያቀርቡ አይጠበቅባቸውም። በሃጅ አሊ ምክር መሠረት በዝሆን ጥርስ የተሰሩ እጀታዎች ያሏቸው አንድ ሣጥን ምላጮችን ሦስት ሜትር በአምስት ሜትር የሆነ አንድ በተረት ውስጥ የሚታወቅ አጭር ሰው፣ አጋዘን ሲያድን የሚያሣይ ስዕል ያለበት ጨርቅ ነበር ያቀረቡት። ስጦታው በጓዳ በኩል ወዲያውኑ ተሰወረ።

ንጉሱ፣ ምንም ዓይነት ምስጋና ሳያቀርቡላቸው አሰናበቷቸው። የተናገሩት ቢኖር በሚቀጥለው ዕለት የህክምና ትዕዛዛቸውን እንደሚጠብቁ ብቻ ነበር። በዙፋኑ አጠገብ ቦታቸውን የያዙት ራስ ዮሐንስ፣ ዛቻ ያለበት በሚመስል አነጋገር፣ መድሃኒቱ መጀመሪያ በሶስት ባሪያዎች ላይ፣ ቀጥሎ በሁለት ባለስልጣኖች ላይ ተሞክሮ እንደሚፈተንና ንጉሰ ነገስቱ ከዚያ በኋላ እንደሚሰጣቸው አክለው ተናገሩ። በዚህ ሂደት ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ላይ አደጋ ቢከሰት በሁለቱ ባዕዳን ላይ ውጤቱ የከፋ ይሆናል። በመጨረሻም በከተማውና በገጠሩ እንደልባቸው ለመዘዋወር ነፃ መሆናቸውን ነገሯቸው። ከሚፈልጉት ማንኛውም ሰው ጋር መነጋገር ይችላሉ። ነገር ግን የካቶሊክን እምነት የሚሰብክ የሚመስል አንድ ቃል ቢተነፍሱ ፈጣንና ተገቢው ቅጣት ይፈፀምባቸዋል።

እንግዶች ለሁለተኛ ጊዜ ብዙ በመቆማቸው ከደከሙ በኋላ፣ ሲደበደቡ የቆዩ ይመስል ክፉኛ እየተንቀጠቀጡ የስብሰባውን አዳራሽ ለቅቀው ወጡ።

ወደ ሃጅ አሊ የሙስሊም ጓደኛ ቤታቸው በመመለስ ላይ ሳሉ አንድ እንደነገሩ የለበሰ እግረኛ መልዕክተኛ ሲሮጥ ደረሰባቸው። ሁለቱ ባዕዳን ሣጥኖቻቸውን ቀርቅበው በፈረሶቻቸው ላይ እንዲጭኑና እንዲከተሉት ነገራቸው። ሃጅ አሊ ብዙውን ነገር ስለዘረፉቸው የመጫን ስራው የሚወስድባቸው ጥቂት ጊዜ ነው። ከቀሯቸው ጥቂት ቁሣቁሶች ውስጥ ያረጁ የአውሮፖውያን ልብሶቻቸውን፣ አረቡ ሊያነብባቸው የማይችላቸውን መፃህፍቶቻቸውን፣ የመድሃኒት ሻንጣቸውንና በጨርቅ ውስጥ ሆነው በኮርቻ ስር ያሉትን የሚወዷቸውን ጉራዴዎቻቸውን በጆንያ ውስጥ ከተቱ። መልዕክተኛው ቀደም ሲል ከንጉሡ ቤት ጉን በተቃራኒው ባለ ከቤተመንግስቱ ግድግዳ ቀጥሎ በሚገኝ የድንጋይ ቤት አስገባቸው። ለዘበኛ ተብሎ የተሠራ ቤት ይመስላል። መግቢያው ወደ አንድ ረዥም የመወጣጫ ደረጃ የሚያመራ ጠባብ የመተላለፊያ ቦታ ነው። በከባድ ቁልፍ ተቸንክሮ የነበረውን ከባድ መዝጊያ በትግል ከከፈተው በኋላ ይህንኑ መልዕክተኛ ተከትለው ደረጃዎቹን ወጡ። መጠነኛ ስፋት ያለው ክፍል አሳያቸው። ወደ ማለዳው ፀሐይ አቅጣጫ በሚከፈት መስኮት ብርሃን ይገባል። በክፍሉ ውስጥ ሁለት የጠፍር አልጋዎች፣ ሁለት የእንጨት በርጮማዎች፣ አንድ ጠረጴዛና ለጋራ የሚያገለግል መስታወት አለ።

በፖንሴና በጓደኛው አዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ ግዙፉ ቁልፍ ምን እንደሚሆን ነበር። ለነርሱው ተሰጥቷቸው ይሀ ከእንግዲህ ቤታችን ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸው ይሆን? መልዕክተኛው ግን ቁልፉን በበሩ ላይ ተወው። ይህ ሰው አረብኛ አያውቅም ነበርና ከርሱ አንዳችም ነገር ማወቅ አልቻሉም።

ሁለቱ ጓደኛሞች ብቻቸውን ከቀሩ በኋላ ለረዥም ሰዓታት በየአልጋቸው ላይ በፀጥታ ተጋድመው ቆዩ።

«እንደ ዮናስ በአሳነባሪ ሆድ ውስጥ የሆንክና በህይወት የምትወጣበት ምንም ዕድል እንደሌለህ ታስባለህ?» ሲል ዡሪሚ በመጨረሻው ጠየቀው።

«በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ እናተኩር» አለ ጃን ባፕቲስት እየተንጠራራ። «እስከአሁን ድረስ ጥቂት መሰናክሎችን አልፈናል። ከእንግዲህ ቀጣዮቹን ማየት ይገባል። ዛሬ ማታ ለንጉሡ ባሪያ መድሃኒት እናዘጋጅለታለን። ሃጅ አሊ እንዳረጋገጠልን፣ ንጉሱ ያለባቸው ሕመም ልክ እርሱ ላይ እንዳለው ደዌ ነው። ከዚያ በኋላ የሚሆነውን እናያለን።»

ይህን ተናግሮ ጃን ባፕቲስት እንቅልፍ ወሰደው። ሜትር ዡሪሚ በደስታ የጓደኛውን ፈለግ ተከተለ።

በሩ ላይ በተፈጠረ አነስተኛ መንኳኳት ነቁ። በውጭ ያለው የፀሐይ ብርሃን ቀነስ ያለ ሲሆን፣ ሰማያዊ ጥላ ከወደ መንገዱ በኩል እየዘለቀ ነው። ጊዜው ከቀትር በኋላ ዘግይቶ ነው። ወደ ክፍላቸው የዘለቀው ወጣት ሰው ሃያ አመት የሚሆነው አጭርና በጣም ቀጭን ነው። ፊቱ በፈንጣጣ የተላላጠ ስለሆነ ሕመሙ ቆዳውን አደድሮታል። ፊቱ ሸካራ ሲሆን አፍንጫው በተለይ አጭርና እንደኳስ ክብ ነው። ጥቋቁር አይኖቹ ብልህነትና ለዛ የተሞሉ ናቸው። በከንፈሮቹ ላይ ፈገግታ ሲያንዣብብባቸው አጠቃላይ እንቅስቃሴው ለዛ ያለው ነው። እነዚህ ምልክቶች ከጥቁርና ከርዳዳው ፀጉሩ ጋር ሲታይ፣ ለጃን ባፕቲስት እንዳልታደለ ወንድሙ ያህል ነው።

«ስሜ ዲሚጥሮስ ነው» አለ በአረብኛ

አረብኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ መናገሩ በግልፅ ያስታውቃል። አፍ የፈታበትን ግሪክኛንም እንደሚናገር ነገራቸው። እነርሱ ግን ይህን ቋንቋ አያውቁትም። ጣሊያንኛን ግን

ሁለቱም ፈረንሣውያን ቬኑስ ውስጥ ተምረው ነበር። ውይይታቸው የቀጠለው በዚህ ቋንቋ ነበረ።

ዲሚጥሮስ፣ የንጉሠ ነገስቱ የግል አሽከራቸው መሆኑን ራሱን አስተዋወቀ። ሃጅ አሊ በጣም ስራ ስለሚበዛበትና በተከታታይ አብሯቸው ሊሆን ስለማይችል እነርሱ በፈለጉት ጊዜ ዲሚጥሮስ ሊያጅባቸው ይችላል። ከማንም ባይሠሙም ዲሚጥሮስ አዲሱ የእስር ጠባቂያቸው መሆኑን ተገነዘቡ። ነገር ግን የዚህ ወጣት ፍልቅልቅና ደስተኛ መሆን ንግግሩንም እንዳለ ሲኦስታ እንዲቀበሉት አደረጋቸው።

«ከተማውን መጎብኘት ትፈልጋላችሁ? እራት ለመብላት ይዣችሁ ልወጣ እችላለሁ። ወይም ምግባችሁ እዚህ እንዲመጣላችሁ ልናደርግ እንችላለን»

ጊዜው ገና ስላልመሸና ስለዋና ከተማውም እስከ ዛሬ ምንም ስላላዩ ከተማውን እየተመሩ ለማየት ተስማሙ።

ሦስቱም ተመሣሣይ የጥጥ ልብሶችን ለብሠው በእግራቸው መንዝ ጀመሩ። ሁለቱ ፈረንሣውያን እነርሱን በሚመስል ሕዝብ መሃል በነፃነት መንቀሣቀስ የሚችሉና ከእንግዲህ በኋላም እንግዶች እንዳልሆኑ የተነገረው ሃሣብ አስደሰታቸው። ዲሚጥሮስ እንደሁልጊዜው ፈገግታው፣ በባለማወቅና በድንገት አስተሣሰባቸውን ያርመዋል።

«እኔ አብሬአችሁ እስካለሁ ድረስ አንዳችም ነገር አያስፈራችሁም። ቀሣውስቱም ሲገድሏችሁ አይደፍሩም» አላቸው።

እነዚህ ቃላት ከተነገሩ በኋላ ሁለቱ ባዕዳን እያንዳንዱን አላፊ አግዳሚ በጥርጣሬ ማየት ጀመሩ። አቢሲኒያውያን ያለልዩነት ግዴለሾች መሰሏቸው። እነርሱ በሚያልፉበት ጊዜ ወደነሱ ዓይኖቹን ዞር የሚያደርግ ወይም አፍጥጦ የሚያያቸው የለም። በመሆኑም መኖራቸውን እንኳ ልብ የሚለው የለም ብሎ ምሎ የሚወራረድ ይኖራል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጓዙበት አነስተኛ መንገድ ወደ ዋና ጐዳና ያድጋል። ከነዚህ መንገዶች በአንደኛው ረዥም ሰልፍ ሲመጣ ሊያሳልፉት በማለት ቆሙ። ሰልፉ ደማቅ ቀይ፣ ዘርፋፋ ካባና በወርቅ የተጠለፉ ቆቦች በለበሱ ቀሣውስት የሚመራ ነው። ክበድ ያሉ ነገሮችን፣



ስርዓት ያላቸው ቀዳዳ የተበጀባቸውን መስቀሎች በቅርፅ ላይ ተሸክመዋል። የመስቀሉ ንድፍ አለቅጥ የተደጋገመና መልክ እንዲኖረው በመሠራቱ ሲገጣጠም መልሶ መስቀል የሚሆን ነው። በመሆኑም ብረቱ ሃያልና መሠረታዊ በሆነ ቅርፅ ላይ እንደ አመዳይ የረጋ አብረቅራቂ መስተዋት መስሏል። ከቀሳውስቱ በስተኋላ ጦሮችን፣ የጠቋቆሩ ጋሻዎችንና ወገባቸው ላይ ሾቤአቸውን የታጠቁ ተዋጊዎች ተከትለዋል። ጥቂቶቹ በከንዶቻቸው ላይ ቀጫጭን የቀይ ጨርቅ ጥምጣሞችን ቋጥረዋል። ይህ የክብር ምልክት መሆኑንና እያንዳንዱ ጥብጣብ የተገደለውን ጠላት ቁጥር እንደሚያመለክት ዲሚጥሮስ አብራራላቸው። በሰልፉ መሃል ላይ፣ ኮስተርና ፀጥ ያሉ ወታደሮች አሉ። እነዚህ ምናልባት የሰልፉ ዓብይ ክፍል ሣይሆኑ አይቀሩም። በረዥም ጦር ጫፍ ላይ የእንጨት መስቀል ተሠርቶበት ከራሱ በላይ ከሁሉም ሰው ሙሉ በሙሉ በሚበልጥ ረዥምና ጠንካራ በሆነው አቢሲኒያዊ ተይዟል። በአንድ መንጠቆ ባለው እንጨት ላይ ከጥቁር ሃር ጨርቅ የተሠራ ጃኬት የመሰለ ነገር ተሰቅሏል። ይህ ነገር ሁለት እጅጌዎች ሲኖሩት ጭራው ላይ ሁለት የተበጣጠሱ የመስመር ምልክቶች አሉበት። ልብሱ በልዩ ልዩ ቀለማት የተኾርኮረኮረ የኔ ብጤ ልብስ ይመስላል። ከዚህ እንግዳ ነገር ከሆነ ምልክት ቀላ ያለ ፈሳሽ ይንጠባጠባል።

«ኦ እንደምትበሳጉ እገምታለሁ» አለ ዲሚጥሮስ እነርሱን በጭንቀት እየተመለከተ።

«ቆዳ ይመስላል» አለ ሜትር ዠረሚ አይኖቹን ብልጥጥ አድርጐ ክፍቶ በፍርሃት

«የዚህችን አገር ህግ ለማድነቅና ልትጨብጧቸው የሚገባችሁ፣ በመጠኑ ለየት ያሉ በመሆናቸውም ለመገንዘብ የሚያስቸግሩ ግን አስፈላጊ ነገሮች አሉ።» አለ ዲሚጥሮስ። «የተለያዩ የቅጣት አይነቶች አሉ አሁን የምታዩት አይነት ቅጣት ብዙም አይፈፀምም። እንደ እድል ሆኖ በዚህ የሚያስቀጣውም ወንጀል እንደሁ አይሠራም። ለጠላት ያደሩ ከሃዲዎች ዓይኖቻቸው እንዲወጡ ይደረጋል።»

«ያንን አይቶናል»

«አዎ፣ ወዳጅ ሆኖ፣ የራሣችን የጦር ሠፈር ሰው ሆኖ፣ የራሣችን ቤተሰብ ሆኖ ልክ አሁን እንደተደረገው ከነህይወቱ ቆዳው ይገፈፋል።»

ይህ ሲነገር፣ ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው ይህ በነፋስ የሚውለበለብ አስደንጋጭና በሞራልም ረገድ መጥፎ የሆነውን ቆዳ ሲመለከቱ አጥወለወላቸው። ከሰልፉ በስተመጨረሻ ያሉት ፊገግ የሚሉ ሴቶችና ሕፃናት ሲሆኑ በፀጥታ ያጨበጭባሉ።

ሦስቱ ሰዎች ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሁለቱ ባዕዳን ባዩት ነገር ክፉኛ እንደሚጉዱ ዲሚጥሮስ ይሰማዋል።

«አትበሳጉ» አላቸው። «የደረሳችሁት ድል አድራጊ ወታደራዊ ሠራዊት ከዘመቻው በተመለሠበት መጨረሻ ላይ ነው። እስረኞቹ እየተቀጡ፣ ከሃዲዎች እየተጋለጡ፣ ጀግኖች እየተሸለሙ ነው። ሕይወት ሁል ጊዜም አስደሳች አይደለም»

«በመስማታችን ደስ ይለናል።» አለ ሜትር ዠረሚ «የኛም ቆዳ በጉዳናዎች መሃል በሰልፍ የሚያልፍበት ጊዜ እስኪመጣ ለህዝቡ የምንሠጠው አዝናኝ ነገር እምብዛም አይኖረንም። ይህን በማወቃችን እንፅናናለን።»

«የናንተ ቆዳ በጉዳናዎች መሃል መቼም በሰልፍ አያልፍም» አለ ዲሚጥሮስ በሳቅ እየተንከተከተ። «ይህ ሙሉ በሙሉ ሊሆን የማይችል ነገር ነው።»

«መድሃኒታችን ውጤት ባይሰጥስ ምን ይሆናል?» ሲል ፖንስ ጠየቀ

«ያን የመሰለ ቅጣት በናንተ ላይ አይፈፀምም። እናንተ የንጉሠ ነገሥቱ እንግዶች ናችሁ»

«ጀስዊቶችስ? የንጉሠ ነገስቱ እንግዶች አልነበሩም እንዴ?» አለ ሜትር ዠረሚ

«ኦ! ቆይ እስኪ» አለ ዲሚጥሮስ አመልካች ጣቱን አውጥቶ «እኔ እስከማውቀው ድረስ ጀስዊቶች ከነ ህይወታቸው ቆዳቸው አልተገፈፈም። እነርሱን በተመለከተ ሕጉ በጥብቅ ነው የተፈፀመው»

«ማለት?»



«ማለትማ በድንጋይ ተወግረው ተገደሉ። ወደታች ተመልሰን ስንሄድ፣ በአደባባዩ መካከል ላይ ሁለት የድንጋይ ክምሮችን ታያላችሁ። የመጨረሻዎቹ በሞት የተቀጡት ጀስዊቶች የተቀበሩበት እዚሁ ነው። እነዚህን የድንጋይ ቁልሎች ደግሞ ማንም እንዲነካቸው አይፈቀድለትም»

«ስለዚህ እኛም የመገፈፍ አደጋ ውስጥ ነን ማለት ነው?» አለ ፖንሴ፣ ከዚህ ቀን፣ በግልፅና በትህትና ከሚናገር ልጅ ጋር መጫዋወቱ ደስታን እየፈጠረለት።

«ኑ፣ ኑ፣ እናንተ ምንም አይነት አደጋ ውስጥ አይደላችሁም» አለ ዲሚጥሮስ። ሁለቱንም ክንዶቻቸውን ይዞ፣ ከርሱ ጉን እንዲራመዱ እያደረጋቸው። «ንጉሠ ነገስቱ ይጠብቋችኋል። እኔ ደግሞ አሽከራቸው ነኝ። ከዚህ በኋላ አዲስ ርዕስ ላይ እንነጋገራለን። ይህች አገር ሌሎች ብዙ ደስታዎችን እንደምትሰጣችሁ ታያላችሁ»

# 11

ከመንገዱ ከፍታ በመጠኑ ዝቅ በሚል አንድ ትልቅ ክፍል ውስጥ እራታቸውን በሉ:: በአንድ አጭር በር አልፈው ሲገቡ፣ መካከለኛ እድሜ ያላት ረዥምና በተለያዩ ቀለማት የተጠለፈ የጥጥ ቀሚስ የለበሰች ሴት ተቀበለቻቸው:: ሴትዮዋ፣ የተለመደው የነገስታት ዝርያ ያላት መሆንዋን የሚያረጋግጥ ጠለቅ ያለ የውበት ምልክት ይታይባታል:: ከሌሎች ክፍሎች በቀጭን የጥጥ ጨርቅ መጋረጃ ወደተለየና ጠባብ ጓዳ ወደሚመስል ቦታ መራቻቸው:: ከመጋረጃው በስተጀርባ ደብዘዝ ያሉ ቅርፆች ሲንቀሳቀሱ ይታያል:: በአቢሲኒያውያን ባህል በህዝብ ፊት ምግብ አይበላም:: ምክንያቱም የእንግዳ ሰው ዓይኖች በምግቡ ላይ ክፉ መንፈስ በማሣረፍ በምግቡ አማካይነት ወደተመጋቢው አካል ይገባል የሚል ፍርሃት አለና ነው:: ስለዚህ በምግብ ሰዓት፣ ምግብ ቤቱ በጥጥ ጨርቆች ወደተከፋፈሉ ተያያዥ የሆኑ ብዙ ትንንሽ ክፍሎች ተለውጦ ተመጋቢዎቹ ከውጭ ተመልካች አይን እንዲከለሉ ይደረጋል:: ምግብ ካበቃና ገበታ ከፍ ካለ በኋላ፣ ዓይነ ርግብ የመሰሉት ስስ መጋረጃዎች በሙሉ ወደ ጐን ሲሰበሰቡ ክፍሉ በሙሉ ወለል ብሎ ይታያል:: ተመጋቢ የነበሩትም ሰዎች በቀለማት ባሸበረቁ የቀርከሃ ጠረጴዛዎች ዙሪያ በበርጮማዎች ወይም በምንጣፎች ላይ ተቀምጠው ይታያል:: መንገደኞቹ አንድ ክንድ ያህል ስፋት ያለው ኪክ መሰል ምግብ ተመገቡ:: ይህ ምግብ የሚዘጋጀው በአቢሲኒያ ከፍተኛ ምድሮች ላይ ሲሆን ከመጋገሩ በፊት እስኪኮመጥጥ ድረስ ይቦካል:: ይህ ምግብ ሲቀርብ መላው በከባድ ቅመማት በተሠራ ወጥ ይሸፈናል:: መጠጥ የሚቀርበው በባለረዥም አንገት ብርሌ ነው:: መጠጡ ከማርና ከውሃ ተበጥብጦ የሚዘጋጅ፣ ጉዳት የሌለው የሚመስልና ከጠጡት በኋላ ግን ግራ መጋባትና በትክክል ማሰብ የሚከለክል አስካሪ ነው:: መጋረጃዎች ሲሰበሰቡና ሌሎች ተመጋቢዎች መታየት ሲጀምሩ፣ ፖንሴና ጓደኛው በዙሪያቸው ውብ ፊቶች ያሏቸውን ወንዶችና ሴቶች ተመልክተው ተደነቁ:: እንደ እውነቱ ሌሎች ተመጋቢዎችን በስሜት ሲመረምሩ ለሴቶች የተለየ ዝንባሌ እንደነበራቸው አተያያቸው በግልፅ ያስታውቅ ነበር::

«ጠንቀቅ በሉ» አለ ዲሚጥሮስ:: «እዚህ ባህሉ ፍፁም ቀላል ነው:: እነዚህ ሰዎች አመንዝራነትን እንደሃጢያት አይቆጥሩም:: ነገር ግን በምንም መልኩ በግልፅ የሚጠብቁትና



የሚጠነቀቁት ስለክብራቸው ነው:: ሁልጊዜም ሴቶችን ትንሽ እንኳ ሳታንቋሽሹ ከፍ ባለ አክብሮት ተመልከቷቸው:: አይኖቻችሁ ሴቶችን ከመመልከት ይቆጠቡ:: ይህ እነርሱ እናንተን እንዳያስተውሏችሁ አያደርጋቸውም:: ማንም ሰው ባይመለከታችሁም ሁሉም ሰው እንደሚያያችሁ እወቁ:: የተሰጠኝን የስራ ሃላፊነት ካላከበዳችሁብኝ በስተቀር ልታስታውሱት የሚገባችሁ ነገር አለ:: በዚህች አገር ውስጥ ትልቁ አደጋ የአንድ ፀጉረ ልውጥ አተያይ ነው:: በዚህች አገር ውስጥ ከአንዷ ጋር ብቻችሁን ብትገኙ፣ ያገባች ትሁን ወይም በደሟ የመሣፍንት ወገን ትሁን፣ በልባችሁ ፍላጐት እንኳ ሊያድርባችሁ ቢችል፣ ከሁሉም በፊት ወደርስዋ ፊፅሞ አትመልከቱ::»

የተገፈፈው የሰው ቆዳ በሁለቱ መንገደኞች ላይ ቀርፆ ያስቀረው ስሜት ገና ብርቱ ስለነበረ፣ ዲሚጥሮስ የነገራቸውን ከሰሙ በኋላ በዙሪያቸው ያለውን መመልከት አቆሙ:: ሌላው እንዲያውቅላቸው ጆሮአቸውን ሁሉ ወደ ዲሚጥሮስ አቀኑ::

ወጣቱ ዲሚጥሮስ፣ ኢጣሊያንኛን አቀላጥፎ ይናገራል:: ቋንቋውን፣ ግሪካዊ ከሆነችው እናቱ እንደተማረ ገልፆ፣ ሴት አያቱ ግን ቺቺሊያዊት እንደነበረች ገለፀላቸው:: እንደሌሎች የነጋዴ ቤተሰቦች የርሱዎቹም የመጡት ቀይ ባህርን አቋርጠው ሲሆን በሁኔታዎች አስገዳጅነት እዚሁ የቀሩ ናቸው:: እናቱ፣ አምስት ልጆች ሲኖሯት ከነዚህ ሁሉቱ የሚወለዱት ከአበሻ አባት ነው:: ዲሚጥሮስ ከነዚህ ዲቃላ ልጆች አንዱ ነው::

«ሰረዥም ጊዜ ያህል በከተማው ውስጥ በጣም ቆንጆው ህፃን እኔ ነበርኩ» በማለት በጥልቀት በተበሳሳው ፊቱ እየተመለከታቸው «ከዚያ በኋላ ወረርሽኝ ገባ:: ብዙ ሰዎች ሞቱ:: እኔ ግን ሕይወቴ ተረፈ:: አሁን የሚያሣስበኝም ይኸው ብቻ ነው:: ከወላጆቼ ሞት በኋላ፣ ንጉሡ እንዳገለግላቸው ወሰዱኝ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ደግነታቸው አልተለየኝም:: ገባችሁ?» ሲል ገራገር የሆነ የአክብሮት ፍርሃት በፊቱ ላይ እየታወቀበት ተናገረና «እርሳቸው ከሌሎች በጣም የተለዩ ርህሩህ ንጉስ ናቸው» አለ::

«ይህን ባህሪያቸውን የሚያረጋግጥልን ጥቂት አሣማኝ ነገር ስላየን አምናለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት

«ምን?» አለ ወጣቱ ሰው «እነዚህ ቀደም ሲል የተፈፀሙ አጋጣሚዎችን እስከአሁን እያሰባችኋቸው ነው? ያ በእውነቱ ትክክል አይደለም። አንድ ንጉሠ ነገስት እንደዚህ ባሉ ጥቃቅን ዝርዝር ጉዳዮች መፈረጅ የለበትም። አፄ እያሱ፣ እኔ እስከማረጋግጠው ድረስ ምናልባት ኢትዮጵያ በብዙ ዘመናት ውስጥ ያገኘቻቸው ድንቅ ንጉስ ናቸው። ለዚህ የሚሆን ምሣሌ ትፈልጋላችሁ? በዚህች አገር ውስጥ አንድ ንጉስ ዙፋን ሲይዝ፣ ወንድሞቹና እህቶቹ ወይም የሥልጣኑ ተቀናቃኝ ይሆናሉ የሚባሉ አምባ ላይ ይታሰሩ ነበር። ከደጋው አገር ሜዳ ላይ ሽቅብ የሚያድጉትንና የማይወጣባቸውን ከረብታዎች አይታችኋቸዋል። እነዚህ ሰዎች በዚህ ቦታ እድሜአቸውን ሙሉ ታስረው ይኖሩ ነበር። ቢያመልጡ እንኳ አካላቸው እንዲጉድል ያደርጋል። ምክንያቱም መግዛት የሚገባው ሙሉ አካል ያለው ሰው ነው የሚል የተፃፈ ሕግ አለ። እናም እያሱ ንጉሠ ነገስት መሆናቸው ሲታወጅ፣ የመጀመሪያ የነበረው ተግባራቸው፣ ልዑሎቹና ልዕልቶቹ ወደታሰሩበት ወደ አምባ ዋሸን ግርኔ ድረስ በእግር ለመሄድ ሰልፍ ማድረግ ነበር። እንደደረሱም፣ እንዲለቀቁ አዘዙና ሰዎቹ እስኪመጡ ጠበቁ። ሰዎቹ ሲመጡ ምን ይመስሉ እንደነበረ ማሰብ አትችሉም። ከተራራው ላይ እንዲወርዱ የተደረጉት ሰዎች ፍፁም የሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነበሩ። እንደ እዮብ በቅማል የተወረረ ቡትቶ የለበሱ ሽማግሌዎች ነበሩ። እነዚህ ከአፄ ኢያሱ በፊት ከነበረው ሦስተኛው ትውልድ የደም ትስስር የነበራቸው ልዑላን ነበሩ። ሕፃናትም ነበሩ። ከነርሱም መካከል አንዱ ጆሮው የተቆረጠበት ነው። ይህ የሆነው አንዲት ባሪያ ልጂ በጣም ስለራራ ሕፃኑ እንዲያመልጥ ለመርዳት በቀሚሷ ውስጥ ትደብቀዋለች። እነዚህ ሰዎች በርግጥ ሊያሳዝኑን ይገባል። ምክንያቱም ይህ የሚፈፀምባቸው ልዑላን ስለሆኑ እንጅ፣ ከሃዲዎች ወይም ወንጀለኞች ሆነው አይደለም። ባህሉ ተገቢ እንዳልሆነና አደገኛነቱንም አፄ እያሱ በትክክል ተገንዝበውት ነበር። ከእስረኞች መካከል በጣም ጀግኖች የሚባሉ፣ ለንጉሡ ጥላቻ ያላቸውና ከዙፋኑ ሊያወርዱት የሚፈልጉ እንጅ፣ በልባቸው ምንም የሌላቸው ናቸው። ይህን እስር ቤት ለመያዝ የሚችል የጠላት ሃይል ቢኖር ለዙፋኑ ሕጋዊ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉና ለበቀል የተዘጋጁ ብዙ ሰዎችን ለማግኘት ይችላል። ይህ ሁሉ ባለፉት ዘመናት የሆነ ነው። ታዲያ አፄ እያሱ ለአፍታም ሳያቅማሙ ሁሉንም ነፃ አድርገው ፈቷቸው። ልብስና ምግብ እንዲሰጣቸው አዘዙ። ለሁለት ቀናት የደስታና የምስጋና እምባ ሲረጭ ውሎ አደረ»



ጠጁ፣ የተናጋሪውን ምላስ እየያዘው ስለሆነ አድማጮቹ በትክክል እንዳያዳምጡት ይደነቃቅፍ ጀመር። በወፍራም ስጋጃ ላይ በምቾት ተቀምጠው፣ አንድ ሽማግሌ በሚጫውተው የክራር ዜማ ተመስጠው፣ ሁለቱ ፈረንሣውያን የዲሚጥሮስን አስመስሎ የመቀለድ ችሎውን እያደነቁ ቆዩ።

«ለመሆኑ እነዚህ ልዑላን የደስታ እንባቸውን ብዙም ሣይቆዩ አላደረቁትም። ደግሞስ፣ ቅናትና ጉጉትስ እውን ከልባቸው ሙሉ በሙሉ ተፍቆ ወጥቷል?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ።

«አዎን፣ ፍፁም ወጥቷል። ንጉሳችን ከነዚህ የቤተሰብ አባላት መደበኛውን የእጅ መንሣት ከመቀበል በስተቀር ሌላ ግንኙነት የላቸውም። አመፅ አስነስቶ የነበረ አንደ የወንድም ልጅ ብቻ ነበር?»

«እናም በቁም ቀዳው ተገፈፈ» አለ ሜትር ዠረሚ።

«እንግዲያውስ ታሪኩን ታውቀዋለሃ?» አለ ዲሚጥሮስ በመደነቅ አይነት

«መቋጫውን ነው?»

ወጣቱ ሰው ከት ብሎ ሣቀ።

«በዚህች ትልቅ አገር ውስጥ የንጉሡን ስልጣን የሚቀናቀነው ቤተሰቡ ብቻ አይደለም። ባላባቶች፣ መኳንንቶች፣ መሣፍንት፣ ልዑላን፣ ገዥዎች፣ ጉሣዎችና እያንዳንዱ ይቀናቀናል። በጣም አነስተኛውን ችግር ይፈጥሩብናል የምንላቸው ሙስሊም ጐረቤቶቻችን ናቸው። እነርሱ ከእስም እንድንነጠል ሊያደርጉ ቢችሉም፣ በአሁኑ ጊዜ ከኛ ጋር በጦርነት ላይ አይደሉም። ንጉሣችን ግን እረፍት የላቸውም። ይህ የሁሉም ነገስታት ሥራ ቢሆንም፣ አሁን ያሉት ንጉሥ ግን ሃያል ጥንካሬና ብርታት ስላላቸው፣ ለረዥም ዘመናት ከነበሩት ሁሉ ታላቁ ንጉሰ ነገስት ናቸው። ልዑላኑን አግባብተዋቸዋል። ጉሣዎችን አረጋግተዋቸዋል። ለሙስሊሞች ክብር ሰጥተዋል። የስራ ከንውናቸው እጅግ ከፍተኛና አስደናቂ ነው»

«ከስርዓቱ ውጭ ብሆንብህ ይቅርታ ታደርግልኛለህ» አለው ፖንሴ የማይረባ ጥያቄ የሚያቀርብ መስሎ «እኒህ ዛሬ ማታ በህይወት ያገኘናቸው ሃውልት የመሰሉ ንጉሥ፣ እንዴት

ይህን ሁሉ ሲያከናውኑ ይችላሉ ብለህ ትናገራለህ? እንዲያውስ ሙሉ በሙሉ በሌፍቴናንት ጄኔራላቸውና በቀሣውስቱ መዳፍ ውስጥ አይደሉም እንዴ?»

«ንጉሡ ነገስቱ?» አለ ዲሚጥሮስ «አታስቀኝ። እነርሱ እርሳቸውን ይፈሯቸዋል። በጣም ስልጣናቸውን ስለወሰዱባቸው ይጠሏቸዋል። ከፍተኞቹ ካህናት በጠንካራ የቤተመንግስት ቁጥጥር ስር አይደሉም። ንጉሡ፣ በመንፈሣዊ ትምህርት ላይ ያላቸው ስሜት እምብዛም ነው። ሆኖም ስልጣናቸውን ማስከበር ስለሚፈልጉ፣ ይህም የሚሆነው የቤተክርስቲያንን አንድነት በመጠበቅ ላይ ሲመሠረት መሆኑን ያውቃሉ። በካህናቱና በባላባቶች መካከል መከፋፈልን አስቀርተው፣ ሁሉንም ከጫማቻው በታች አድርገዋቸዋል። በታላቅ ስብሰባ ላይ ሕይወት ያለው ሐውልት መስለው ቢታዩ ካህናቱን፣ ልዑላኑና መሣፍንቱ ከፊታቸው ሆነው እንዲመለከቱ ለማድረግ ነው። እንዳያችሁት ሁላቸውም ደክመው ሊወድቁ ነበር»

«ከዚያ ሁሉ ክምችት ውስጥ ከሌሎቹ ይበልጥ ተሰሚነት ያለውና አንድ መልዕክት በቀጥታ ሊያደርስላቸው የሚችል የለም?» ሲል ከቆንሲሉ ተቀብሎ የያዘውን የዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ አስቦ፣ ጆን ባፕቲስት ጠየቀው።

«ከነዚያ ካያችኋቸው ውስጥ? የለም፣ አንድም እንኳ የለም። ነገር ግን ሌሎች መንገዶች አሉ»

«ለምሳሌ ባንተ በኩል?» ሲል ጆን ባፕቲስት፣ ዲሚጥሮስን እየተመለከተው ጠየቀው።

«እንዲህ ያለ ነገር ስታስቡ ለኔ እጅግ ከፍተኛ ክብር ነው»

በጨለማው ጉዳና ውስጥ እየተንገዳገዱ ወደ ቤት ተመለሱ። ዲሚጥሮስ፣ እስከበራቸው ድረስ በዓይኑ ተከተላቸው። ጆን ባፕቲስት ከመተኛቱ በፊት የመድሃኒት ቅመሞችንና መጠናቸውን የጻፈበትን ደብተሩን በመድሃኒት ሣጥኑ ውስጥ ፈለገ። አንዲት አነስተኛ የመጻፊያ እርሳስ በአንድ ኪሱ፣ የማስታወሻውን ደብተር በሌላ ኪሱ አስቀመጠ።

«ነገ ደግሞ ማስታወሻ መውሰድ እጀምራለሁ።» አለ ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ እየተጋደመ



«ለምን?» አለ ሜትር ዠረሚ መንጋጭላው እስኪላቀቅ ድረስ አፉን ከፍቶ እያዛጋ።

«በመጀመሪያ ደረጃ አስደናቂና አስደሳች ነው። ሁለተኛ ነገር ከዚህ አገር የምንወጣበትን ዘዴ የምናገኝበት ስለሚሆን ነው»

❧

ገና ድቅድቅ ጨለማ እያለ በመዝጊያው ጎኑንቸር ውስጥ የመክፈቻው ቁልፍ ሲተሻሽ ጆን ባቲስት ሰማ።

በአልጋው ስር የደበቀውን ጉራዴ አፈፍ አደረገው። በሩ በዝግታ ተከፈተ። አንድ ሰው አጭር ሻማ በሸክላ መቅረዝ ላይ ይዞ ቆሟል።

ጆን ባፕቲስት ዘልሎ ሲነሣ፣ ተረጋግቶ ጠበቀ። ወዲያውኑ፣ ግዙፉ የሜትር ዠረሚ ጥላ ድምፁን አጥፍቶ ወደ በሩ ዘልሎ ሲወረወር የጉራዴውን ብርቅርቅታ ተመለከተ። ፕሮቴስታንቱ፣ በቅፅበት ደርሶበት የጉራዴውን ሹል ጫፍ በሰርጐ ገቡ ሰው ደረት ላይ አሳረፈው። እንግዳው፣ እጆቹን በመማረክ ብድግ ሲያደርግ የያዘው የሻፍ መብራት በፊቱ ላይ አበራበት። ዲሚጥሮስ ነበር።

«በዚህ ውድቀት ሌሊት ምን ትፈልጋለህ?» ሲል ሜትር ዠረሚ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ።

«እህ! እባካችሁ ምንም ድምፅ አታሰሙ። ጉራዴያችሁንም አስቀምጡ» አለ ዲሚጥሮስ በሹክሹክታ።

ሜትር ዠረሚ ፈንጠር ብሎ ሲቆም ዲሚጥሮስ ወደ ክፍሉ ውስጥ ዘለቀ።

«ልብሣችሁን ልበሱ» አለ ዲሚጥሮስ በርጋታ

«እንደለበስን ነን»

«እንግዲያውስ ተከተሉኝ። አንዳችም የሚያስፈራችሁ ነገር የለም»

ሁለቱ ጓደኛሞች ለአፍታ ያህል ርስ በርሳቸው ተያዩ። ጕራዴያቸውን አስቀምጠው ወጣቱን ሰው ተከተሉት። ከቤቱ ውስጥ ሳይወጣ ቀደም ሲል አይተውት እንደነበረና ወደ ጣሪያው የሚአስወጣ ሳይሆን እንደማይቀር በገመቱት በር በኩል ሄደ። ይህ በር ወደ ጣሪያው የሚያደርስ ሳይሆን ወደ አንድ ጠባብ የመተሳለፊያ ቦታ ያመራል። ሁለት ሌሎች በሮችን ሲያልፉ፣ ግድግዳው የተሠራበትን የድንጋይ ቅርፅና መጠን ሲገነዘቡ በቤተመንግስቱ ውስጥ እንደሆኑ አወቁ። ዲሚጥሮስ ከፊት ከፊታቸው እየተራመደ በአንድ በሚጠማዘዝ ደረጃ ላይ ሲወጡ፣ በጠባቡ ሳንቃ መስኮት በኩል ቀዝቃዛ ነፋስ ከውጭ ይገባል። በመጨረሻም የመተኮሻ ቀዳዳ ያለውና የቤተመንግስቱን ምሽጐች ሁሉ መመልከት የሚያስችል የግንብ አናት ላይ ወጡ። ሰማዩ ደመና የሌለበት ንፁህ ነበር። ከተማ ውስጥ፣ በቃፊር ጣቢያዎችና በጥበቃ ቦታዎች ከሚታዩት የእሣት ፍሞች ሌላ የለም። ሰማዩ ጣሪያ ሆኖ ከዳር እስከዳር ምድሪቱን ሲሸፍን፣ ልክ የሃር ጨርቅ በመልኩና በፊርሱ ብቻ እኩል የተረጨበት ሆኖ የሚያንፀባርቅ ይመስላል። በአቢሲኒያውያን ደጋ ምድር ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ተጓዦች ከአገራቸው እጅግ ርቀው መኖራቸውን በትግስት ቢያስቡትም፣ ሰማዩ ግን ሁልጊዜም ያስታውሣቸዋል። በቆሙበት ቦታ ላይ ባሉበት የመታኮሻ ቀዳዳዎች በደቡባዊ በኩል ያለውን መስቀል ይመለከታሉ።

የግንቡን እያንዳንዱን ማዕዘን ከሚያመለክቱት ጉልላቶች አንዱ ላይ ጕንበስ ብሎ እስኪያልፍ ድረስ፣ ዲሚጥሮስ እንደ ሕፃን መራቸው። ጉልላቱ፣ እንዲት እኩል አራት ማዕዘን ለሆነች ክፍል ጣሪያ ነው። ክፍሏ በአንድ የእንጨት ጠረጴዛና በአራት በርፖማዎች ተጊጣለች። በአንደኛው ላይ አንድ ሰው ተቀምጧል። ሰውዬው፣ በወገቡ ላይ የጥልፍ ቀበቶ ያለበት ቀላል ነጭ ጃኬት ለብሷል። አንድ ክርኑን ጠረጴዛ ላይ አሣርፎ፣ ወደ ጧፉ ጕንበስ ብሎ ተቀምጦ ቢቆይም እነርሱ ሲደርሱ ቀና አለ። ከአይኖቹና ከአፍንጫው ቅርፅ ህይወት ያለው ሐውልት፣ ረጋ ያለ ጣኦት ይመስላል። እውነቱ ግን በዘያኑ እለት ጧት ከፊት ለፊታቸው ቀርበው የሰገዱላቸው ንጉሠ ነገስቱ እንደሆኑ አወቁ። ፖንሴ፣ ለአፍታ ያህል አመነታ። እንዲህ ባለች ጠባብ ክፍል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወለሉ ላይ መዘርጋት ይኖርባቸዋል? ይህ ምቾት የሌለው ጉዳይ ነው። ጆን ባፕቲስት ስለሠውነት ቀዳው ባይጨነቅ ኖሮ፣ ፊቱን በመሣቀቅ ከፉኛ ሊያጨማድደው ነበር። ነገር ግን ንጉሡ በሁለቱም ጕናቸው ያሉትን በርፖማዎች አመለከቷቸውና ትንሽም እንኳ እፍረት ሳይሠማቸው በሁለቱም ምንጣፎች ላይ ተንጋደ ወድቆ የነበረውን ሌላውን በርፖማ አቃኑት።



ሁለቱ ፈረንሣዮች በትንሹ ከአንገታቸው ዝቅ አሉና ከንጉሡ ጕን ተቀመጡ። ከሁኔታው ጋር በመያያዙ እንጂ፣ ንጉሠ ነገስቱ ከሌሎች ዜጐቻቸው ይህን ያህል የሚጋነን የበለጠ ግርማ አልነበራቸውም። አቢሲኒያውያን ላይ የሚታየው አይነት የረጋና የልኬዋ መልክ ቢታይባቸውም፣ ንጉሠ ነገስቱ ፊታቸው ዕረፍት ሲያገኝ የሐዘንና የመሳቀቅ ነገር በግልፅ ይታይባቸው ነበር። ሁለቱን ባዕዳን ሰዎች እንደተመለከቱ ሞቅ ያለ ፈገግታ አሳዩዋቸውና ወዲያውኑ ደግሞ ያ የቀድሞው የድካም አተያያቸው ተተካ። በሰውነት አቋማቸው ሲታዩ፣ በነገስታት ዝርያ አኳያ አነስ ያሉና ሲበዛ ቀጭን ሰው ናቸው። እድሜአቸው አርባ አመት የሚሞላቸው ሲመስሉ በመጠኑ ከትከሻቸው ጐበጥ ይላሉ። በአይኖቻቸው ላይ የጭካኔ እሳት የሚተፉና ድንጋይ ልብ መሆናቸውን የሚያመለክት ነገር የለባቸውም። ከአንድ ቀን በፊት በአስፈሪው የስቃይ ቅጣት ማዘናቸውን የማያውቅ፣ አዝኖላቸው፣ እኒህ ይልቁንስ የደከሙ ለንቋሳ ሰው ናቸው ይላቸው ነበር።

«ስላየኋችሁ ደስ ብሎኛል» አሉ ለስለስ ባለ ድምፅ

ዲሚጥሮስ ቃላቶቻቸውን ወደ ኢጣሊያንኛ ተረጐማቸው

«ግርማዊነትዎ ታላቅ አክብሮት አድርጐልናል . . . » ሲል ጆን ባፕቲስት ጀመረ።

ንጉሡ፣ የዲማጥሮስን አስተርጓሚነት አቋረጡ

«አትቸገሩ» አሉ «ይህ ዋጋ የለውም □□ እነርሱም የሉም»

ፖንሴ መናገር አቃተው።

«ለካህናቱ ደህና አድርገህ ነው መልስ የሰጠሃቸው» ሲሉ ንጉሡ አስተያየታቸው ግዴለሽ በሚመስል መልክ ቀጠሉ።

ባለማቋረጥም በክንዳቸውና በሆዳቸው አካባቢ እንደሚያክኩ አስተዋሉ።

«አምን፣ ያሳችኋቸው ቃላት ሁሉ ተነግረውኛል። እነሱ ጥበበኞች ናቸው። እኔም እንደናንተው ከእንግዲህ በኋላ እነርሱ በሚያወሩት ተአምር አላምንም። የነርሱ ተአምሮች ትኩሣትን እንኳ ሲያድኑ አይታወቅም። ከመንፈሣዊው አለም በምናገኘው ምልክት ስለመጭው

ዘመን ማወቅ እንችላለን የሚለው ሥነ ስራታቸው ሁሉ ማታለል ነው። አንድ በራሪ ኮከብ በታየበት ጊዜ ስለኔ መሸነፍ አስቀደሙው መናገራቸውን ሰምታችሁ ይሆናል። ይህ መቼም ሁል ጊዜ የሚደረግ ነው። ውድቀቱን በእጅጉ ስለሚፈልጉ ፣ከዋክብት ብርታቱን እንዲሰጧቸው እንደለመኑ ናቸው። ይሁን እንጅ እናንተ ካቶሊክ ካልሆናችሁ የኛንም አይነት ካልሆናችሁ ሃይማኖታችሁ ምንድን ነው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ የተሃድሶ ቤተክርስቲያን ይባላል» አለ ፖንሴ

«ጀስዊቶች እዚህ በነበሩበት ጊዜ ስለዚህ ቤተክርስቲያን ፍፁም ተናግረው አያውቁም።»

«ጥሩ ምክንያት አላቸውና ነው። እነርሱ እጅግ መጥፎዎች ጠላቶቻችን ናቸው።»

«አምናችኋለሁ።» አሉ ንጉሠ ነገስቱ

ቀጠል በማድረግ ድክም ያለውን አመለካከታቸውን ወደ ሜትር ዠረሚ መለስ በማድረግ በዝግታ ቀጠሉ።

«ይሁንና ይህ ሰው ከነርሱ አንዱ ነው ብዬ እምል ነበር።»

«ጀስዊት!» አለ ፖንሴ

ሜትር ዠረሚ አመዱ ቡን አለ

«አዎን፣ ወይም የነርሱን ዘዴ ለማቆየት የሚጥር ቄስ ነገር ይሆናል ብዬ ነበር» በማለት ጆን ባፕቲስትን በድጋሜ እያጠኑት ተናገሩ «አንተ ዶክተር መሆንህን አውቃለሁ። እርሱ ግን ሲራራውን የተቀላቀለው እንደ ሌባ ወይም እንደ ቄስ በኋላ ነው»

ሜትር ዠረሚ ዘልሎ ሊነሳ ነበር። ፖንሴ ክንዱን አጥብቆ ይዞ አቆየው።

«ደግነቱ ሃጅ አሊ ሁሉንም ታሪክ ነግሮኛል። ይህ ሰው የስራ ሸሪክህ እንደሆነና ፈረንሳዮቹ ግን ሲራራውን እንዳይቀላቀል መቃወማቸውን ተገንዝቤአለሁ። አትፍሩ፣



አምናችኋለሁ። ስለመድሃኒት ችሎታው እንዳላችሁ በግልፅ ይታወቃል። የኔ ፍላጐት ደግሞ ይኸው ብቻ ነው። ያለን ጊዜ አጭር ስለሆነ ሕመሜን ላሣያችሁ።»

የጧፍ ነበልባሎች በድንጋዩ ጉልላት ላይ ጥላቸውን አጥልተዋል። በጣም ከፍ ያለውና ባለጉልላቱ ጣሪያ ዋሻ ይመስላል። ሰማይና መሬት እየተሳቀቀ ሲሆን፣ ከበላያቸው ባለው ጨለማ ውስጥ በአንድ ወደ ምሸራቅ በሚከፈት ጠባብ መስኮት ሰማያዊውን ሰማይ መለየት ችለዋል።

ንጉሠ ነገስቱ ቀበቶአቸውን ፈትተው ቆሙ። በቀልጣፋ እንቅስቃሴ ጃኬታቸውን አወለቁ። ፖንሴ ቀረብ ብሎ በዝምታ መረመራቸው።

«ልትነካው ትችላለህ።» አሉት ንጉሠ፣የዶክተሩን ማቅማማት ተመልክተው።

ሜትር ዠረሚ ጧፉን ከፍ አድርጐ እንዲይዝለት ጠይቆት፣ ፖንሴ የተጐዳውን አካባቢ መረመረ። ይህን ጉዳት ለማየት በመቻሌ የታደልኩኝ ነኝ ሲል አሰበ። ይህ ቁስል፣ ከሃጅ አሊ ቁስል ጋር አንዳችም መመሣሰል የለውም። ከወገባቸው በላይና ከሆዳቸው አካባቢ ንጉሡ ትልቅና በተሠነጣጠቁት ቦታዎች መግል የሚያዥበት ነው። ዶክተሩ ሌላም የተጐዳ ቦታ እንዳለ ቢፈልግ ማግኘት አልቻለም። ሕመምተኛውን ወደዚህና ወደዚያ እያዟዟራቸው ብዙ ጊዜ አያቸው። ማንም ሰው ይህን ቡድን ከቅርብ ርቀት ሆኖ ቢመለከተው በጣም የሚያስገርም ትርዒት ማየት ይችላል። እርቃናቸውን የቆሙት ጉባጣው የነገስታት ንጉስ ያንን ጭራሮ አካላቸውንና ሰፋፊ ቁስል ሁሉም እንዲያየው በትህትና ገልጠውታል። በጐናቸው የተዋጊ ቅርፅ ያለው ግዙፉ ሜትር ዠረሚ ጧፉን በፀጥታ ይዞ ቆሟል። ጆን ባፕቲስት ሕመምተኛውን በእርጋታ ይነካቸውና የህመማቸውን ምንነት ለመረዳት ጥረት ያደርጋል። አንድን ንጉስ በታዛዥነት ከማገልገል ይልቅ፣ ወንድማዊ ተግባሩን ማከናወኑን መመልከት በራሱ ትርዒት ነው።

«ስመሆኑ የሕመም ስቃይ አለው?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ።

«አዎን» አሉ ንጉሠ ነገስቱ «ሆኖም የህመሙ ስቃይ ምንም አልነበረም። ማሣከኩ ነው የከፋው።»

ዶክተሩ ምልክት ሲሰጣቸው ልብሦቻቸውን ለበሱ።

«ብዙ ሰዓት የፈጀውን ያንን ስብሰባ አስቡት» ሲሉ ንጉሱ ቀጠሉ «በጥፍሮቼ ስጋዬን እንዳልቆፍረው ፍርሃት ነበረኝ። ሆኖም መንቀሳቀስ አልነበረብኝም። ያለተራቸው እንደዚያ የሚለፈልፉት እነዚያ ውሾች መታመሜን ያውቃሉ።ሊያውቁ የሚችሉትም ይህንን ብቻ ነው።በህመሜ ስሰቃይ እንዲያዩኝ አልፈልግም ፤ወይም የህመሜ ሲቃይ አስገድዶኝ በፊቴ ላይ የሚነበበውን ስሜት እንዲያውቁ አልፈልግም። መንፈሴ ሳይሰበር መታየት አለበት። ይህ ካልሆን ቦጫጭቀው ይጥሉኛል»

በጠረጴዛው ዙሪያ ተመልሰው ተቀመጡ።

«ለመሆኑ ህክምና ወስደው ነበር?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቃቸው።

«ጥቂት ነገሮችን ሞክሬአለሁ። ገላ መታጠብን፣ በጭቃ ቁስሉን መድፈን፣ የእናቴ አዋላጅ የነበረችና ጥቂት የመድሃኒት እውቀት አለኝ የምትል አሮጊት ሴት፣ የሆነ ዱቄት ሰጥታኝ ነበር።»

«እናስ?»

«እየባሰ፣ እየባሰ መጣ»

«እንትንስ፣ እንትንስ . . . » ፖንሴ አቅማማ። « . . . ለሃያ አመታት ምንም ሳይቀምሱ የኖሩት ታላቁ ቅዱስስ?»

«ምን? ሰምቻለሁ እንዳትለኝ? ቀንና ማታ እንዲጠብቁ አደረግሁ። በመጡ በማግስቱ ገና ሰማይና መሬት ሳይላቀቅ በአራት እግራቸው እየዳሁ ማድ ቤት በወይራ ፍሬ ቋንጣን ይዟቸው ተገኙ። ከነሆዳቸው ወደ ገዳማቸው እንዲመለሱ አዘዝኩ»

አራቱም ሣቁ

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ «ለህመምዎ የሚሆን ቅባት እናዘጋጅልዎታለን። ሆኖም ግን መድሃኒቱ አስቀድሞ በአንድ ባሪያዎ ላይ ይሞከር?»



«አይደረግም። ለካህናቱ የፈለጋችሁትን የማይጉዳ መድሃኒት ስጧቸው። ለኔ ግን የመድሃኒት ማዘዣችሁን በቀጥታ በዲሚጥሮስ በኩል ላኩልኝ። እንዴት እንደምጠቀመው ስርሱ መንገራችሁን አትርሱ»

«የኛን መድሃኒት ሲወስዱ ሌሎች ህክምናዎችን ሁሉ የግድ ማቋረጥ ይኖርብዎታል።»

«አትስጉ»

«የህክምናችንን ውጤት ለመወሰን በሁለት ቀናት ውስጥ በድጋሚ ልናይዎ አስፈላጊ ይሆናል»

«ስብሰባዎቻችን አደገኞች ናቸው። ስለስብሰባዎቻችን ማንም ሰው ሊያውቅ አይገባውም። እኛም ከሚያስፈልገው በላይ ልንገናኝ አይገባንም። ከዛሬ ጀምሮ ለሁለት ቀናት ሁኔታዎችን ለማስተካከል እሞክራለሁ። እናንተ ግን ትዕግስት አትጡ። ይህን ደግሞ በፍፁም ትንፍሽ ማለት እንደሌለባችሁ እወቁ»

ንጋት ተቃረበ። ፊቶቻቸውን ግራጫና አመዳም የሚያስመስል ሰማያዊ ብርሃን ክፍሉን ሞላው። ንጉሠ ነገስቱ በአንዲት ጠባብ በር በኩል ትተዋቸው ወጡ። በምሽት ግዳግዳ በኩል ተመልሰው ቤታቸው ገቡ።

«ህመማቸው ምን እንደሆነ አውቀሃል?» ሲል ዲሚጥሮስ ወጥቶ ሲሄድ ሜትር ዠረሚ ጠየቀው።

«አውቄዋለሁ ለማለት አልደፍርም። ሕመሙ ግን ከባድ ነው»

## ፩

ኮስተር ብሎ ተጀምሮ በደስታ ከታጀበው ከመጀመሪያው ምስጢራቸውና ተከትሎት ከመጣው ጥልቅ ወደጅነታቸው በኋላ፣ አሊስና ፍራንቾይዝ የዕለት ተዕለት ወደ ሆነው

አሰልቺው የጆን ባፕቲስት እፅዋት እንክብካቤ ጥልቅ ብለው ገቡ። ውይይታቸው ሁሉ የሚገመት አቅጣጫ እየያዘና መልካሞ ጊዜ ይመጣል ብለው የሚያስቡትን ሁኔታ ማንፀባረቅ ጀመረ። ሁልጊዜም በዚያ ቦታ ተወስነው መቅረታቸውና የሚጠብቋቸውን ሰዎች በእርግጠኝነት ያስገኝላቸዋል የተባለው ቤት፣ ቀስ በቀስ ስቃይ የበዛበት የተራዘመ አለመገኘትን የሚያሣያቸው ሆነ። አንዳቸውም ራሳቸውን በትክክል መቆጣጠር አልቻሉም። ምንም እንኳ ሰላም ወዲያውኑ ቢወርድም፣ በማይሆን ነገር ላይ ሁለትና ሶስት ገዜ ተጣልተዋል። ይህ ደግሞ ግንኙነታቸውን ያለ አንዳች ዓይነት ለውጥ ለረዥም ጊዜ ሊዘልቅ እንደማይችል የሚያስጠነቅቃቸው ነበር። በዚህ የተነሣ አሊስ አንድ ሃሣብ አመጣች።

«አንቺ እንድታገለግያት፣ እናቴን ባግባባት ምን ይመስልሻል?» ስትል ፍራንቾይዝን ጠየቀቻት። «እየተመላለስሽ ስትሰሪ በቆንስላው ውስጥ ልንተያይ እንችላለን። በበኩሌ ላንቺ የጠለቀ ወዳጅነት እንዳለኝ በማሣየት ጓደኛዬ ተደርገሽ እንድትመደቢልኝ አደርጋለሁ። ለሽርሽር አብረን እንወጣለን። እዚህም ቢሆን ልንመጣ እንችላለን። ነገር ግን ሁልጊዜም እዚህ ቦታ ብቻ ለመገናኘት መገደድ አይኖርብንም»

ፍራንቾይዝ ለሃሣቡ አጨበጨበች። ከዚህ በኋላ ማዳም ዴ ማይሴን የሚያግባቡበትን ዘዴ መሻት ይኖርባቸዋል። እቅዱ ገና ፍሬ ሳያፈራ በህይወታቸው ውስጥ የጋለ ስሜት አጫረባቸው።

አሊስ፣ የአንዲት የጠፋች ፈረንሣዊት ሴት ልጅ ሁኔታ ስሜቷን እንደነካው ለእናቷ መንገር ጀመረች። በመድሃኒት ዕፅዋቱ ማሣደጊያ አጠገብ በደሣሣ ጐጆ ውስጥ የምትኖር ምስኪን ሴት ተክሎቹን በመንከባከብና ውሃ በማመላለስ ትረዳታለች። ቀደም ሲል ወጣቷ ወይዘሪት፣ ምስኪኗ ሴት ስላደረገችላት ዕርዳታ ጥቂት ሣንቲሞችን ልትከፍላት እንድትችል እናቷን ጠየቀቻት። ቀጠል አድርጋ የዚህችን ምስኪን እድለቢስነቷን ማስረዳት ቀጠለች። በጨዋታቸው መሃል፣ ይህች ምስኪን በጠባይዋ መጥፎ እንዳልሆነችና የአርባ ቀን እድሏ በዚህ ጨካኝ ከተማ ውስጥ ቤሳ ቤስቲን የሌላት ምስኪን አድርጐ እንዳስቀራት ነገር ጣል ታደርጋለች። እናትና ልጅ፣ የዚህ አለም ሃዘን እርር ኩምትር ያደረጋቸውን ምስኪኖች ያስባሉ። ማዳም ዴ ማይሴ ደግሞ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ካለ የማታ እራት የማጣት ጊዜ ጠብቆ ስላቆያቸው ታመሰግናለች። ሁለቱ የሚወያዩባቸው ርዕሶች አልነበራቸውም። አሁን ግን



ፍራንቾይዝ ለውይይታቸው ተመራጭ ርዕሣቸው ሆነች። ከእለታት አንድ ቀን ማዳም ዴ ማይሴ፣ ስለዜጐቻቸው ተመፅዋችነት ወሬ ስትጠይቃት ጉዳዩን አፍረጥርጣ ለመናገር የቆረጠችው አሊስ በተስተካከለ ድምፅ

«አዕምሮዋ ፍፁም ሰላማዊ ነው። ሴትዮዋ ውሳኔ ላይ ደርሣለች።»

«የምን ውሣኔ?»

«ነግሬሽ ካልሆነ ረስቼዋለሁ። በጣም ሃብታም የሆነ ቱርካዊ ሰው ሊያገባት ጠይቋት ነበር። ይህ ጋብቻ ለሕይወትዋ ዋስትና ይሰጠው ነበር። በርግጥ ለመወሰንና ላለመወሰን ስታወላውል ረዥም ጊዜ ትቆያለች። ሰውዬው ሽማግሌና አስቀያሚ ነበር። ቢያገባት እርሷ እራተኛ ሚስቱ ትሆንና የጋብቻውን አሳመቺነት ከቀሩት ሦስት ሚስቶች ጋር መጋራት ሊኖርባት ሆነ።»

«ያስፈራል» አለች ማዳም ዴ ማይሴ «የክርስቲያን እምነቷንም ለመተው ቃል መግባት ግድ ሊሆንባት ነው?»

«የማመንታቷ ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው። በጣም ሃይማኖተኛ ስለሆነች ክርስትናን መካድ ለርሷ ፍፁም ሞት ነበር»

«እሺ እና በመጨረሻ ምን ወሰነች?» ስትል የአሊስ እናት ጠየቀች።

«ቱርካዊው ሰውዬ፣ እስልምናን መቀበል ክባድ ሸክም አይሆንም፤ ዝም ብለሽ እግዚአብሔር ማለት አላህ ማለት ነው፣ መሃመድም የአላህ ነብይ ናቸው ትያለሽ። የምታደርጊውም ይህን ብቻ ነው። ሙስሊሞች ክርስቶስን እንደ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ተቀብለውታል። ከመሃመድም ይቀድማል። ለርሱ ልትፀልይ ይፈቀድልሻል ይላታል። በአጭሩ ቱርካዊው ሃይማኖቷን ብትለውጥ ምንም እንደማታጣ፣ በአኳያው ግን ቢያንስ በየለቱ ሆዷን [illegible]ልታ ልትበላ እንደምትችል ያሣምናታል።»

«ልጄ» አለች ማዳም ዴ ማይሴ፣ አይኖቿን በስጋት በልጥጣ «ይህች ምስኪን ሴት ጠፍታ ትቀር ነበር። እነዚህ አረመኔዎች የሚናገሯቸውን፣ ሰው መስማት የለበትም። ቅድስት ከተማችንን በመቆጣጠር በሺህ የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያኖችን አወደሙ። ቁጥራቸው በውል

ያልታወቀ ክርስቲያኖችን ገደሉ:: የሚከፈለውን ከፍለን ቱርካዊ እንዳትሆን በተቻለን መከላከ ይኖርብናል:: ከሠማሁት ተነስቼ የተገነዘብኩት እነዚህ በሚስቶቻቸው ላይ ሲበዛ ባለጌዎ የሆኑ ሰዎች መሆናቸውን ነው:: ሴትዮዋ እንዲህ ያለውን ሰው ብታገባው በምድር ላ መሞቷ ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም ነፍሷን ለሲኦል ሰጥታው ትቀራለች::»

ሁለቱ ሴቶች፣ ይህን አስፈሪ ውጤት ያለውን ጭውውት ለማስወገድ ሌላ ዘዴ ፈለገ በመጨረሻም ፍራንቾይዝ እነርሱን ለማገልገል እንድትገባ አሊስ ሃሣብ አቀረበች:: እናቷ ሃሣቡን በቁም ነገር ተቀበለችው::

«አዎን አስቤበታለሁ:: ልብስ አጣቢያችን ወደ ፈረንሳይ ከተመለሰችበት ጊዜ ጀም ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እርሷን በሌላ እንዲተኳልኝ ስጠይቀው ነበር:: እርሱ ግን ይህን ቦታ ሊሸፍ የሚችል ብቃት ያለው ሰው በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ የለም እያለ ሁልጊዜም ይመልስል ል:: እንደሚመስለኝ እርሱ በኢኮኖሚው የሚገፋፋ ነው:: የአገሪቱን ገንዘብ ወጭ የማድረ ጉዳይ በተነሣ ቁጥር አባትሽ ሁልጊዜም ሲበዛ የመመጠን ነገር ያሣያል::»

«ይህ የተሳሳተ የኢኮኖሚ አስተሣሰብ ይመስለኛል:: የልብስ አጠባውን ተግባ የተረከቡት ሁለቱ ኑቢያውያን ባሪያዎች የብዙ ልብሶችን ቀለማት አበላሽተዋል:: የናይለ ልብሶችንም ሲበዛ የማጠቢያ ሶዳ እየተጠቀሙ እያቃጠሏቸው ነው::» ስትል ሃሳ ያልተዋጠላት አሊስ ተናገረች::

«ልብስ ሲተኩሱ ያለውን ትተን፣ ብርግጥ ጥፋት ነበር:: ይሁንና እንደአለመታደ ሆኖ አባትሽ ለዚህ አይነት ጉዳይ ቁብ አልነበረውም:: ልብሶቹን በተመለከተ ቅሬታው የሰማሁት ከጥቂት ወራት በፊት አረንጓዴ የሃር ካልሲዎቹ፣ ከኔ ባርኔጣዎች ጋር አብረው ተነክረው ቀይ ሽክላ መስለው ሲወጡ የተናገረው ብቻ ነው::»

«ይኸውልሽ፣ አየሽ? ከትርፉ ይልቅ እውነተኛ ልብስ አጣቢ በማግኘት የሚገኘውን ጠቀሜታ እንዲገነዘበው ልናደርገው እንደምንችል እርግጠኛ ነኝ:: አባቴ፣ ለስራው ዕጦ ለማግኘ ት ጊዜ የለኝም ይላል:: እስከ አሁን ያለው ቢቀር አንድ ማግኘታችን ራሱ ጥሩ ነገር ነው»



አሊስ ጥሩ አድርጋ ተከራክራ ስለአሳመነቻት፣ እናቷም ጉዳዩን ለሙሴ ዴ ማይሌ ልታቀርብለት ተስማማች:: ምንም እንኳ የሰው ህይወት በእግዚአብሔር እጅ ያለ በመሆኑ ለማዳን ምንም ማድረግ ባትችልም፣ የኃይማኖተኛዋ ሴት ነፍስ ከትክክለኛው መስመር ወጥታ ስትጠፋ ከማየት ይልቅ ልታድነው ፈቃደኛ ሆነች::

«ጉዳዩን ለአባቴ እንዴት አድርገሽ ነው የምታቀርቢለት?» ስትል አሊስ ጠየቀቻት::

«ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ:: ነገሮችን መደባበቅ ጥሩ አይደለም:: አንቺ እንደነገርሽኝ እኔም ሁሉንም ሐቅ እነግረዋለሁ::»

ፈገግ ሳለማለት አሊስ ራሷን ተቆጣጠረች:: ነገር ግን የእናቷን ቃላት ለፍራንቾይዝ በሌላ ጊዜ ስትነግራት ሁለቱም ከት ብለው ስቀዋል::

ሙሴ ዴ ማይሌ፣ አቋሙን አለሣልሶ፣ የልብስ አጠባውን ጉዳይ ለሁለት ሣምንታት የሙከራ ጊዜ ብቻ ለመጠቀም ለባለቤቱ ፈቀደላት:: የቤት ውስጥ ጉዳዮችን እንዳይረዳ ሥራ ለሚበዛበት፣ ፍራንቾይዝ በአጭሩ እንድትተዋወቅ በመደረጉ፣ የባለቤቱ የማዳም ዴ ማይሌን ልብ ማሸነፍ ቻለ:: ከመጀመሪያው ዕለት ጀምሮ አዲሷ ልብስ አጣቢ በጥንካሬ መስራት ጀመረች:: ምንም እንኳ ቸልተኛ ቢሆንም፣ ከሁለት ሣምንት በኋላ ቤቱ መስወጡን ቆንሲሉ አረጋገጠ:: ልብሶቹ እንደበፊቱ ማብረቅረቅ ጀመሩ:: በፖንሴ ቤት ከሚገኙት ዕፀዋት በቀመመቻቸው ማጠቢያዎች ፍራንቾይዝ የተበላሹትን የቆንሲሉን የእግር ሹራቦች የጀመሪያው ቀለማቸው እንዲመለስ ለማድረግ ቻለች:: ሴቶቹ ሽሮ የመሰለ የወየበ ልብስ ከመልበስ ይልቅ ነጭ መልበስ ቻሉ:: ከሁሉም በላይ ፍራንቾይዝ በጣም የቆሸሹትን የቆንሲሉን ሁለት ሙሉ ልብሶች ተራ በተራ በእርጋታና በእርግጠኝነት በጥንቃቄ ያዘቻቸው:: ከእለታት አንድ ቀን ማለዳ፣ ፀሐፊው የወረቀት ክምር ይዞ ወደ ፅሕፈት ቤቱ ሲገባ፣ አንድ ነገር እንዳጎደለ ቆንሲሉ ተገነዘበ:: የከፍሉን ዙሪያ ቢቃኝም፣ ከተለመደው ውጭ የሆነ ነገር ማግኘት አቃተው:: ነገር ግን ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሙሴ ማቼን ሲመለከተው ፀሐፊው እንዳችም እፍንጫ የሚወጋ ጠረን እንደሌለው ተገነዘበ:: ስለዚህ ለዚህ ሁሉ ፍራንቾይዝ ተቀጥራለች::

እንደታቀደው፣ አሊስና ፍራንቾይዝ ጓደኝነታቸው በቆንስላው ውስጥ ቀጠለ:: ወጣቷ ልጃገረድ በየዕለቱ ማለዳ ዕፅዋቱን ለመንከባከብ ትሄዳለች:: አሊስ ብቻዋን ትሄድና ከበፊቱ

ይልቅ አጭር ጊዜ ብቻ ትቆያለች። ከዚያም ትመለስና በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ትላለች። ሙሴ ዶ ማይሌ የያዛቸው የቤቱ ክፍሎች፣ የክብረ በዓል ክፍል ማለትም የንጉሡ ሥዕል ያለበትና ጥቂት የሚዋሰኑ ክፍሎች፣ ብዙ ጊዜ ባዶ የሚሆኑት በሁለተኛው ፎቅ ላይ ለጉብኚ ባለስልጣናት የሚሆኑ አፖርታማዎች ናቸው። ማዳም ዶ ማይሌ በበኩልዋ ከክፍሏ እምብዛም አትወጣም። የተቀረው የቤቱ ክፍል ለምሳሌ የመፀዳጃ ክፍሎች፣ የመተላለፊያ ክፍሎች፣ የእሲስ መኝታ ክፍል፣ የመልበሻ ክፍሎች፣ የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች፣ ጓዳዎች፣ የልብስ ማጠቢያ ክፍሎች ሁሉ፣ ለሁለቱ ጓደኛሞች መገናኘት ምቹ ቦታዎችን ሰጧቸው። የተለያዩት አካባቢዎች ግብረ አበርነታቸውን በውበት አደሰላቸው። ጥንቃቄአቸውንም የሚያጓጉ አደረጉላቸው። ሁለቱም ሁሌም ጥንቃቄ ቢያደርጉም በዚያ ሰፊ ቤት ውስጥ ለመወያየት አንድ ሺህ እድል ሰጣቸው።



# 12

ያልተጠበቀውን ውይይት ከንጉሡ ነገስቱ ጋር ባደረጉ በሚቀጥለው ማለዳ፣ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዣሪሚ ሁለት መድሃኒቶችን በማዘጋጀት ራሣቸውን በሥራ ወጥረው ነበር። ከመድሃኒቶቹ አንዱ፣ ለንጉሡ የሚሄድላቸው ሲሆን ሁለተኛው ካህናቱ እንዲመረምሩት ይላክላቸዋል።

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ በየአመቱ የዝክር ድግስ በሚደረግበትና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ወደሚሠበሰብበት ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ትልቅ ቤተክርስቲያን፣ ዲሚጥሮስ ይዟቸው ሄዱ። ፀሐይ ደማቅ ብርሃኗን ታበራለች። በያንዳንዳቸው አዕምሮ ውስጥ የነበረው የመጨረሻው ነገር የስቃይ ቅጣቱ ነበር። ዐይኖቻቸው ሊያዩ እስከሚችሉበት ርቀት ድረስ ሲመለከቱ፣ ነጭ የለበሱ ሴቶችና ህፃናት፣ ጥቋቁር ዣንጥላዎቻቸውን ዘርግተው፣ በትናንሽ አህያዎች ላይ ሆነው ይሰግራሉ። ሽማግሌ ወንዶች፣ ረዣዥም የእረኛ ዘንጐቻቸውን እየተመረኮዙ ይጓዛሉ። ደማቅ ቀለማት ያሏቸውን ካባዎች የደረቡ ብዙ ካህናትና መነኮሣት፣ መስቀሎቻቸውን በሰልፍ ሰድረው አለፉ። ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ከፀሐይዋ ቃጠሎ ለማዳን ሁሪያ ከፊፋቸው ላይ የሚቅጨለጨሉ የብር ደወሎች ያሉባቸው ትላልቅ፣ ቀያይና ጥቋቁር ጃንጥላዎች፣ በወጣት ባሪያዎቻቸው ተዘርግቶ ተይዞላቸዋል። ሁሉም ሰው ወደ አንድ የጥድ ዛፎች ጫካ ያመራል። የነዚህ ዛፎች የታችኞቹ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መሬት እየተጠማዘዙ ስለወረዱ ሕፃናት እየተንጠለጠሉባቸው ኸዋኸዋ ይጫወታሉ። ቤተክርስቲያኑ እምብዛም አይታይም። ስምንት ማዕዘን የሆነው ክብ የሣር ክዳን ጣሪያው፣ ተስተካክለው በተቆረጡና ከቤተክርስቲያኑ ግድግዳ ስምንት ጫማ ያህል ርቀው በበቀሉ ትላልቅ የጥድ ዛፎች ግንድ ላይ አርፏል። በነዚህ የዛፍ ግንዶችና በቤተክርስቲያኑ መካከል የጊንዲላ ወለሎችን በመጨመር ይህ ተፈጥሮአዊ ምሰሶ ወደ ክብ ሰገነትነት ተለውጧል።

ዲሚጥሮስ ጫማዎቹን ሲያወልቅ፣ መንገደኞችም በተመሣሣይ ፈፀሙ። የመጀመሪያውን የቤተክርስቲያኑን ክልል ጥሰው ለማለፍ ከቻሉ በኋላ፣ የተለያዩ የእድሜ ዘመናት ያላቸውን የፃድቃንና ሰማዕታት ሥነ ሥዕሎች ተመለከቱ። አንዳንዶቹ የባዘንታይን የአሣሣል ጥበብ ተፅዕኖ ያለባቸው ሲመስሉ፣ ብዙዎቹ ግን፣ በተለይ የአቢሲኒያውያን አሻራና